# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 123 ጥር 3 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



















ፎቶ፡ ሐዱሽ አብርሃ

# የዛሬና የነገ ሥራችንን ለማጠናከር

## ትውልዱ የራሱን የዲፕሎማሲ ዐሻራ ማኖር ይገባዋል

### - የዲፕሎማሲ ሳምንት ኤግዚቢሽን ተከፈተ


ገጽ 4




ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

## "የገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች የኢትዮጵያን ሙሉ ገፅታ የሚያሳዩ ናቸው"

### - አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ የቱሪዝም ሚኒስትር

ዳግም ከበደ

አዲስ አበባ፡- በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሃሳብ አመንጪነት እየተገነቡ የሚገኙ የገበታ ለሀገርና ሌሎች የቱሪዝም


በዲፕሎማሲ ሳምንት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## "ድርቁ ወደ ረሃብ እየተቀየረ ነው የሚለው ሃሳብ የተሳሳተ ድምዳሜ ነው"

### - አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም (ዶ/ር) የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር

አስቴር ኤልያስ

አዲስ አበባ፡- በአንዳንድ አካላት ዘንድ በኢትዮጵያ ያለው ድርቅ ወደረሃብ እየተቀየረ ነው በሚል እየተሰነዘረ ያለው ሃሳብ የተሳሳተ ድምዳሜ ነው ሲሉ የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም (ዶ/ር) አስታወቁ፡፡ ሡብዓዊ ድጋፉን በራስ አቅም ከመቻል አልፎ ትርፍ አምራች እስከመሆን እንደሚሠራም ገልጸዋል፡፡

ኮሚሽነር አምባሳደር ሽፈራው (ዶ/ር) ከኢፕድ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንዳስታወቁት፤ በአንዳንድ አካላት ድርቁ ወደረሃብ ተቀይሯል ሲባል የሚነገረው


በዲፕሎማሲ ሳምንት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

## ብሔራዊ ጥቅማችንን በዘሳቂነት የምናስከብረው ውስጣዊ አንድነታችንን በማጠናከር ነው

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- የሚታዩ ጫናዎችን ተቋቁመን ብሔራዊ ጥቅማችንን በዘላቂነት የምናስከብረው ውስጣዊ አንድነታችንን በማጠናከር መሆኑን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ገለጹ፡፡

አቶ ደመቀ መኮንን ‹‹የዲፕሎማሲ ሳምንት›› መክፈቻ ላይ ትናንት ባደረጉት ንግግር እንዳሉት፤ በየዘመኑ ያጋጠሙንን ፈተናዎች ተቋቁመን ብሔራዊ ጥቅማችንን እያስከበርን የመጣነው በሕብረታችንና በጠንካራ አንድነታችን ነው፡፡ የቅርብ ጊዜ


ብሔራዊ ጥቅማችንን .. ወደ ገጽ 4 ዞሯል









# ምክር ቤቱ የሰላም ሚኒስቴር ለጸጥታ ችግሮች መፍትሄ አበክሮ እንዲሠራ አሳሰበ

ማርቆስ በላይ

አዲስ አበባ፡- የጸጥታ ችግሮችን ለመቅረፍ የተቋቋመው የሰላም ሚኒስቴር ሥራውን በአግባቡ ሊወጣ እንደሚገባ ምክር ቤቱ አሳሰበ። የሰላም ሚኒስቴር በበኩሉ መንግሥት በተለያዩ አካባቢዎች በተለይ በአማራና ኦሮሚያ ክልሎች የተከሰቱ ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ምንጊዜም ዝግጁ መሆኑን አሳውቋል።

ስድስተኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሦስተኛ ዓመት የሥራ ዘመን 11ኛ መደበኛ ጉባዔ ትናንት ሲካሄድ የተለያዩ የምክር ቤት አባላት በተለያዩ የሀገሪቷ አካባቢዎች ያጋጠሙ የጸጥታ ችግሮች በርካታ ጉዳት እያደረሱ መሆኑንና ለመፍትሄው የሰላም ሚኒስቴር አበክሮ ሊሠራ እንደሚገባ አንስተዋል።

ችግሮቹ በውይይት መፈታት እንዳለባቸውና የሰላም ሚኒስቴር የሚጠበቅበትን ሃላፊነት ሊወጣ እንደሚገባ የምክር ቤት አባላት አሳስበዋል።

በተለይ በአማራና በኦሮሚያ ክልለሎች በርካቶች ላይ ጉዳት ያስከተሉ ግጭቶች መኖራቸውን አንስተው፤ ግጭቶቹ በሰላማዊ መንገድ ተፈትተው ህብረተሰቡ ሰላማዊ ሕይወት እንዲመለስ በአግባቡ መሥራት እንደሚገባ የተለያዩ የምክር ቤት አባላት ጠይቀዋል።

በግጭቶቹ ሳቢያ በርካታ ንጹሃን በመፈናቀላቸው ለችግር መዳረጋቸውን የምክር ቤት አባላት ጠቁመው፤ የሀገርና የሕዝብ ንብረት እየጠፋ ከመሆኑም በላይ የሀገር መከላከያ ሠራዊት ዋጋ እየከፈለ በመሆኑ ችግሮችን በውይይት ለመፍታት መሥራት ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

የሰላም ሚኒስትር አቶ ብናልፍ አንዱዓለም በበኩላቸው በሰጡት ምላሽና ማብራሪያ፤ መንግሥት በአማራና ኦሮሚያ ክልል ያለውን ግጭት በሰላማዊ ውይይቶች ለመቅረፍ ዝግጁ መሆኑን ገልጸዋል።

በአማራና ኦሮሚያ ክልል ያለው ግጭት በሰላማዊ ወይይቶች ለመቅረፍ በመንግሥት በኩል ጥረቶች እየተደረጉ መሆናቸውን ጠቅሰው በጦርነት የትኛውንም የሀገሪቱን ችግሮች መቅረፍ አይችልም ሲሉ ጠቁመዋል።

ኦሮሚያ ክልል ከሚንቀሳቀሰው የሸኔ ታጣቂ ቡድን ጋር ለመደራደር መንግሥት ተደጋጋሚ ሙከራዎችን ማድረጉን አስታውሰው፤ ልዩነቶች በውይይት ተቋጭተው የተፈለገው ሰላም እስኪሰፍን መንግሥት ለውይይት ዝግጁ መሆኑን አመላክተዋል።

ቤኒሻንጉልና በጋምቤላ ክልል የሚንቀሳቀሱትን ታጣቂዎችን ወደ ሰላማዊ መንገድ በማምጣት ተስፋ ሰጪ ሥራዎች ተሠርተዋል ያሉት አቶ ብናልፍ፤ ዘላቂ ሰላም እስኪመጣ ቀጣይነት ያላቸው ሥራዎች መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል።

የጦርነት መቋጫው ድርድር በመሆኑ በኦሮሚያና በአማራ ክልል ያሉ ታጣቂዎች ተጨማሪ ዋጋ ሳይከፈል ወደ ሰላማዊ መንገድ እንዲመጡ መጠየቁን የገለጹት ሚኒስትሩ፤ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል የሚገኙ የታጠቁ ሃይሎች ወደ ድርድርና ውይይት ሊመጡ እንደሚገባ ተናግረዋል።

በሀገሪቱ ባለፉት አምስት ዓመታት የነበሩ ችግሮች ምክንያታቸውና የተፈቱበት መንገድ በጥናት እንዲረጋገጥና እንዲለይ መደረጉን ጠቅሰው፤ በተለይም የወሰን፣ ማንነት፣ የአስተዳደራዊ፣ ፍትሀዊ ተጠቃሚነት፣ የመልካም አስተዳደርን ጨምሮ፣ የሀብት ክፍፍልና የተለያዩ ችግሮች መኖራቸውን አስረድተዋል።

ለሀገሪቱ የሰላም እጦትና የግጭት መበራከት ለውጥ ጋር ተያይዞ የመጡ ችግሮች መኖራቸውን በመግለጽ፤ የፖለቲካ ባህል አለመዳበርና ከታሪክና ትርክት ጋር ተያይዞ የሚመጡ ችግሮች መኖራቸውንም ጠቁመዋል።

በጥቂት ፖለቲከኞች አለመረጋጋትና የሥልጣን ፍላጎት የተነሳ ሕዝብ እየተሰቃ የሚሄድበት ሁኔታ ሊቆም ይገባል ያሉት አቶ ብናልፍ፤ ከመገዳደል ወደ መደራደር መምጣት የሚያስችል የፖለቲካ ባህልን ማዳበር ያስፈልጋል ብለዋል።

በተያያዘ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች አዋጅን መርምሮ አጸደቀ።

የምክር ቤቱ አባላት በቀረበው ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ላይ ሰፊ ክርክር ካደረጉ በኋላ ረቂቅ አዋጁ፣ አዋጅ ቁጥር 1314/2016 ሆኖ በሙሉ ድምፅ ጸድቋል።

የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታው ዶክተር እዮብ ተካልኝ በበኩላቸው በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች አሠራራቸውን አዘምነው በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ አዋጁ ጠቃሚ መሆኑን አስረድተዋል።

# 100 ሚሊዮን ዶላር ያስመዘገቡ 11 ኩባንያዎች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ሊሠማሩ ነው

## - የመቀሌ ኢንዱስትሪ ፓርክ በቅርቡ ወደ ሥራ ይገባል

ልጅዓለም ፍቅሬ



አዲስ አበባ፡- በአጠቃላይ 100 ሚሊዮን ዶላር ካፒታል ያስመዘገቡ 11 ኩባንያዎች በተለያዩ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው ለመስራት ስምምነት ማድረጋቸውን የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ገለፀ። በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት ሥራ አቁሞ የነበረው የመቀሌ ኢንዱስትሪ ፓርክ በቅርቡ ወደ ሥራ እንደሚገባ ኮርፖሬሽኑ አስታውቋል፡፡

የውል ስምምነቱ የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ አክሊሉ ታደሰና የየኩባንያዎቹ የሥራ ኃላፊዎች ትናንትና ተፈራርመዋል።

የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ አክሊሉ ታደሰ በስምምነቱ ወቅት እንደተናገሩት፤ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው የሚሠሩት 11 ባለሀብቶች በተለያዩ ዘርፎች የሚሰማሩ ሲሆን፤ በአጠቃላይ 100 ሚሊዮን ዶላር መነሻ ካፒታል ያስመዘገቡ ናቸው፡፡

ኢንቨስተሮቹ በአምስት የተለያዩ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ላይ ይሠማራሉ ያሉት አቶ አክሊሉ፤ በመቀሌ፣ በጅማ፣ በቦሌ ለሚ፣ በባህርዳር እንዲሁም በቂሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚሠማሩ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

በመቀሌ፣ በጅማና በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ላይ በእያንዳንዳቸው ሦስት ኢንቨስተሮች የሚገቡ ሲሆን፣ የተቀሩት በባህርዳርና ቂሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው ኢንቨስት የሚያደርጉ መሆናቸው አስረድተዋል።

እንደ አቶ አክሊሉ ገለጻ፤ ባለሀብቶቹ በአግሮ ፕሮሰሲንግ፣ በአልባሳትና በጨርቃጨርቅ፣ በመድሃኒት እንዲሁም በፕላስቲክ ማምረት ዘርፍ የሚሠማሩ ናቸው።

ባለሀብቶቹ 31 ሺህ ካሬ ሜትር የማምረቻ ሼዶችና አራት ነጥብ አምስት ሄክታር የለማ መሬት ተረክበው ወደ ሥራ ይገባሉ ያሉት አቶ አክሊሉ፤ በፓርኮቹ ኢንቨስት ከሚያደርጉ መካከል አብዛኞቹ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች እንደሆኑ አመላክተዋል፡፡

በስምምነቱ ከ50 ሺህ በላይ ለሚሆኑ አርሶ አደሮች ዘላቂ የሆነ የገበያ ትስስር እንደሚፈጠር ገልጸው፤ አልሚዎቹ ወደሥራ ሲገቡም ከአምስት ሺህ በላይ አዳዲስ የሥራ እድል እንደሚፈጠር ጠቁመዋል።

እንደ አቶ አክሊሉ ገለጻ፤ የመቀሌ ኢንዱስትሪያል ፓርክ የተወሰነ ጥገና ተደርጎለት ሥራ መጀመር የሚያስችለው ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል። ሦስት አዳዲስ ኩባንያዎች በፓርኩ ኢንቨስት ለማድረግ ስምምነት አድርገዋል።

የመቀሌ እንዱስትሪ ፓርክ በአጭር ጊዜ ወደ ሥራ እንዲገባ ኮሚቴ ተቋቁሞ ሲሠራ ቆይቷል ያሉት አቶ አክሊሉ፤ በፓርኩ የሚሰሩ ሰራተኞች ደሞዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል ብለዋል።

በተለይ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ውጤታማ ለማድረግ የተሟላ ሎጂስቲክ ወሳኝ ነው፤ በቅርቡ ኢትዮጵያ ያገኘችው የባህር በር ዘርፉን ለማሳደግ ጉልህ ሚና ይጫወታል ሲሉ ተናግረዋል።



# የአውሮፓ ህብረት የሁለት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር ድጋፍ ስምምነት ፈረመ

## - ድጋፉ 200 ሺህ ሰዎችን ተጠቃሚ ያደርጋል

መስከረም ሰይፉ

አዲስ አበባ፡- የአውሮፓ ህብረት 200 ሺህ ለሚሆኑ በግጭትና በተፈጥሮ አደጋ ለተጎዱ ዜጎች የሚውል የሁለት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር ድጋፍ ስምምነት ፈረመ፡፡

የአውሮፓ ህብረት ከተለያዩ ሠብዓዊ አገልግሎት ከሚሰጡ ተቋማት ጋር በመተባበር በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉና ሠብዓዊ ችግር ውስጥ ለወደቁ ዜጎች የ 2 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር ድጋፍ ስምምነት በትናንትናው እለት ፈርሟል፡፡

በኢትዮጵያ የአውሮፓ ህብረት አምባሳደር ሮላንድ ኮቢያ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ የተከሰቱ ግጭቶች እና የተፈጥሮ አደጋዎች በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ብሎም በምግብ ዋስትና ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል።

የተፈረመው ድጋፍም በግጭት የተፈናቀሉ፤ ጾታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች ፤ በተለያዩ የተፈጥሮ አደጋዎች ለተጎዱ ማህበረሰቦች እና አረጋውያን እንዲሁም ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ኢትዮጵያውያን በቀጥታ ተጠቃሚ የሚያደርግ ይሆናል ብለዋል።

ይህ መርሀ ግብር ለሶስት ዓመታት የሚቆይ ሲሆን ከ 2 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብሩ (43 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዩሮ) ድጋፍ ፕሮግራም ውስጥ 2 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብሩን የአውሮፓ ህብረት ድጋፍ የሚደረግ መሆኑን ጠቅሰው፤ ቀሪውን ደግሞ የጀርመን መንግሥት፣ የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን፣ የዴንማርክ ቀይ መስቀል እንዲሁም የዓለም አቀፉ የስደተኞች ድርጅት እንደሚያደርጉ ጠቅሰዋል፡፡

መርሀ ግብሩ 200 ሺህ የሚሆኑ ዜጎችን በቀጥታ ተጠቃሚ ማድረግ የሚችል ነው ያሉት አምባሳደር ሮላንድ፤ በተለይ በአማራ፣ አፋር፣ ትግራይና በቤኒሻንጉል ክልሎች በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ችግሮች ለተፈናቀሉ ዜጎች ዘላቂነት ባለው መልኩ መልሰው እንዲቋቋሙ ለማስቻል የሚያደርግ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ኢትዮጵያ ከአራት ሚሊዮን በላይ የውስጥ ተፈናቃይ እንዳለ የገለጹት አምባሳደሩ፤ በመርሀግብሩም ድጋፍ በሚደረግባቸው ክልሎች በግጭት የተጎዱና ከፍተኛ የጉዳት ደረጃ ያስተናገዱ ዞኖች ትኩረት እንደሚሰጣቸው አክለዋል፡፡

ድጋፉ የተለያዩ የወደሙ መሠረተ ልማቶችን መልሶ ለመገንባት፣ በግብርናና ሌሎች ዘርፎች ላይ ክህሎት መር ሥልጠና ለመስጠት፣ የፋይናይስ አገልግሎት ለመስጠትና የሥራ እድል ለመፍጠር መሠረታዊ አገልግሎቶችን ለማሻሻል ያለመ ነው ብለዋል።

በኢትዮጵያ የዓለም አቀፍ የፍልሰት ድርጅት ተወካይ አቢባቶ ዋኔ በበኩላቸው፤ በብዙ የኢትዮጵያ ክፍሎች በርካታ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡

ይህ መርሀ ግብርም ባለፉት ሶስት ዓመታት በአፋር፣ በአማራ፣ በትግራይ እና በቤኒሻጉል ጉሙዝ ክልሎች በተከሰቱ ግጭቶች አካባቢያቸውን የለቀቁ ተፈናቃዮች የሥነልቦናና ኢኮኖሚያዊ ድጋፎችን የሚያገኙበት ይሆናል ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያ በሚደረጉ ግጭቶች የተፈናቃዮች ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ መምጣቱን የተናገሩት ተወካይዋ፤ ሠብዓዊ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ድጋፍ ለማድረግ ጣልቃ መግባታቸውን እንዲቀጥሉም አሳስበዋል፡፡

# ሕገወጥ የዜጎች

## ዝውውርን ስለመከላከል እየተሠራ ያለው ሥራ በቂ አይደለም

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- ሕገወጥ የዜጎችን ዝውውርን ለመከላከል እየተሠራ ያለው ሥራ ችግሩን ቀንሷል ማለት አያስችልም ሲሉ የፍትህ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ በላይሁን ይርጋ ተናገሩ።

በአዲስ አበባ ከተማ ሕገወጥ የዜጎችን ዝውውር ወንጀል ለመከላከል ምክር ቤት ተቋቁሞ እየተሠራ ሲሆን ምክርቤቱ በትናትናው ዕለት የሥራ ሪፖርት እና እቅዱን ለባለድርሻ አካላት አቅርቧል።

በሪፖርቱ ላይ ተገኝተው አስተያየት የሰጡት የኢፌዴሪ ፍትህ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ በላይሁን እንደተናገሩት፤ ሕገወጥ የዜጎችን ዝውውርን ለመከላከል እየተሠራ ያለው ሥራ ችግሩን ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ አልተሠራም። ችግሩም ከመሠረቱ እንዳይፈታ ያደረገው ዘርፉ የሚመለከታቸው አካላት ቅንጅታዊ አሠራራቸው ዝቅተኛ በመሆኑ ነው።

በ2012 ዓመት ምህረት ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ለመከላከል የወጣው አዋጅ ቁጥር 11/ 78 የተለያዩ መዋቅሮችን በጥናት ተመስርተው በቅንጅት እንዲሠሩ የሚያስቀምጥ አዋጅ ቢጸድቅም ተግባራዊ ሳይሆን አራት ዓመታት አስቆጥሯል ብለዋል።

ሕገወጥ የዜጎችን ዝውውር ወንጀል ለመከላከል እየተሠራ ባለው ሥራ ቅንጅታዊ አሠራሩ እንዳይጠናከር ካደረጉ ተግዳሮቶች መካከል በሕጉ የተመላከቱ ነገሮች በክልሎች ተግባራዊ አለመሆናቸው ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ወንጀሉ አንድ ቦታ ላይ የሚፈጸም ሌላ ቦታ ላይ የሚቆም ባለመሆኑ ከክልሎችና ከተቋማት ጋር በቅንጅት መሥራት ያስፈልጋል ሲሉ ገልጸዋል።

ሕገወጥ የዜጎችን ዝውውር ወንጀል ለመከላከልና በክልሎች መካከል ቅንጅታዊ አሠራር እንዲኖር ክትትልና ድጋፍ እንደሚደረግ ጠቁመዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ገንዘብ ከሚቀሳቀስባቸው ወንጀሎች አንዱ ሕገውጥ የሰዎች ዝውውር ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ወንጀሉን ለመከላከል እየተሠራ ያለው ሥራ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለዋል።

የወንጀሉም መበራከት ዋነኛ መንስኤው ሥራ አጥነት ነው፤ ለዜጎች የሥራ እድል በመፍጠር የወንጀሉን ቁጥር መቀነስ ይገባል ሲሉ አብራርተዋል።

ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት እያንዳንዱ ቢሮ በመደበኛ እቅዱ ውስጥ አካቶ መሥራት ይኖርበታል ሲሉ አክለዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገራት ድርጅቶችን በማደራጀት ሕገወጥ የዜጎችን ዝውውር ወንጀል ለመከላከል በትኩረት ይሠራል። ከተማ አስተዳደሩ የጀመራቸውን ሥራዎች የሚደግፍ ይሆናል ሲሉ አመላክተዋል።



ሠላማዊት ካሳ



ሙሐመድ እድሪስ (ዶ/ር)



አቶ ስለሺ ግርማ

# የሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ጥሪ ተደራሽ ያልሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ለመድረስ አዲስ በር የከፈተ ነው

## - ጥሪውን ተከትሎ በርካቶች ወደ ሀገር ቤት እየገቡ ነው

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ለሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ያደረጉት ጥሪ ተደራሽ ያልሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ለመድረስ አዲስ በር የከፈተ መሆኑ ተገለጸ፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት፣ የቱሪዝም ሚኒስቴርና የዳያስፖራ አገልግሎት በተለያዩ ሀገራት የሚኖሩ የሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገር ቤት እንደሚጡ የቀረበላቸውን ጥሪ መነሻ በማድረግ እስካሁን ድረስ የተከናወኑ ተግባራትን እና በቀጣይ ያሉ እቅዶችን አስመልክተው ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አማካኝነት በውጭ ሀገር ለሚኖሩ ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን የቀረበው ጥሪ ተደራሽ ያልሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን የመድረስ ዓላማን ያሳካ እንደሆነና የቀረበውን ጥሪን ተከትሎ ከተለያዩ ሀገራት በርከት ያሉ የሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገር ቤት እንደገቡ በማብራሪያው ተጠቅሷል፡፡

የዳያስፖራ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ሙሐመድ እድሪስ (ዶ/ር)፤ ቁጥሩ እስከ 20 በመቶ ሊገመት የሚችል በውጭ ሀገር የሚኖሩ የሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን መኖራቸውን በመግለጽ፤ ይህንን ትውልድ ከሀገሩ ጋር ማስተሳሰር መቻል አለበት ብለዋል፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ አጀንዳ የሆነው የማንነት ቀውስና ማረፊያ የለሽ ትውልድ እንደሚያጋጥም ገልጸው፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህንን ጥሪ ሲያስተላልፉ ትውልዳዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አንጻር ጭምር እንደሆነ አመላክተዋል፡፡

ጥሪው እንደ ትልቅ አጋጣሚ የሚታይ መሆኑን የገለጹት ዳይሬክተሩ፤ “ያልደረስንባቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች መድረስ የሚለውን ዓላማ ያሳካንበት አዲስ በር የከፈተ ነው” ብለዋል፡፡ ጥሪ ለተደረገላቸው ወገኖችም “የሀገር አለኝ” ስሜትን የፈጠረ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ ጥሪው ይፋ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ከፍተኛ መነቃቃት ተፈጥሯል፡፡ ከጥሪው ዓላማ አንጻር ከሀገራቸው ጋር የሳሳ ግንኙነት እንዳላቸው የሚታሰቡ ሰዎች መጠራታቸው ልዩ ስሜትን ፈጥሮባቸዋል፡፡

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አግልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ካሳ በበኩላቸው፤ የሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያውያን ጥሪ ወደ ሀገር ቤት መጥተው ከሀገራቸው ባህልና ማንነት ጋር ትስስር እንዲኖራቸው፤ የተለያዩ የቱሪስት መስህቦችን እንዲጎበኙና በሀገራቸው የልማት ሥራዎች ላይ የራሳቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ለማድረግ እንዲሁም ወላጆቻቸው የገነቧትን ሀገር እንዲያውቁ ለማድረግ እንደሆነ አስታውቀዋል፡፡

በሦስት ዙር በተከፋፈለው ሀገራዊ ጥሪ በመጀመሪያው ምዕራፍ በርከት ያሉ የሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው መምጣት መጀመራቸውንና ደማቅ አቀባበል እየተደረገላቸው መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ እየተደረገ ያለው አቀባበል በቀጣይ ምእራፍ ለሚመጡ ዜጎች ተነሳሽነትን የፈጠረ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ላይ ያለውን የሠላምና ጸጥታ ሁኔታ አስተማማኝ ማድረግ እንዲቻል የተለያዩ ኦፕሬሽኖች እየተደረጉ እንዳለ የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ከተማዋን ለነዋሪዎቿ እንዲሁም ወደ ሀገር ቤት ለሚመጡት እንግዶች ምቹ ለማድረግ ኦፕሬሽኑ አሁንም ተጠናክሮ መቀጠሉን ጠቁመዋል፡፡


የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ በበኩላቸው ሀገራዊ ጥሪው ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ሀገራቸውን እንዲያውቁ፣ ሀገራዊ ትስስር እንዲፈጥሩና ወላጆቻቸው የገነቧትን ሀገር እንዲያውቁ የተደረገ ነው ብለዋል፡፡ በዚህም በርካቶች ወደ ሀገር ቤት እንዲገቡ ሰፊ ሥራዎች መሠራታቸውን ጠቅሰው እስካሁንም እየገቡ እንዳለ ገልጸዋል፡፡

በሀገራቸው በሚኖራቸው ቆይታ በተለይም “ከብዝኃ ባህልዎ ጋር ይተዋወቁ” በሚለው ፕሮግራም የኢትዮጵያ ሳምንት፣ የኢትዮጵያን ምድረ ቀደምትነት የሚያስተዋውቁ ሁነቶች፣ የጉብኝት ፕሮግራም፣ የኢትዮጵያን ይግዙ ሁነትና በብዝኃ ባህል ላይ ያተኮሩ መርሀ ግብሮች እንደሚኖሩ ተናግረዋል፡፡

ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን በውጭ ሀገራት የተወለዱ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም ከእድሜ አንጻር በህጻንነታቸው ከኢትዮጵያ ወጥተው ብዙ ጊዜ በውጭ ሀገር የኖሩና ከሀገራቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማደስ የሚፈልጉ መሆናቸው ተገልጿል፡፡

# በኢትዮጵያ 19 ከመቶ ሴቶች የፎሊክ ንጥረ ነገር እጥረት ይገጥማቸዋል

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**



ዶክተር እንዳለ አማረ



ዶክተር ፋሲል መንበር

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ከሚኖሩ ሴቶች 19 ከመቶ ያህሉ የፎሊክ ንጥረ ነገር እጥረት የሚገጥማቸው መሆኑን የጤና ዘርፍ ተመራማሪዎች አስታወቁ።

በቅዱስ ጳውሎስ ሚሌኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የሕጻናት ህክምና ክፍል ረዳት ፕሮፌሰር እና የሕጻናት ስፔሻሊስት ዶክተር ፋሲል መንበር ለኢትዮጵ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ፎሊክ ቀይና ነጭ የደም ሴሎች ሥራቸውን በአግባቡ እንዲሠሩ የሚያስችል ንጥረ ነገር ነው። በሀገራችን ሴቶች ላይ ችግሩ የተለመደ ነው።

አንዳንድ ጥናቶች እንዲያውም 40 ከመቶ ድረስ ሴቶች የንጥረ ነገሩ እጥረት የሚገጥማቸው መሆናቸውን እንደሚገልጹ በመጥቀስ የችግሩን ስፋት ይገልጻሉ።

የፎሊክ እጥረት ሲከሰት መጀመሪያ የምትጎዳው እናት ናት ያሉት ዶክተር ፋሲል፤ እጥረቱ የድካም ስሜትና ቶሎ በበሽታ የመጠቃት ችግሮችን እንደሚያስከትል ገልጸዋል።

የፎሊክ እጥረት ያለባት ሴት በምትወልዳቸው ሕጻናት ላይ የአእምሮ ጤና መታወክ፣ የጭንቅላት ዕድገት መዛባትና የጀርባ አጥንት ክፍተት የሚያጋጥም መሆኑን ጠቅሰው፤ ከዚህ በተጨማሪ የሰውነት አካል አለመታዘዝ፣ የአጥንት በአግባቡ አለማደግና የሽንት ፊኛ በአግባቡ ሥራውን ያለመስራት ችግር እንደሚገጥምም አብራርተዋል።

ብዙ እናቶች እርግዝናቸውን የሚያውቁት አንድና ሁለት ወራት ካለፈ በኋላ መሆኑን ያነሱት ዶክተር ፋሲል፤ ይህ ሁኔታ እናት ቀድማ ስለራሷ ጤንነት እንድታውቅ እድል የሚሰጥ ባለመሆኑ በልጁ ላይ ሊከሰት የሚችልን ችግር ቀድሞ መከላከል እንደማይቻል ይናገራሉ።

ከዚሁ ጋር አያይዘው ማንኛውም እናት ከእርግዝና በፊት ስለ ራሷ ጤንነት በምርመራ ማወቅ እንዳለባትና የፎሊክ እጥረት ካለባትም ከእርግዝና በፊት ንጥረ ነገሩን በክኒን መልክ መውሰድ እንደሚገባት ይመከራሉ።

የፎሊክ ንጥረ ነገር ምንጭ የሆኑ እንደ ጎመን፣ ቆስጣ፣ ሰላጣ የመሳሰሉት አረንጓዴ አትክልቶችን፣ ከፍራፍሬ አቮካዶን፣ አተርና ባቄላ የመሳሰሉ ጥራጥሬዎች እንዲሁም እንቁላልና ስጋን አሰባጥሮ በመመገብ ችግሩን መከላከል እንደሚቻል አመላክተዋል።

ዶ/ር ፋሲል ጥናቶችን ጠቅሰው እንደነገሩን፣ በዓለም ላይ በዓመት እስከ 300 ሺህ ሕጻናት የፎሊክ እጥረት ከሚያስከትላቸው ችግሮች ጋር ሲወለዱ፣ በሀገራችን ከ10 ሺህ ሕጻናት በ65ቱ ላይ ችግሩ ይከሰታል።

በኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የምግብ ሳይንስ ከፍተኛ ተመራማሪ ዶክተር እንዳለ አማረ በበኩላቸው፤ በኢትዮጵያ ከ19 ዓመት እስከ 49 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ 19 ከመቶ ሴቶች ፎሊክ እጥረት እንደሚገጥማቸውና በተጨማሪም ከሚጠበቀው ክብደት በታች መሆናቸውን ተናግረዋል።

ኢንስቲትዩቱ የሠራውን ጥናት አጣቅሰው ማብራሪያ የሰጡት ዶክተር እንዳለ፣ የንጥረ ነገር እጥረቱ እድሜያቸው በመውለጃ እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሴቶች ላይ ነው ብለዋል።

ይህ በመሆኑም አዲስ በሚወለዱ ህጻናት የአእምሮና አካላዊ ጤና ላይ ከፍተኛ ችግር እያስከተለ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

የፎሊክ እጥረት የሚያስከትላቸውን የጤና ችግሮች ለመቅረፍና የእናትና ልጅ ጤናን ለመጠበቅ እንደ ማኅበረሰብ የአመጋገብ ሥርዓታችንን ማስተካከል ይገባናል ሲሉም መክረዋል።

በተለይም ተመሳሳይ የምግብ አይነቶችን ደጋግሞ ከመመገብ ይልቅ ማግኘት የምንችላቸውን ምግቦች በማሰባጠር ችግሩን መቀነስ እንደሚቻል አመላክተዋል።

# የዛሬና የነገ ሥራችንን ለማጠናከር ትውልዱ የራሱን የዲፕሎማሲ ዐሻራ ማኖር ይገባዋል

## - የዲፕሎማሲ ሳምንት ኤግዚቢሽን ተከፈተ

**ሞገስ ፀጋዬና ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- የዛሬና የነገ ሥራችንን ውጤታማነት ለማጠናከር ትውልዱ የራሱን የዲፕሎማሲ ዐሻራ ማኖር ይገባዋል ሲሉ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ገለጹ። "ዲፕሎማሲያችን ለብሔራዊ ጥቅማችን" በሚል መሪ ቃል የተዘጋጀው የዲፕሎማሲ ሳምንት ኤግዚቢሽን ትናንትና በሳይንስ ሙዚየም ተከፍቷል።

የእለቱ የክብር እንግዳ የሆኑት የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ባደረጉት ንግግር እንዳስታወቁት፤ የዛሬና የነገ የዲፕሎማሲ ሥራችንን ለማጠናከር ካስፈለገ ትውልዱ በዲፕሎማሲ ሥራው ላይ የራሱን ዐሻራ ሲያስቀምጥ ይገባል።

በታሪካችን ሂደት ኢትዮጵያን በበጎ የሚያስጠሯት ስኬቶችን ያስመዘገበችና በመሪዎቿ አማካኝነት ተደማጭነትን ያተረፈች ሀገር መሆኗን ማወቅ እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቷ ገለጻ፤ አሁንም ኢትዮጵያ በርካታ ዲፕሎማሲያዊ ሥራን ትሻለችና ወጣቶች፣ ሴቶች፣ ምሁራንና ሁሉም ዜጋ በዚህ ሥራ ለመሰማራት ማወቅና መማር ይጠበቅባቸዋል።

በቀጣይም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተገቢውን ቦታ ለማግኘት እና ተደማጭነትን ለማትረፍ ታሪካችንን መጠበቅና ማወቅ አለብን ሲሉ አስገንዝበዋል።

ወደፊት መሄድ የምንችለው እርስ በዕርስ በመዋጋትና ሌሎች በሰሩት ታሪክ እየተመካን ሳይሆን እያንዳንዳችን የራሳችንን ዐሻራ በማስቀመጥ ነው ብለዋል።

ከታሪኩ ጋር ያልታረቀ ሕዝብ፣ ታሪኩን ለመበረዝና ለማጥፋት የሞከረ ትውልድ መሠረቱ የተናጋ ይሆናል ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ ወደድንም ጠላንም ታሪካችንን ማወቅና መማር አለብን ሲሉ ተናግረዋል።

ሀገራችንን ወደ21ኛው ክፍለ ዘመን ለማሻገር ዲፕሎማሲ ወሳኝ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ ቴክኖሎጂን በመጠቀምና ሁሉም ዜጋ የድርሻውን በመወጣት ዓለም ከደረሰበት መድረስ ይገባናል ሲሉ አመላክተዋል።

ብዙ ታሪክ የሌላቸው ሀገራት ሥራቸውን በማውጣት ዓለም አቀፍ እውቅና እያገኙ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያም ያላትን ታሪክ በሚገባ ማሳወቅ አለባት ብለዋል።

ዲፕሎማሲ በሀገሮች መካከል የዳበረ መልካም ግንኙነት እንዲኖር የሚያግዝ በመሆኑ ዓለም ባለችበት የዲፕሎማሲ ሥርዓት እኩል መጓዝ እንድንችል የዲፕሎማሲ ሥርዓታችንን ማሳደግ አለብን ሲሉ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ታሪክ የ 116 ዓመታት ታሪክ አለው ያሉት ፕሬዚዳንቷ፣ በነዚህ ዓመታት የተሳካ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ በየሀገራት ያሉ አምባሳደሮችና ኢትዮጵያውያን በሙሉ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ በዓለም አደባባይ በበጎ የምትነሳበትን የዲፕሎማሲ ስኬቶችን አስመዝግባለች ያሉት ወይዘሮ ሳህለወርቅ፤ አውደ ርዕዩ እውነተኛውን የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ታሪክና እውነተኛ ገጽታ ያሳያል ብለዋል።

የውጭ ፖሊሲ የአንድ ሀገር የውስጥ ነጸብራቅ ነው፤ በዕለቱ የተከፈተው የፎቶግራፍ አውደ ርዕይም ይህንኑ ያሳያል ብለዋል።

ኢትዮጵያ ነጻነቷን ጠብቃ መቆየቷንና የበርካታ ዓለም አቀፍ ድርጅት መስራች መሆኗን በጉልህ የሚያሳይ ታሪካዊ የፎቶግራፍ አውደ ርዕይ መሆኑን አመላክተዋል።

አውደርዕዩ የዲፕሎማሲያችንን እውነተኛ መልክ የሚያሳይ የታሪክ መስታወት ብቻ ሳይሆን የመጪውን ዘመን የዲፕሎማሲ ጉዞ የምንዳስስበት፣ የውጭ ፖሊሲያችን መገለጫ የሆኑ የትኩረት መስኮች የሚታዩበት መሆኑን አስታውቀዋል።

አውደርዕዩ የዲፕሎማሲን ታሪክ እና ፖሊሲ ህብረተሰቡ እንዲረዳውና ከታሪካችን እንድንማር ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት መሆኑን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ የበርካታ ዓመታት የዲፕሎማሲ ታሪክ ያላት ሀገር መሆኗን ገልጸው፤ በነዚህ በርካታ ዓመታት የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅምንና ሀገራዊ ክብርን በዓለም ዙሪያ ሲያስጠብቅ የዘለቀው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በተለያዩ ሀገራት የሚገኙ ሚሲዮኖች፣ ዲፕሎማቶችና ባለሙያዎች አመስግነዋል።

በመድረኩ ተቀማጭነታቸውን አዲስ አበባ ያደረጉ አምባሳደሮች፣ የዓለም አቀፍ ተቋማት ድርጅት ሃላፊዎችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

የዲፕሎማሲ ሳምንት ኤግዚቢሽኑ ከጥር 2- 24 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ለሕዝብ ክፍት ሆኖ ይቆያል።

# ብሔራዊ ጥቅማችንን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ዘርፈ ብዙ ጫናዎችን ተቋቁመን የዘለቅነውም በሕዝባችን ጽናትና አብሮነት ነው።

በመሆኑም አሁን የሚታዩትን ጫናዎች ተቋቁመን ብሔራዊ ጥቅማችንን በዘላቂነት የምናስከብረው ውስጣዊ አንድነታችንን በማጠናከር ነው ብለዋል።

ከታሪክ እንደተማርነውና አሁንም እንደምንመለከተው የሀገራችንን መጠንከር በበጎ የማይመለከቱ ኃይሎች አሉ ያሉት አቶ ደመቀ፤ ስንወረር ድምጻቸውን ያላሰሙ፣ ዘላቂ ጥቅማችንን ለማረጋገጥ እውነታን መሠረት አድርገን በምንራመደው አንድ ርምጃ ሁሉ ጩኸቱና ጫናው ብዙ ነው። ይህም ወደፊት ምን ያህል ፈተና እንዳለና የተጠናከረ ሥራ እንደሚጠይቀን የሚያሳይ ነው ብለዋል።

ከዚህ ተጽዕኖ ለመውጣት የድላችን አልፋና ኦሜጋ ውስጣዊ ጥንካሬያችን መሆኑን ጠቁመው፤ ጠንካራ ዲፕሎማሲና የውጭ ግንኙነት መሠረቱ የውስጥ ጥንካሬና አብሮነት ነው። በሁሉም መስክ ኢትዮጵያ አሸናፊ ሆና እንድትዘልቅ ማንኛውንም የውስጥ ችግር በሰላማዊ መንገድ ለመፍታትም ሁሉም ወገን የሰላም አምባሳደር መሆን አለበት ብለዋል።

ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረውና ብዙ ውጣ ውረዶችን ያለፈው የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ታሪክ ሰፊ መሆኑን አስታውሰው፤ ‹‹የዲፕሎማሲ ሳምንት›› አውደ ርዕይ ከሰፊው ባህር በጥቂቱ ጨልፎ እስካሁን የተሠሩ ሥራዎችን ለማሳየት የተዘጋጀ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ዝግጅቱ ከታሪክ ሂደቶች ተምረን አሁን ያለንበትን የዲፕሎማሲ ትልም ለማሳካትና የወደፊቱን የውጭ ግንኙነታችንን በጠንካራ መሠረት ላይ ሆነን ለማስፈጸም እንዲረዳ ያለመ መሆኑንም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጨምረው ገልጸዋል።

"ዲፕሎማሲያችን ለብሔራዊ ጥቅማችን" በሚል መሪ ቃል በሳይንስ ሙዚየም የተዘጋጀው የዲፕሎማሲ ሳምንት አካል የሆነው የፎቶግራፍ አውደ - ርዕይ ከጥር 2 እስከ 24 ቀን 2016 ዓ.ም ለጎብኚዎች ክፍት ሆኖ እንደሚቆይም ተመላክቷል።

# "የገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

መዳረሻ የልማት ፕሮጀክቶች የኢትዮጵያን ሙሉ ገፅታ የሚያሳዩ ናቸው ሲሉ የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ ተናገሩ። ፕሮጀክቶቹ በፈጠሩት መነቃቃት የሀገር ውስጥና የውጭ ቱሪስት ፍሰቱ እየጨመረ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

አምባሳደሯ ትናንት በፅህፈት ቤታቸው ከመገናኛ ብዙሃን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ላይ እንደተናገሩት፤ የገበታ ለሸገር፣ ገበታ ለሀገር እና ገበታ ለትውልድ መዳረሻ ልማቶች የኢትዮጵያን የቱሪዝም ሀብቶችና መስህቦች በሙሉ ገፅታ ያሳያሉ።

ከዚህ ቀደም በነበረው ልምድ የቱሪስት እንቅስቃሴው በተወሰኑ ቦታዎች ላይ የተመሠረተ ነበር ያሉት ሚኒስትሯ፤ አሁን ተገንብተው የተጠናቀቁት የቱሪዝም መስህቦች ሙሉ ገፅታ ከማስተዋወቅ አንፃር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል። የቱሪስት ፍሰቱም ባለፉት ዓመታት ጨምሯል ብለዋል።

በኢትዮጵያ የሚገኙ መስህቦችን ሙሉ በሙሉ ማሳየት እና የቱሪስቶች መዳረሻ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑንም ገልፀዋል።

ከዘርፉ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን ማግኘትና እድገት ማስመዝገብ የሚቻለውም ሁሉንም ሀብቶች መጠቀም፣ ማስተዋወቅና የቱሪስት መዳረሻ ማድረግ ሲቻል መሆኑንና የፕሮጀክቱ ዋነኛ ግብም ይህንን መሠረት ማድረጉን አምባሳደሯ ገልጸዋል።

የገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች እንደሚገኙ የገለፁት አምባሳደሯ፤ በቀጣይ ተግባራዊ የሚሆነው የገበታ ለትውልድ ፕሮጀክትም እንዲሁ ከዚህ ቀደም ባልተለመዱ የኢትዮጵያ ክፍሎች ተግባራዊ እንደሚሆንና የቱሪስት መዳረሻ አማራጮችን እንደሚያሰፋ አብራርተዋል።

አምባሳደሯ በአፅእኖት እንደተናገሩት፤ የገበታ ለሀገር እና የመዳረሻ ልማት ፕሮጀክቶቹ ዋና ዓላማ መሠረተ ልማቱን ወደ ልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች ማዳረስ ነው። ፕሮጀክቶቹ የሎጅዎች ግንባታ ላይ ብቻ ያተኮሩ ሳይሆኑ የቱሪስት መሠረተ ልማትን ማስፋፋት ያለሙም ጭምር ናቸው።

‹‹በቱሪዝም ዘርፍ ላይ መንግሥት አስቻይ ፖሊሲ፣ የሕግ ማእቀፍ ማውጣት እና የግል ዘርፉን የማበረታታት ሚና ነው ያለው›› ያሉት ሚኒስትሯ፤ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሃሳብ አመንጪነት እየተገነቡ ያሉ የገበታ ለሸገር፣ የገበታ ለሀገር እንዲሁም የገበታ ለትውልድ ፕሮጀክቶች የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ለማነቃቃት ተግባራዊ እየተደረጉ መሆኑን አንስተዋል።

በዋናነት በመንግሥት እየተሠሩ ያሉ የልማት ሥራዎች የግሉ ዘርፍ ደፍሮ መግባት እንዲችል ለማድረግ መሆኑንም ገልፀዋል።

በአብዛኛው የግል ዘርፉ በከተማ አካባቢዎች ከመከማቸት ባሻገር በድፍረት በርቀት ያሉ አካባቢዎችን ማልማት ላይ ውስንነት እንደሚታይበት ያነሱት ሚኒስትሯ፤ በዚህ ምክንያት መንግሥት በተወሰኑ የልማት ጉዳዮች ላይ እየተሳተፈ እንደሚገኝ አብራርተዋል። ይህ በመደረጉ ምክንያትም ተጨባጭ ውጤቶች እየተመዘገቡ መሆኑን ተናግረዋል።

በወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም፣ በጨበራ ጩርጩራ እና ሌሎች መዳረሻዎችም የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ እያደረገ መሆኑን በመጥቀስ እንደ ሀገር ኢትዮጵያ ያላትን መስህብ በሙሉ ገፅታ ማሳየት እንዲቻል እድል መከፈቱን ገልፀዋል።

የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ከዚህ ቀደም ወዳልተለመዱ የኢትዮጵያ ክፍሎች የመጓዝ እድሉን በእነዚህ ፕሮጀክቶች አማካኝነት ማግኘት መቻላቸውንም አብራርተዋል።

በዚህ ምክንያት ወደ መስህብ ሥፍራዎቹ የሚጓዙ ጎብኚዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥሩ እያሻቀበ ነው ብለዋል።

ሚኒስትሯ አያይዘው እንደተናገሩት፤ የቱሪዝም ሚኒስቴር በቅርቡ የለሙትን መዳረሻዎች ጨምሮ የኢትዮጵያን የቱሪዝም መስህቦች ለማስተዋወቅ እየሠራ ነው።

የሀገር ውስጥ ቱሪዝም እንዲነቃቃ የተለያዩ መርሀ ግብሮችን በመቅረፅ ተግባራዊ እያደረገም ነው ብለዋል።

ባለፈው ዓመት ይፋ የተደረገው "ልወቅሽ ኢትዮጵያ" ንቅናቄም አንዱ እንደሆነ ያነሱት አምባሳደሯ፤ የውጭ ቱሪስት ፍሰቱን ለመጨመርና የሀገሪቱን ገፅታ ለመገንባትም በልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ በመገኘት የማስተዋወቅ ሥራ እያከናወነ እንደሚገኝ አሳውቀዋል።

# "ድርቁ ወደ ረሃብ እየተቀየረ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ድምዳሜ የተሳሳተ ነው። በኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ስሌት ድርቁ ወደረሃብ አልተቀየረም።

ድርቁ ወደ ረሃብ እየተቀየረና ሰው እየሞተ ነው አይነት መደምደሚያ ላይ ለመድረስ የራሱ የሆነ ክትትል እና የራሱ የሆነ ማረጋገጫ መሥራትን የሚጠይቅ መሆኑን የጠቀሱት አምባሳደሩ፤ አንዳንድ አካላት በዚህ መንገድ የሚያናፍሱት ነገር እኛ ዘንድ ትክክል ነው ብለን አንወስደውም ሲሉ ገልጸዋል።

ወደረሃብ የተቀየረ ድርቅ አለመኖሩን ተናግረዋልም፤ በዚህ መልኩ እየተነገረ ያለ አባባል ስህተት መሆኑንም አስረድተዋል።

እንደ አምባሳደር ሽፈራው ገለፃ፤ ሞትን ያህል ነገር ሲከሰት "የገደለው ይህ ነገር ነው" ብሎ ለመደምደም የራሱ የሆኑ ደረጃዎች አሉት። ይሁንና ባልተገባ መንገድ ዝም ተብሎ የሚነገረው ሁኔታ የመንግሥትን ጥረት አቅልሎ ለማየት የሚደረግ ሙከራ ነው።

ስለሆነም በኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር በኩል ድርቁ ወደረሃብ አለመቀየሩንና በድርቅ ምክንያት የሞተ ሰው አለ ተብሎ የተደረሰበት መደምደሚያ አለመኖሩን መግለጽ እወዳለሁ ብለዋል።

ኮሚሽነሩ፣ ሞት ተፈጥሯዊ ጉዳይ እና ሁሌም ከማኅበረሰባችን ጋር አብሮ ያለ ነገር ቢሆንም "በዚህ ጉዳይ ነው የሞተው" በሚል ማረጋገጫ በመስጠት በእርግጠኝነት መናገር ግን እጅግ በጣም አዳጋች እንደሆነ ገልጸዋል። ስለዚህ በአንድ ቀበሌ ወይ በአንድ ድርቁ ባለበት አካባቢ ሰው ቢሞት፤ ይህን ሰው የገደለው ድርቁ ወደረሃብ ተቀይሮ ነው የሚል አይነት መደምደሚያ አግባብነት የለውም ብለዋል።

ከዚህ በኋላ ሠብዓዊ ድጋፉን በራስ አቅም ከመቻል አልፎ ትርፍ አምራች እስከመሆን ይሠራል ያሉት ኮሚሽነር ሽፈራው፣ አሁንም ለሚቸገረው ማኅበረሰብ ሠብዓዊ ድጋፍን በቅርበት ማዳረስ እና ድርቁም ይሁን ሌሎች ነገሮች ዜጎችን ወደሚጎዱበት ደረጃ እንዳይደርሱ እየተሠራ ነው ብለዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ሠብዓዊ ድጋፍን በራስ አቅም መቻል ላይ ትኩረት እንደሚደረግ ጠቅሰው፤ ይህ በአንድ በኩል የተረጂን ቁጥር ለመቀነስ የሚያስችሉ ሥራዎችን በስፋት መሥራትን እንደሚፈልግ አብራርተዋል።

ተጨማሪ ምርት በማምረትም በተለይ ከገበያ ጋር መሻማት ሳያስፈልግ የሚያስፈልገው የሠብዓዊ ድጋፍ ለሚያስፈልገው እንዲዳረስ መሥራት እንደሆነ አስረድተዋል።

ስለዚህ የሠብዓዊ ድጋፍ አቅርቦቱ ይቀጥላል ያሉት ኮሚሽነር ሽፈራው፤ ይህ በሚደረግበት ጊዜ ርዳታው ለሚገባው ብቻ እንዲሆን የማድረግ እና ሁሉም ባለድርሻ እንዲተባበር የሚደረግ ይሆናል ብለዋል።

እንደ ኮሚሽነር ሽፈራው ንግግር፤ የተወሰነ አካባቢ ላይ ድርቅ የሚያስቸግር ቢሆንም በአመዛኙ ግን ሰፋፊ ቦታዎች ላይ ትርፍ ምርትን በማምረት ከተፈጠረው ጫና መውጣት ይቻላል።

ኮሚሽኑ፣ ከትናንት በስቲያ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ በቀጣይ ለስድስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዜጎች የሠብዓዊ ድጋፍ እንደሚቀርብ መግለጹ ይታወቃል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ዲፕሎማሲ ተስፋ ያደረግናቸውን ነገዎች ማሳኪያ ትልቅ አቅም ነው!

እንደ ሀገር ከማኅበራዊ ማንነታችን የሚመነጨው የረጅም ዘመን የዲፕሎማሲ ጉዟችን ትናንት ሆነ ዛሬ በዓለም አቀፍ መድረኮች ከፍ ያለ ስፍራ አጎናጽፎናል ፤ በብዙ ተግዳሮቶች ውስጥ ሆነን ብሄራዊ ጥቅሞቻችን አስጠብቀን እንድንጓዝም ረድቶናል ።ዛሬ ላይ ለጀመርነው እና ተስፋ ሰጪ እየሆነ ለሚገኘው የለውጥ ጉዟችን ስኬት ትልቅ አቅም እየሆነንም ይገኛል ።

በመከባበር እና ሰጥቶ በመቀበል ላይ የተመሰረተው የሀገሪቱ የረጅም ዘመን የዲፕሎማሲ ታሪክና ትርክት ፤ ለሀገር እና ለሕዝብ ክብር የተገዛ ፤ ለሰብአዊነት እና ለሰብአዊ እሴቶች ቅድሚያ የሚሰጥ፤ በሀገር ሉአላዊነት እና በብሄራዊ ጥቅም ላይ መቼም እና በየትኛውም ሁኔታ የማይደራደር፤ እንደ ሀገር ካለን ማኅበራዊ ስሪታችን የተቀዳ ነው።

በዓለም ገናና ሆነን ካለፍንባቸው የደመቁ የታሪክ ምዕራፎቻችን ጀምሮ ፤ በብዙ ውጣ ውረዶች በተፈተንባቸው ዘመናት ፤ የዲፕሎማሲ መንገዳችን / መርሆዎቻችን ምንም ዓይነት መዛነፍ ሳያሳዩ ፤ በመከባበርና ሰጥቶ በመቀበል ላይ ተመስርተን ረጅም ዘመን መጓዝ እንድንችል ረድተውናል። ይህም እንደ ሀገር ከፍያለ ዓለም አቀፍ ዕውቅና እንድናገኝ አድርጎናል ።

በቀደመው ዘመን ፤ ለብሄራዊ ክብራችን ፣ ለሉአላዊነታችን እና ጥቅማችን ከፍ ያለ መስዋዕትነት በመክፈል ከማኅበራዊ ማንነታችን ለሚመነጩት የዲፕሎማሲ መርሆዎቻችን የቱን ያህል የተገዛን እንደሆነ ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በተጨባጭ ማሳየት ችለናል።

በዚህም መላው ዓለም ስለ ማኅበራዊ ማንነታችን በተሻለ መንገድ እንዲረዳ ከማድረግ አልፈን፤ ለብዙዎች ፋና ወጊ በመሆን ደምቀን የምናበራበት ትርክት ባለቤት ሆነናል። በዚህ ደማቅ ታሪክም አንገታችንን ቀና አድርገን መሄድ የምንችልበትን የስነልቦና ከፍታ መጎናጸፍ ችለናል።

በትውልዶች ቅብብል በብዙ ተግዳሮቶች እና ፈተናዎች እየተናጠ ዘመናትን በደማቅ ቀለማት አሸብርቆ ዛሬ ላይ የደረሰው ሀገራዊ የዲፕሎማሲ ጉዟችን ፤ በተግዳሮቶች እና ፈተናዎች ወቅትም ሆነ ማግስት ሀገር እንደ ሀገር ጸንታ እንድትቆም ፤ከመቆምም አልፋ መራመድ እንድትችል ስትራቴጂክ አቅም በመሆን አገልግሏል ፤ ዛሬም እያገለገለ ነው።

ወቅት የሚፈጥራቸውም ሆኑ ታሪካዊ ጠላቶቻችን ከፍ ባሉ ማንነቶች እና ማንነቶቹ በፈጠሩላቸው አቅሞች ሜዳ ሞልተው ለያዥ ለገላጋይ አንመች ባሉባቸው ወቅቶች ሳይቀር ፤ ብሄራዊ ክብራችንን ፣ ሉአላዊነታችንን እና ጥቅማችንን አስጠብቀን ለመጓዝ የመረጥነው የዲፕሎማሲ መንገድ ከብዙ ኪሳራ ታድጎን አትራፊ አድርጎናል።

ከሕዝባችን ማኅበራዊ እሴቶች የሚቀዱት የዲፕሎማሲ መርሆዎቻችን ፤ በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ የሕዝባችን የዕለት ተዕለት ህይወት አካል የመሆናቸው እውነታ ፤ ዜጎች በተፈጠረው አጋጣሚ ሁሉ ለሀገራቸው ዲፕሎማት የሚሆኑበትን የተሻለ አጋጣሚ ፈጥሯል ፤በየወቅቱ በዲፕሎማሲው ዘርፍ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን/ ፈተናዎችን አሸንፎ ለመሻገር ትልቅ ሕዝባዊ አቅም መፍጠር አስችሏል ።

ይህንን ሀገራዊ አቅም ፣ የደመቀ ትርክት ለጀመርነው የለውጥ ጉዞ ስኬት ጉልበት እንዲሆን ለማስቻል ፤ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ከፍ ባለ መነቃቃት ወደ ሥራ ተገብቷል ። መነቃቃቱ በዘርፉ ያሉትን የትናንት ተሞክሮዎችን በአግባቡ ማወቅ ፤ ዛሬን መገምገምና ነገን ብሩህ አድርጎ መጠበቅ የሚያስችል ሁለንተናዊ ዝግጁነት መፍጠር ነው።

ይህ ዝግጁነት በተለይም ለውጡ እንደ አንድ ትልቅ የታሪክ ትርክት ይዞት ሊመጣው ከሚችለው ሀገራዊ ተጠቃሚነት አንጻር ፤ ሊያጋጥሙት የሚችሉትን የተለያዩ ተግዳሮቶች /ፈተናዎች በስኬት ለመሻገር ብርቱ አቅም ሆኖ ማገልገል የሚያስችል ነው።

እኛም ሆንን የቀደሙት ትውልዶች ከፍ ባለ የሀገር ፍቅር መንፈስ ተፈጥራ ማየት የምንፈልጋትን የበለጸገች ሀገር እውን ለማድረግ ፤እንደ ሀገር ለጀመርነው በልማት ድህነትን ታሪክ የማድረግ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ስትራቴጅክ አቅም በመሆንም ያለው አስተዋጽኦ ከግምት ያለፈ ነው ።

ዲፕሎማሲ ከፈረጠመ ወታደራዊ አቅም ባልተናነሰ መጠን ትልቅ ዋጋ እያገኘ ባለበት በዚህ ዘመን ፤ በዘመናት ያካበትናቸውን የዲፕሎማሲ አቅሞች ፤ ዘመኑን በሚዋጅ የዲፕሎማሲ እውቀት ፣ ጥበብ እና ቴክኖሎጂ በመታገዝ፣ በዘርፉ ይዘነው የመጣነውን ዓለም አቀፍ ከፍታ በማስቀጠል ፤ ብሄራዊ ጥቅሞቻችንን ማስከበር የዚህ ትውልድ ዋነኛ ኃላፊነት ነው።

ትውልዱ የቀደሙት አባቶቹ በዲፕሎማቲክ ዘርፍ የነበራቸውን ዓለም አቀፍ ከፍታ በአግባቡ በማጤን ፤ ከከፍታው በስተጀርባ ያለ፤ ብሄራዊ እሴቶቻችንን በማጎልበት ፤ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የሚመጥን አዲስ የዲፕሎማሲ ትርክት መፍጠር ይጠበቅበታል። ለዚህ ደግሞ በሁሉም መልኩ ለሀገር ዲፕሎማት ሊሆን የሚያስችለውን ማንነት መገንባት ይጠበቅበታል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፦ 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሀገርን አንድ እርምጃ ወደፊት የሚያራምደው የኅብረት ሥራ ማህበራት ሪፎርም

ሶሎሞን በየነ

ኢትዮጵያ ባህር አቋርጦ ቅኝ ሊገዛት የመጣን ጠላት ከአንዴም ሁለቴ አንበርክካ ወደመጣበት በመመለስ በአፍሪካ በቅኝ ገዥዎች ጥላ ስር ያልወደቀች ብቸኛ ሀገር ናት። ይህም ያኔ በቅኝ ግዛት ስር የነበሩ የአፍሪካ ሀገሮች የኢትዮጵያን ገድል ተምሳሌት በማድረግ "ነጭ አይሸነፍም" ከሚለው የበታችነት አስተሳሰብ ወጥተው ለነጻነታቸው እንዲታገሉና ነጻ እንዲወጡ የነጻነት ችቦ ያቀጣጠለች ሀገር ናት።

ሀገሪቱ የነጻነት ፈር ቀዳጅ ከመሆኗ ባለፈ አህጉሪቱ በሁለንተናዊ አቅሟ የጎለመሰችና ተወዳዳሪ እንድትሆን እንደ የቀድሞው አፍሪካ አንድነት የአሁኑ የአፍሪካ ህብረት፣ የአፍሪካ ልማት ባንክ ...ወዘተ የመሳሰሉ የአፍሪካ ምሰሶ የሆኑ ተቋማትን ከሌሎች እህትና ወንድም የአፍሪካ ሀገራት ጋር ሁና በመመስረት ቀዳሚ ናት። ሀገሪቱ እነዚህን የመሳሰሉ ተቋማትን፣ አሠራሮችን፣ አደረጃጀቶችን ወዘተ ቀድማ በመጀመርና በማስተዋወቅ በአፍሪካ የብዙ ነገሮች ፈር ቀዳጅ ናት።

ይሁን እንጂ እንደ ቀዳሚነቷ ያላትን ልምድና ተሞክሮ በመቀመር፤ ተቋሞቿ ጊዜውን የሚመጥን ለውጦችን እየተቋቋሙ እንዲሄዱ ባለመደረጉ ብዙዎቹ ተቋማቶቿ የእድሜያቸውንና የቀዳሚነታቸውን ያህል ውጤት ሲያስመዘግቡ አይስተዋልም። ሀገሪቱ የብዙ ነገሮች ጀማሪ ወይም አስተዋዋቂ ከሚለው ስም በዘለለ እንደ ፈር ቀዳጅነቷ ውጤታማ ሆና ዜጎቿ ሲጠቀሙና በውጤቷ ሌሎች ሲጎመዡ አይስተዋልም። ይልቁንም በተቃራኒው ከሷ ልምድ ወስደው በኋላ ወደ ሥራ ከገቡ ሀገራት ጋር ስትነጻጸር በመካከላቸው የሰማይና የምድር እርቀት አለው ቢባል ማጋነን አይሆንብኝም።

ለአብነት ኢትዮጵያ ዘመናዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት በማቋቋም ከአህጉሪቱ ግንባር ቀደም ከሚባሉ ሀገራት ትጠቀሳለች። በሀገሪቱ ዘመናዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት በቅድመ አብዮት ጊዜ በ1953 ዓ.ም የገበሬዎች እርሻ ድንጋጌ በማውጣት የተጀመረ ነው ፤ በደርግ ዘመንም ሆነ ከደርግ ሥርዓት በኋላ ዓለም አቀፍ መርሆችን በማካተትና ማሻሻያ በማድረግ የኅብረት ሥራ ማህበራት ድንጋጌዎችና አዋጆች ወጥተው ተግባራዊ ለማድረግ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይቷል።

በየሥርዓቱ የነበረው የኅብረት ሥራ ማህበራት እንቅስቃሴ የተለያየ መልክ የነበረው ሲሆን፤ በየዘመናቱ የነበሩ መንግሥታት ማህበራቱን የፖለቲካ መሳሪያ አድርገው ይጠቀሙባቸው ስለነበር እድገታቸው የተቆራረጠ ነበር። ኅብረት ሥራ ማህበራቱ ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዘርፍ ልማትና እድገት በተለያየ መንገድ በርካታ አስተዋጽዖ ከማድረግ ባለፈ ህዝቡ ለሚገጥመው ችግር ቀድሞ ደራሽ ቢሆኑም፤ ተቋማቱ ውስብስብ ተግዳሮቶች ያሉባቸው ናቸው።

በዘርፉ የአስተሳሰብና አመለካከት ችግር ከመኖሩ ባሻገር አቅምን አሰባስቦ በትስስርና በቅንጅት አለመሥራት፣ የዕውቀት፣ የክህሎትና የቴክኖሎጂ ክፍተት፤ የአደረጃጀት፣ አስተዳደር፣ አሠራርና የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮች ጎልተው ይታያሉ። እንዲሁም የሀብት ብክነት፣ የአባላት ተጠቃሚነት አለመረጋገጥና እምነት ማጣት፣ አማራጭ የፋይናንስ አቅርቦት አለመኖር ከፖሊሲ የትኩረትና የሕግ ማዕቀፍ ጋር ተዳምሮ ማህበራቱ በቁጥራቸው እንዲሁም በዕድሜያቸው ልክ የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዳይወጡ እንዳደረጋቸው የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ።

ትናንት ሀገሪቱ በነበራት የኅብረት ሥራ ማህበራት የአመራር፣ የአባላት፣ የባለሙያ ወዘተ ማሰልጠኛ ተቋም ውስጥ ሰልጥነው ወደ ዘርፉ በመግባት ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ እዚሁ አፍንጫችን ስር ጎረቤት ሀገር ኬኒያን ለዋቢነት እንውሰድ። ከቅኝ ግዛት ከወጣች በኋላ በደርግ ዘመነ መንግሥት ከኢትዮጵያ ልምድ ቀስማ ወደ ዘርፉ የገባችው ኬንያ፤ አምስት ሺህ የህብረት ሥራ ማህበታርን ብቻ ይዛ፤ ዛሬ ላይ በዘርፉ ከሰባት ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ዜጎቿ የሥራ እድል ፈጥራለች።

በኬንያ ማህበራቱ 800 ቢሊዮን ዶላር ካፒታል የፈጠሩ ሲሆን፤ ከሀገሪቱ ብሔራዊ የገንዘብ ክምችት ውስጥ 31 በመቶ ድርሻው የህብረት ሥራ ማህበራቱ ነው። ለሀገሪቱ ነፍስ ወከፍ ምርት 47 በመቶ ገደማ ድርሻ አላቸው። በተጨማሪም በኬኒያ በከተሞች ከተገነቡ 10 ቤቶች ውስጥ ዘጠኙ በሕብረት ሥራ ማህበራት የተገነቡ ናቸው። ይህም በከተሞች የመኖሪያ ቤትን ችግር በማቃለል ረገድ 90 በመቶ ድርሻ ይወጣሉ ማለት ነው። ማህበራቱ 63 በመቶ ለሆነው ህዝብ ተደራሽ ናቸው።

በቤት፣ በባንክ ወዘተ ዘርፎች እንደ ኢኮሜርስ የመሳሰሉ የፋይናንስ አሠራሮችን በማስተዋወቅ የፈጠራና የምርምር ማዕከል ጭምር ናቸው።በተለይ ማህበራቱ የኑሮ ውድነትንና የዋጋ ግሽበትን ከማረጋጋት አኳያ የሚወጡት ሚና አይተኬ ነው። በኬንያ ነጋዴዎች እንደኛ ሀገር ከነበረው ዋጋ በእጥፍ መጨመር ይቅርና የአንድ ሳንቲም የዋጋ ጭማሪ ማድረግ አይችሉም።

ምክንያቱም ህብረት ሥራ ማህበራቱ ከፍተኛውን ምርት ስለሚሸፍኑ፣ የጎደለውን ስለሚሞሉ እንዲሁም ምርቱ ጠፋ እንኳን ቢባል ከዓለም ገበያ ጭምር ገዝተው ስለሚያቀርቡ የገበያ ዋጋ በነሱ መዳፍ ቁጥጥር ውስጥ ነው። በተመሳሳይ ወደ ሀገራችን ኢትዮጵያ ስንመጣ በህዝብ ቁጥር፣ በነፍስ ወከፍ ምርት፣ በእድገት፣ በማህበራት ብዛት ወዘተ እንበልጣለን።

በዘርፉ ያስመዘገብነው ውጤት ከኛ ልምድ ቀስማ በኋላ ወደ ሥራ ከገባችው ኬኒያ ጋር ስናወዳድረው ልዩነቱ የትየ ለሌ ነው። በኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ከ110 ሺህ በላይ መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ያሉ ሲሆን፤ ይህም ኬኒያን በ105 ሺህ ማህበራት እንበልጣታላን ማለት ነው።

ይሁን እንጂ በሀገሪቱ ያሉ ማህበራት የካፒታል መጠናቸው አንድ ቢሊዮን ዶላር ነው። ማህበራቱ የፈጠሩት የሥራ እድል ደግሞ ከአንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን አልተሻገረም። እንዲሁ የገበያ ድርሻቸው ዝቅተኛ ነው። ዋጋን ከማረጋገት አኳያ እየተወጡት ያለው ሚና የሚጠበቅባቸውን ያህል አይደለም።

ከዚህ አንጻር የጎረቤት ሀገር ኬኒያን እና የተሻለ ተሞክሮ ያላቸው የተለያዩ ሀገራትን ልምድ በመቀመር በዘርፉ የሚስተዋሉ የአደረጃጀት፣ የአሠራር፣ የመለካከት፣ የሕግ ክፍተቶችን በመሙላትና በማስተካከል ማህበራቱ እንደ እድሜያቸውና ቁጥራቸው የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲወጡ ጥልቅ የኅብረት ሥራ ማህበራት ልማትና እድገት ሪፎርም ንቅናቄ ተጀምሯል።

በኅብረት ሥራ ማኅበራት የሪፎርም ንቅናቄ አስፈላጊነትና አተገባበር ላይ ያተኮረ የባለድርሻ አካላት የምክክር መድረክ ከሰሞኑ በአዳማ ከተማ ተካሂዷል። በመድረኩ የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጌታቸው መለሰ (ዶ/ር) እንደገለጹት፣ ሪፎርሙ የተቀናጀ ሁለንተናዊ ሪፎርም በመሆኑ ሁሉንም የእሴት ሰንሰለት እና የባለድርሻ አካላት ሚና ያካተተ ነው።

የሪፎርም ሥራው ማኅበራቱ ሊግ እንዲመሠርቱ፣ የቁጠባና የብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት እንዲሁም ባንክ እንዲያቋቁሙ ያስችላል። ምርትና አገልግሎታቸውን ዓለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ በጥራትና በብዛት እንዲያቀርቡ ይረዳቸዋል። በተጨማሪም የኅብረት ሥራ ማህበራት የፖሊሲ ማዕቀፍ በመንደፍና የሕግ ማዕቀፍ በማሻሻል ጠንካራ አደረጃጀት፣ አስተዳደር ... እንዲኖራቸውና የኦዲት፣ የኢንስፔክሽን፣ የብቃትና ዕውቅና አሰጣጥ በተሟላ ፖሊሲ ማዕቀፍና አሠራር ሥርዓት እንዲተገበር ይሠራል።

እነዚህ ቁልፍ የሪፎርም ተግባራት ተፈጻሚ ሲሆኑ ዘመናዊ አደረጃጀት ያላቸው፣ በሰለጠነ የሰው ሃይል የሚመሩና በቴክኖሎጂ የታገዘ ጥራት ያለው ምርትና አገልግሎት የሚሰጡ ማህበራት እንደሚፈጠሩ አመላክተዋል። በመሆኑም ዓለም አቀፍ ዓውዱ ካለበት አሁናዊ ሁኔታ እና ከሀገራዊ የፖሊሲ ለውጥ አንጻር ተወዳዳሪ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ለመፍጠር በዘርፉ ሁለንተናዊ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል የሪፎርም ንቅናቄ ለማድረግ ወደ ሥራ መገባቱ ዘመኑን የዋጀ ነው።

ይህም ሆኖ ግን ሰው ተኮር የሆኑ የህብረት ሥራ ማህበራት ያሉባቸው ማነቆዎች ተፈትተው የሰፊውን ማህበረሰብ በልቶ የማደርና የመልማት ጥያቄዎች እንዲመልሱና የሀገሪቱን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ገበያ በማረጋጋት ረገድ የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲወጡ መንግሥት፣ የግሉ ዘርፍ፣ ማህበራቱና የማህበራቱ አባላት እንዲሁም ሰፊው ህዝብ የበኩሉን ሚና ሊጫወት ይገባል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

## የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ሳምንት

**ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽክታብ)**

‹ከአፍሪካ መዲናነት እስከ ዓለም መድረክ› በሚል መሪ ሀሳብ ከጥር 2 ቀን 2016 ዓ.ም እስከ ጥር 24 ድረስ በሳይንስ ሙዚየም የተዘጋጀው የኢትዮጵያ የዲፕሊማሲ ሳምንት ኢግዚቢሽን ሀገራችንን ለውጪው ማህበረሰብ ከመግለጥና ቀጣይ የተግባቦት አቅጣጫዎችን ከመትለም አኳያ ላቅ ያለ ፋይዳ ያለው ነው።

ለሀያ ሁለት ቀናት ያክል ክፍት ሆኖ የሚቆየው አውደ ርዕይ በዲፕሎማሲው ዘርፍ ሶስት አንኳር አላማዎችን እንዳነገበ ይነገራል። የመጀመሪያው ላለፉት በርካታ ዓመታት ያለፍንበትን የግንኙነት ሂደት የሚቃኝ ነው። ይሄ ማለት ከየት ተነስተን የት እንደደረስን፣ ባለፈው ጊዜ በነበረን የውጪ ሀገራት ግንኙነት ያተረፍነውን እንደ ውጤት የሚቀበል ኪሳራችንን ደግሞ እንደተግዳሮት የሚያጤን ነው። በመቀጠል አሁን ያለንበትን የዲፕሎማሲ ሂደት የሚገመግም ሆኖ እናገኘዋለን።

ሁለተኛው በአሁኑ ወቅት ከውጪ ሀገራት ጋር ያለን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ግንኙነት ምን እንደሚመስል፣ ትርፍና ኪሳራውን የምንገመግምበት ነው። ሶስተኛው ፤መጪውን በመቃኘት የምንደርስበትን የሚመለከት ነው። እኚህ የትናንት የዛሬና የነገ የዲፕሎማሲ ሂደቶች አሁን ባለችውና ወደፊት በምትፈጠረው ሀገራችን ላይ ያለውን አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖ በአንክሮ እንድናይ እድል የሚሰጥ አውደ ርዕይ ነው።

የዲፕሎማሲ ሳምንቱ የሀገሪቱን ቀጣናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የስኬት አቅጣጫ በማሳየት ብርቱ ፋይዳ እንደሚኖረው ይታመናል። በተግባቦቱ ዘርፍ የነበረንንና ያለንን ወደፊትም የሚኖረንን የሰጥቶ መቀበል ጉርብትና ጨምሮ ካለፈው መማርን በማካተት አዲስ ንቃትን እንደሚፈጥር ሰሞኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሳምንቱን አስመልክቶ በሰጠው መግለጫ ጠቁሟል።

የነበሩ ስኬቶችን እና ተግዳሮቶችን ነቅሶ በማውጣት ለቀጣዩ ግስጋሴ መንገድ የሚጠርግ እንደሚሆንም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዴኤታ አምባሳደር ቡርቱካን አያኖ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት ቃለ መጠይቅ አረጋግጠዋል። የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ከራሷ አልፎ ለጥቁር ህዝቦች ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክቷል› ያሉት ደግሞ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ናቸው።

ኢትዮጵያ በዓለም አደባባይ ስሟን በወርቅ ቀለም ከጻፈችባቸው አጋጣሚዎች ውስጥ የዲፕሎማሲው ዘርፍ አንዱ ነው። ከራሳችን አልፈን ለሌሎች በተረፈ የተግባቦት ሂደት ውስጥ አልፈን ሀገር እንዳጸናን ብዙ መረጃዎች አሉ። ከነበረን የመደማመጥ ልምድና የሉአላዊነት መሻት ለመላው ጥቁር ህዝብ የነጻነት ችቦን ያበራን፣ አለም ባልሰለጠነችበት ዘመን በዲፕሎማሲው ወንዝ ተሻግረን ከሀያላኖች ጋር ለተግባቦት የተቀመጥን መሆናችን ለየትኛውም ማህበረሰብ የሚተረክ ጉዳይ አይደለም። ይሄ ስም ዛሬም ቀጥሎ ለትላልቅ ዓለም አቀፍ እድሎች መልስ ሲሰጥ እያየን ነው።

በስልጣኔና ቀድሞ በመንቃት ከአፍሪካ አልፎ ዓለምን ያነቃ የዝማኔና የእውቀት ባላባቶች ነበርን። ለዚህ ምስክር የሚሆኑን ከምሥራቅ አፍሪካ ኢጋድን፣ ከአፍሪካ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን፣ ከዓለም ደግሞ ሌግ ኦፍ ኔሽንን ጨምሮ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን መስራች አባል ሀገራት መሆናችን ነው። የቅርብ ጊዜዎቹን እናስታውስ ካልን ደግሞ እንደብሪክስ ያሉ በጎ አጋጣሚዎችን መጥቀስ እንችላለን፡

እነዚህ ወንዝ ተሻጋሪ እድሎች በሌላ በምንም የመጡ ሳይሆኑ ከሌላው ዓለም ጋር በነበረን የመነጋገርና የመወዳጀት ከፍ ሲልም አብሮ የማደግ ተሳትፎ የመጡ ናቸው። የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ሳምንትም ይሄን እውነታ የሚዘክር፣ እውቅና የሚሰጥና የሚያበረታታ መድረክ ነው።

ከአፍሪካም ሆነ ከዓለም ግንባር ቀደም ገናና ስም ይዘን በነጻነትና በሉአላዊነት የምንጠራው ለመነጋገር ባለን ልምድና ይሁንታ መሆኑ ብዙም አጠያያቂ አይሆንም። የኢትዮጵያን የዲፕሎማሲ ታሪክ ስናጠና ብዙ ዓመታትን ወደ ኋላ መሄድ ግድ ይለናል። ይሄ የታሪክ ትርክት በበጎ የምንነሳበት አንዱ ገድላችን ነው።

**በስልጣኔና ቀድሞ በመንቃት ከአፍሪካ አልፎ ዓለምን ያነቃ የዝማኔና የእውቀት ባላባቶች ነበርን። ለዚህ ምስክር የሚሆኑን ከምሥራቅ አፍሪካ ኢጋድን፣ ከአፍሪካ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን፣ ከዓለም ደግሞ ሌግ ኦፍ ኔሽንን ጨምሮ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን መስራች አባል ሀገራት መሆናችን ነው**

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከተመሰረተ ጀምሮ ባሉት ጊዜአት ውስጥ እንኳን መቶ አስራ ስድስት (116) ስኬታማ የዲፕሎማሲ ዓመታትን አሳልፈናል። ይህ ትልቅ ስኬት ነው። ይህን ያህል ዓመት ውጤታማ የሆነ ዲፕሎማሲን መከወንና ከዓለም ሀገራት ጋር ሁለንታዊ ወዳጅነትን የፈጠረ ሀገር ማግኘት ቀላል አይደለም። ባለፉት አመታት በውጤታማነት የመጣንባቸው ቀጣናዊ፣ አፍሪካዊና ዓለም አቀፋዊ የዲፕሎማሲ ሂደቶች ከእድልና ድላቸው በተጨማሪ ኢትዮጵያዊ ማንነትን የሚናገሩ ሀገራዊ በጎ አሻራዎች ናቸው።

እነዚህ ሂደቶች እንደሀገር የጨመሩልን መልካም ስም እንዳለ ሆኖ በተጨማሪም የአፍሪካ ቁንጮ አድርገውን ሰንብተዋል። የአየር ንብረት ለውጥን በተመለከተ፣ አፍሪካዊ ችግሮች ላይ ያተኮሩ ወዘተ የመሳሰሉ አፍሪካን ወክለን በዓለም አቀፍ መድረክ ላይ የተሳተፍንባቸው ታላላቅ ኃላፊነቶች የዚህ ዲፕሎማሲ ውጤት አንዱ ማሳያ ነው።

በአፍሪካ ደረጃም በርካታ አዳዲስ ለውጦችን ማንሳት ይቻላል። በጸጥታው ምክር ቤት አፍሪካ ተወካይ እንዲኖራት ለአፍሪካውያን ድምጽ በመሆን እስከመሟገት የደረሰ፣ ለምንም ነገር ሀያላኑን ደጅ የምንጠናበትን ልምድ ያስቀረ ‹ለአፍሪካ ችግር አፍሪካዊ መፍትሄ› በሚል አዲስ እና ተራማጅ አስተሳሰብ አዲስ ትውልድና አዲስ አህጉር የፈጠርንበት ክስተት ማንሳት ይቻላል። አስታራቂና ሽምጋይ ሆነን የገባንባቸው አፍሪካዊና ዓለም አቀፋዊ መድረኮች ከዚህ ጎን የሚጠቀሱ የተሰሚነት ድሎቻችን ናቸው።

የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ሳምንት እንደስሙ ስለኢትዮጵያ የሚወራበት የሚነገርበትና የሚሰማበት ሳምንት ነው። አሳታፊና መረጃ ሰጪ መሆኑ ደግሞ ለየት ያደርገዋል። የተለያዩ ምሁራንን፣ አምባሳደሮች፣ ዲፕሎማቶች እና ጥሪ የተደረገላቸውን የሁለተኛ ትውልድ ትውልደ ኢትዮጵያውያንን የጋበዘው መድረኩ በእውቀትና በመረጃ በሳይንሳዊ ትንታኔም ዳብሮ ቀጣይ ሂደቶችን እንደሚያስተካክል ይጠበቃል። አውደ ርእዩ ከወሬ ባለፈ ግልጽና ተጨባጭ በሆነ መልኩ እውነታውን ለሕዝብም ሆነ ለመላው ዓለም ከማስረዳት አኳያ የማይናቅ ሚና ይኖረዋል።

እንደሀገር በዲፕሎማሲው ዘርፍ መልስ የሚፈልጉ ትላልቅ ጉዳዮች አሉን። በቀጣይም ለሰነቅናቸውና ልንደርስባቸው ላቀድናቸው ግቦች በእውቀትና ልምድ የተደገፈ መሰል የግንኙነት መርሆች ያስፈልጉናል።

ይሄ እንዲሆን እንደ ‹የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ሳምንት› ን የመሳሰሉ አስተማሪና አወያይ፣ አንቂና አበረታች መድረኮች ያስፈልጉናል። ሕዝብን ከመንግሥት ጋር መንግሥትንም ከሕዝብ ጋር የሚያቆራኙ ውህደት ፈጣሪ መድረኮች ለቀጣይ ስኬቶቻችን የአንበሳውን ድርሻ ወሳኝ ናቸው።

እንዳሳለፍነው ረጅም እና ታሪካዊ የዲፕሎማሲ ጉዞ በዚህ ረገድ ብዙ ተሰርቷል ለማለት አያስደፍርም። ይሄ እንደድክመት ተወስዶ በቀጣይ እርማት የሚወሰድበት የቤት ስራችን ነው። በሀገራት የእርስ በእርስ ጉርብትና መቶ ዓመታትን የተሻገረ ሀገር እንደብሄራዊ ድል ታሪኩን ሊዘክርና ሊያከብር ይገባል። አልተጠቀምንበትም እንጂ ኢትዮጵያን ከሚገልጡና ከሚያስተዋውቁ ታሪክ ነጋሪ ሁነቶች ውስጥ የዲፕሎማሲ ታሪካችን አንዱ መሆን የሚችል ነበር።

ውጤታማ ዲፕሎማሲን መተግበር ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ብልጽግና የጀርባ አጥንት ነው። በዲፕሎማሲ ያልበረታና ያልጎበዘ ሀገር በምንም ሊበረታ አይችልም። አሸናፊ ሆኖ መውጣት አይቻልም። እኛ ደግሞ ከመበርታትም አልፈን ማንም በሌለው የረጅም ታሪክ ውስጥ የምንጠራ አሸናፊዎች ነን።

ስልጣኔ ካልነበረበት ከዛ የደብዳቤና የመልዕክተኛ ዘመን ጀምሮ ሀገራችን ከውጪው ማህበረሰብ ጋር ስለሰላም፣ ስለልማት፣ ስለፖለቲካ፣ ስለግዛት አንድነት፣ ስለሉአላዊነት ትመክር ነበር። ይሄ ገናና ተግባርን ስምና ዛሬ ላይ ተሀድሶ አቅጣጫዎቻችንን ጠራጊ እንዲሆን ማድረግ የእኛ ፈንታ ነው።

‹የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ሳምንት› ለዚህ እውነታ መልስ ሰጪ ነው። አውደ ርዕዩም መጪውን የሚያስቃኝ ከምንም በላይ ደግሞ ለቀጣይ ሂደቶቻችን አጽንኦት የሚሰጥ ነው። ከአዲስ ግንኙነት አኳያ የነበሩብንን አስተካክለን በአዲስ ሀይል እንድንነሳ ሙያዊ እገዛ የሚሰጠን ነው። ቀጣይነት ቢኖረውና በአፍሪካና በዓለም ሀገራት ዘንድ የነበረንን የእርስ በርስ ግንኙነት እንደምስክር ተጠቅመን ለቀጣይ ድሎቻችን እንደመወጣጫ ብንጠቀመው የተሻለ እድልን የሚፈጥር ነው።

‹ከአፍሪካ መዲናነት እስከ ዓለም መድረክ› የሚለው መሪ ሃሳብ ካሳለፍነው የዲፕሎማሲ ሂደት አንጻር በትክክልም ኢትዮጵያን የሚመጥን ሃሳብ ነው። ከአፍሪካ ተነስተን ዓለም አቀፋዊነትን የዋጀንበት የእርስ በርስ ግንኙነት አለን። እኚህ ታሪካዊ እርምጃዎቻችን እንደሀገር ዛሬ ላይ ለተፈጠሩብን ጫናዎችና መድሎዎች ምናልባትም እንደመፍትሄ ሆነው ሊጠቅሙን የሚችሉ ናቸው።

የታላቁ ህዳሴ ግድብ ለአስር ለራቀ ዓመታት በብዙ የዲፕሎማሲ ሂደት ውስጥ ያለፈ ነው። ሰሞነኛው የባህር በር ጥያቄና መልስም የውጤታማ ዲፕሎማሲ አንዱ ማሳያ ነው። ይህን ስምምነቱን ተከትሎ በአንዳንድ ሀገራት ዘንድ የተፈጠሩ ብዥታዎችም በተመሳሳይ በዲፕሎማሲያዊ አካሄድ እንደሚጠሩ እርግጥ ነው።

ዲፕሎማሲ የሚለውን ቃል በአንድ ሌላ ቃል ብንተካው ‹ሰላማዊ ግንኙነት› የሚል ሆኖ እናገኛዋለን። የቃሉ ትርጓሜ በየትኛውም ሀገራዊ አውድ ውስጥ ጣልቃ የሚገባ ነው። ያለሰላማዊ ግንኙነት ልማትና እድገት የማይታሰብ ነው። ፖለቲካና ኢኮኖሚ፣ ሉአላዊነትና ራስገዝነት ዋጋ አይኖራቸውም። በአጠቃላይ ከህልውና ጉዳይ ጋር አስተሳስረን ልናየው የሚገባ እውነታ ነው። ዓለም ወደ አንድ መንደር እየመጣች ባለችበት በዚህ ዘመን አይደለም በቀደመው ዘመን የዲፕሎማሲ ዋጋ ምን ያክል እንደነበር አይተናል።

ከዚህ በመነሳት ለጉዳዩ አጽንኦት ሰጥተን ወደፊት መንቀሳቀሱ ዋጋ ያለው ይሆናል። ለጀመርናቸውም ሆኑ ወደፊት ለምንጀምራቸው ድህነት ማለፊያ የትንሳኤ ትልሞች ‹ከሌላው ጋር እንዴት መኖር እና እንዴት መወዳጀት› የሚሉት ጽንሰ ሀሳቦች ገዢ ሀቆች ሆነው ከፊት ይመጣሉ። በዚህ ረገድ የተሳካልን ሕዝቦች ነን። እድሎቻችንን ግን ከዚህም በላይ ልንጠቀምባቸው ይገባል።

አንድ ሀገር ከሌላው ዓለም ጋር ከምትተሳሰርበትና ጥቅሟን ከምታስከብርባቸው መንገዶች ውስጥ ቀዳሚው የዲፕሎማሲ አካሄድ ነው ስንል ራሱን የቻለ ህግና ሥርዓት አለው እያልን ነው። ይህ ህግና ሥርዓት ነው የራስ ጥቅምን ሳያስነኩ ሰጥቶ መቀበል የሚለውን መርህ እውነት የሚያደርገው። ጥቅምን በማስነካት ውስጥ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የለም። እስከዛሬ ጥቅማችንን አላስነካንም ወደፊትም አናስነካም።

ዲፕሎማሲያዊ ወዳጅነት ራስን ለሌሎች መግለጥና ሌሎችን ወደ ራስ ማቅረብ ከሚለው አገላለጽ ጋር ተጣጥሞ መሄድ የሚችል ነው። በዚህ ረገድ ሀገራችን ኢትዮጵያ እድለኛ ሀገር ናት ማለት ይቻላል። ዘመናትን ያስቆጠረ የመልካም ተግባቦት ስም ባለቤት ናት። ከአፍሪካ ቀድማ ከዓለም ሀገራት ጋር በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የተሳካለት ግንኙነት አድርጋለች። በሌሎች ዘርፎች ላይም ወዳጅነትን በመፍጠር ሰላም መር በሆነ እንቅስቃሴ ራሷን ጠቅማ ሌሎችን ስትጠቅም የኖረችበትን መቶ ዓመታትን ያስቆጠረ የዲፕሎማሲ ዝማኔ ማንሳት ይቻላል።

የአሁኑ የዲፕሎማሲ ሳምንትም የሄድንበትን ረጅም የተግባቦት ሂደት የሚያስቃኝ ቀጣይ አቅጣጫዎቻችንንም የሚጠቁም የኢትዮጵያ የንቃትና የብርታት ጉባኤ ነው ማለት ይቻላል። ከዚህ ውጪ በእንዴትም ብንገልጸው አቻ ትርጉም አናገኝለትም።

የነበሩንን ማስታወስ ያሉንን አጥብቀን እንድንይዝ እድል የሚሰጠን ነው። የነበሩንን መግለጥና ለተቀረው ዓለም ማሳየት ቀጣይ ተግዳሮቶቻችንን የሚቀንስ ለትውልዱም ተስፋን የሚሰጥ አካሄድ ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ሳምንት በብዙ ረገድ ዋጋ ያለው እንደሆነ መመስከር ይቻላል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሰል ሀገራዊ ዳናዎችን የሚገልጡ፣ ገጽታ የሚገነቡ የሩቅና የቅርብ ሁነቶችን ወደ ሕዝብ የሚያቀርብበትን መድረክ በቀጣይም ይበልጥ አጠናክሮ ሊቀጥልበት ይገባል።

አሁን ላይም ትጋታችንን ለሀገራችን አውለን፣ ክፍተቶቻችንን በመሙላት በዳግም በጎ ስም ታሪክ የምናድስበት ጊዜ ላይ እንገኛለን። መጪው ጊዜም በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚው፣ በሰላም ፈጣሪነትና በልምድ ልውውጥ ዘርፍ በዲፕሎማሲው ልቀን ሀገራችንን ከነበረችበት እንፋቅቅ የምናራምድበት እንዲሆን ትጋት ያስፈልገዋል።

# ወቅታዊ

# “የገበታ ፕሮጀክቶች የግሉን ዘርፍ በማነቃቃት በርካቶች ወደ ቱሪዝም ኢንቨስትመንት እንዲገቡ እያስቻሉ ነው”

*- የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ*



**የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ በወቅታዊ ነባራዊ የቱሪዝም ዘርፉ እንቅስቃሴ ላይ ከመገናኛ ብዙኃን ጋር ያደረጉትን ቃለ ምልልስ ሙሉቃል**

**ጥያቄ፡- በሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው በዋነኝነት ትኩረት ከተሰጣቸው አምስት የምጣኔ ሀብቱ ዘርፎች መካከል የቱሪዝም ዘርፉ አንዱ ነው ። በአስር ዓመቱ መሪ የልማት እቅድም ትኩረት የተሰጠው ዘርፍ ነው። እቅዱ ስመተግበር ወደ ሥራ ከተገባበት በ2013 ዓ.ም ጀምሮ ኮቪድ 19 ጨምሮ በሰሜኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተፈጠሩ ግጭቶች ለዘርፉ ፈተና ሆነዋል ። ዘርፉ እነዚህን ፈተናዎች አልፎ አሁን ያለበት ደረጃ ምን ይመስላል?**

**አምባሳደር ናሲሴ ፡-** እንደሚታወቀው በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርሙ ልማታችንን እና እድገታችንን ያፋጥናሉ ተብለው ታሳቢ ከተደረጉ ዘርፎች አንዱ ቱሪዝም ነው። ይህንንም ስናደርግ በምክንያት ነው። አንዱ ምክንያት ያለንን ሃብት ታሳቢ በማድረግ ነው፣ ያለንን የተፈጥሮ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ሀብት ለቱሪዝም በጣም የተመቻቸ በመሆኑ ነው።

ሁለተኛው ታሳቢ የተደረገው ያለንበት ጂኦግራፊካል አቀማመጥ / ሎኬሽን ነው። እንደሚታወቀው ያለነው በጣም ስትራቴጂክ ቦታ ላይ ነው። ለብዙ ሀገራት ቅርብ ነን፤ ይህ ብቻ አይደለም፤ ለምሳሌ አውሮፓን ብንወሰድ ዋና ገበያችን ነው፤ ለአውሮፓ ቅርብ ነን። መካከለኛው ምሥራቅንም ብንወስድ ትልቅ ገበያ እየሆነ ያለ ስፍራ ነው። የአፍሪካ ሀገሮችን ጨምሮ ለሌሎች ሀገሮችም ቅርብ ነን፤

ከዚህ በተጨማሪ ለቱሪዝም ከሚያስፈልጉ አንዱ ዓለም አቀፍ በረራ የመኖሩ ጉዳይ ነው ። ለዚህ ደግሞ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከ120 ሀገራት በላይ ይበራል። ይህም ለእኛ በጣም ጥሩ ሁኔታን ይፈጥራል። ስለዚህ ታሳቢ የተደረጉ ብዙ ጉዳዮች አሉ ማለት ነው።

ከዚህ በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ደረጃ ወደ አፍሪካ የሚመጣው የቱሪዝም ፍሰት እያደገ ይሄዳል የሚል እሳቤ አለ። የሚቀጥሉትን ዓመታት ካየን እስከ 2050 ዓ.ም ባሉት ዓመታት ቱሪስቶች ወደ አፍሪካ የሚያደርጉት ፍሰት ከሌሎች በበለጠ እያደገ ይሄዳል። እነዚህ ነገሮች ሁሉ ታሳቢ ተደርገው ነው እቅዱ የወጣው።

እቅዱ በጣም ሰፊና ትልቅ እንደመሆኑ ያንን ለማሳካት ደግሞ በተለይ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት በጣም ብዙ ሥራ ያስፈልጋል። እንደተባለው ደግሞ አስቀድሞ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ተከስቶ ነበር፤ ከዚያም ደግሞ የሰላምና ፀጥታ ሁኔታ በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ፤የሰሜኑን ጦርነት ጨምሮ ለዘርፍ ተግዳሮት ነበር። ያንን ተከትሎ የተለያዩ የጉዞ ክልከላዎችና የመሳሰሉት ሁኔታ ተፈጥረው ስለነበር የመጀመሪያዎቹ ዓመታት በጣም ብዙ ፈተናዎች የነበሩባቸው ነበሩ።

ነገር ግን ለእነዚህ ፈተናዎች አልተንበረከክንም። በጣም ብዙ ስራዎች ተሰርተዋል። ምንም እንኳን ብዙ ተግዳሮቶች የነበረበት ጊዜ ቢሆንም፤ችግሮቹ ዓለምአቀፍ የቱሪስት ፍሰቱ ላይ ተፅዕኖ ያሳረፉ ቢሆኑም ፤ በጣም ብዙ የቤት ስራዎች ስለነበሩን እነሱ ላይ ትኩረት ለማድረግ ተሞክሯል። እንደ ሀገር ካሉን የቤት ስራዎች መካከል የመዳረሻ ልማት ስራዎች ይጠቀሳሉ።

በጣም ብዙ መስህቦች አሉን። ታሪካዊ ሀብታችን ብዙ ነው። የብዝሀ ባህል መገለጫዎች ነን። በተለያዩ ኮርነሮች የተለያዩ ትልልቅ ፌስቲቫሎች ሊሆኑ የሚችሉ ሃይማኖታዊ ሆኑ ባህላዊ ኩነቶች አሉን። ከዛም ባለፈ የተፈጥሮ፣ የመልክአ ምድር፣ የአየር ፀባይ ውበት አለን፤ ለቱሪዝም ዘርፍ የአየር ፀባይ በጣም አስፈላጊ ነው።

በዱር እንስሳትም በተለያየ መልኩ በተፈጥሮ የታደልናቸው ሀብቶች ብዙ ናቸው። ነገር ግን እነዚህ ብዙ ጉድለቶች አሉባቸው። ብዙዎቹ መስህብ ናቸው እንጂ መዳረሻ አልሆኑም።በመስህብና በመዳረሻ መካከል ልዩነቱ ምንድነው ከተባለ መስህቡ አለ ነገር ግን መደረሻ ለማድረግ ግን የተለያዩ መሰረተ ልማቶች ማሟላት ይጠበቃል።

መሰረተ ልማቶች ብቻ ሳይሆኑ ደግሞ ከመሰረተ ልማትም ባለፈ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ማሟላትን ግድ ይላል። የተወሰኑ ምሳሌዎችን ለማንሳት እሞክራለሁ፤ በቅርቡ የተከፈተውን የጨበራ ጩርጩራ የዝሆን ዳና ሎጅን ብናይ የጨበራ ጩርጩራ ፓርክ እዛው ነበረ፤ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን መጥተው ስሙን እስከንሰማ ድረስ ብዙዎቻችን ስለፓርኩ አናውቅም፤ ብዙዎቻችን ስለፓርኩም አልሰማንም።

የመጀመሪያውን ጉዞ ያደረጉት ሰዎች እንደሚገልፁት፤ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችንን ጨምሮ መሄጃ መንገድ እንኳ ስላልነበረ በጣም ዳገት ቧጦ በእግር በጣም በአስቸጋሪ ሁኔታ ነበር ማየት የተቻለው። በአጠቃላይ ተደራሽ አልነበረም ማለት ነው። ስለዚህ መስህቡ አለ ነገር ግን መዳረሻ መሆን አይችልም።

ቱሪስቶች ሄደው እዛ ለመድረስ መሄጃ መንገድ የላቸውም፤ ከደረሱም በኋላ ደግሞ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ፣ የሚያርፉበት፤ ቡና የሚጠጡበት የተለያዩ አገልግሎቶችን የሚሰጥ አካል የለም። ስለዚህ አንዱ የነበረን ትልቅ ክፍተት የቱሪስት መሰረተ ልማትና የቱሪስት መዳረሻ አለመኖር ነበር። በእነዚህ ዓመታት በተለያየ መልኩ የመዳረሻ ልማት ስራዎች በሰፊው ተሰርተዋል።

ለእዚህም የክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችንን የገበታ ለሸገር ፕሮጀክቶች መጥቀስ ይቻላል። ከዛም ቀጥሎ ገበታ ለሀገርን ማንሳት ይቻላል። አሁን ደግሞ ወደ ገበታ ለትውልድ እየገባን ነው። በገበታ ፕሮጀክቶች የተለያዩ የመዳረሻ ልማት ፕሮጀክቶች ተሰርተዋል ፤ ይህም ደግሞ የግሉን ዘርፍ አነቃቅቶ በርካቶች ወደ ቱሪዝም ኢንቨስትመንት የገቡበት ሁኔታ ታይቷል። አንዱ የቤት ስራችን እሱ ስለነበረ እሱን ስንሰራ ቆይተናል።

ሁለተኛው የቤት ስራችን ዓለም አቀፍ ቱሪዝምን ለማሳደግ የሀገር ውስጥ ቱሪዝም እድገት በጣም ያስፈልጋል። ምክንያቱም የሀገር ውስጥ ቱሪዝም አንደኛ ለመሰረተ ልማትና ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት መስፋፋት በር ይከፍታል። ሁለተኛ የማስተዋወቅ እድልንም ይጨምራል። ምክንያቱም እየመጣ የሚጠቀም ሁሉ በሶሻል ሚዲያ ፖስት ሲያደርግና በተለያየ መልኩ ስያስተዋውቅ መዳረሻዎች የበለጠ እየተዋወቁ ይሄዳሉ።

ሶስተኛ ደግሞ የዓለም አቀፍ ቱሪዝም ገበያ ሲቀዛቀዝ የሀገር ውስጥ ቱሪዝም እንቅስቃሴ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማቶቻችን እንዳይጠፉ እንዳይከስሙ፣ የተፈጠሩ የሥራ እድሎች እንዲቀጥሉ ያስችላልና በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የሰራነው የቤት ሥራ የሀገር ውስጥ ቱሪዝም ንቅናቄን ማስጀመር እና እሱ እንዲቀጥል ማድረግ ነው።

አራተኛው የቤት ስራችን የማስተዋወቅና የኢትዮጵያን ገፅታ የመገንባት ሥራ ነው። ከዚህ አንፃር ምንም እንኳ ያው ጦርነት ውስጥ የነበርንም ቢሆንም፣ ምንም እንኳን ተግዳሮቶች የነበሩበት ወቅት ቢሆንም፣ በተለያየ መልኩ ወደ ሀገራችን የሚመጣ የቱሪስት ፍሰት እንዳይቀዛቀዝ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። ከተደረጉ ጥረቶች መካከል በተለያየ ዙር በውጭ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ለትውልደ ኢትዮጵያን የተደረጉ ጥሪዎች ናቸው ።

በዚህም በጣም ብዙ ጎብኚዎችን ወደ ሀገር ውስጥ የመሳብ እንዲሁም በተለያዩ የዓለም አቀፍ መድረኮች በመገኘት ኢትዮጵያን የማስተዋወቅ እና ስለኢትዮጵያ እውነታውን የማስጨበጥ ስራዎችም ተሰርተዋል። ባለፉት ጊዜያት እነዚህን የቤት ስራዎች ስንሰራ ቆይተናል። ከጥራት ጋር የተያያዙም ብዙም ባይባል የሞከርናቸው ስራዎች አሉ፤ እነሱን እናስቀጥላለን።

እነዚህን በመጀመሪያው ዓመት በስፋት መሰራት የነበረባቸውና የተጠራቀሙ የቤት ስራዎች ተሰርተዋል። ነገር ግን የተለያዩ ፈተናዎች የሉም ማለት አይደለም ። ሀገር በጦርነት ውስጥ ስትሆን ፣ ጦርነት ለልማት የሚሆንን ሀብት መጠየቁ አይቀርም፤ ያም ሆኖ የመስራት አቅማችን ያን ያህል የተገደበ አልነበረም። ፈጠራ የተሞላባቸው መፍትሔዎችን ፈልገን ብዙ ስራዎች ተሰርተዋል።

**ጥያቄ ፡- ገቢ ከማሳደግ እና የስራ እድል ከመፍጠር አኳያ በዘርፉ እየተከናወኑ ያሉ ስራዎች ምን ደረጃ ላይ ይገኛሉ ?**

**አምባሳደር ናሲሴ ፡-** ቅድም እንዳነሳሁት ትላልቅ ግቦችን አስቀምጠናል። ከቱሪስት ፍሰት አንጻር

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

## “የገበታ ፕሮጀክቶች የግሉን...

ከገጽ 7 የዞረ

በጣም ትልቅ ግብ አስቀምጠናል። የስራ ዕድል ከመፍጠር አንጻርም ትልቅ ቁጥር አስቀምጣናል። ከመዳረሻ ልማት አንጻር እንዲሁ ትልቅ ቁጥር አስቀምጠናል /ይህን አሁን የከለስንበት ሁኔታም አለ/ ከመዳረሻ ልማት አንጻር መድረስ የየምንፈልግበት ቦታ አለ።

እነዚህን ግቦች ተሳቢ በማድረግ የተለያዩ የተጀመሩ ስራዎችን በማስቀጠል ላይ ነን ። ይህንንም በማድረጋችን በጣም ብዙ ጥቅሞችን እያየንብት ነው ። ለምሳሌ ያለፈውን የ2015 በጀት አመት የመጨረሻ ወራት / ከጥር እስከ ሰኔ አካባቢ ያሉትን ወራት/ ብንወስድ የአለም ቱሪዝም ድርጅት /WTO/ ባወጣው ሪፖርት መሰረት የቱሪዝም ስራዎቻችን ዳግም ማስራራት ችለዋል፤ ማንሰራራት ብቻም ሳይሆን ብዙ የቱሪስት ቁጥር ካዩ የአፍሪካ ሃገራት መካከል ኢትዮጵያ አንዷ መሆን ችላለች።

ይህ የሆነው ለምንድን ነው ? እነዚህ ሁኔታዎች ተደማምረው ነው። አዳዲስ መዳረሻዎች ወደ ስራ መግባታቸው፣ በሃገር ገጽታ ግንባታ ላይ በቂ ስራ ባይሰራም ጥሩ ጅምር መኖሩ፣ የሀገር ውስጥ ቱሪዝም መነቃቃት መቻሉ.፣ መንግስት ለዘርፉ የሰጠውን ትኩረት ተከትሎ የግሉ ዘርፍ በዘርፉ በስፋት ማሳተፍ በመቻሉ ነው።

የቅንጅት ስራዎቻችንም ሌሎች አስተዋጽኦ ያደረጉ ናቸው። ከተለያዩ የመንግሥት እና የግል ተቋማት ጋር ስራዎችን አብረን ማከናወናችን ፤በተለይ በማስተዋወቅ ረገድ እንደ ኢትዮጵያ አየር መንገድና ቱር ኦፕሬተሮች ከመሳሰሉት ጋር የተከናወኑ ስራዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል። እነዚህ የቅንጅት ስራዎች የቱሪስት ፍሰቱ እየጨመረ እንዲመጣ እና ከፍተኛ መነቃቃት እንዲፈጠር አስተዋጽኦ አድርገዋል። ያለፈውንም ሩብ ዓመት ስንመለከትም ከዚህ የተለየ አይደለም ። የሀገር ውስጥ ቱሪዝምን ጨምሮ የቱሪስት ፍሰቱ በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል ።

ልንደርስብት ከምንፈልገው ቁጥር አንጻር ሲታይ ግን አሁንም ብዙ የቀሩን የቤት ስራዎች እንዳሉን ታሳቢ እናደርጋለን። ከእቅዳችን አንጻር ጥሩ መጥናል ፤ነገር ግን ደግሞ በስፋት ሰርተን ያስቀመጥነውን ቁጥር ቢቻል ማሳካት ካልተቻለ ቀረብ ማለት ያስፈልጋል።

**ጥያቄ ፡- በአቅዱ መነሻ ላይ በ2012 ዓ.ም ወደ 850 ሺ ቱሪስቶች ሀገሪቱን ይጎበኙ እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ፤ በእቅዱ ማብቂያ ላይ ደግሞ ይህን አሀዝ ወደ ሰባት ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ለማድረስ ነው እየተሰራ ያለው። በሀገሪቱ እየተከናወኑ ያሉ የመዳረሻ ልማት ስራዎች ለእዚህ አጋዥ ይሆናሉና የመዳረሻ ፕሮጀክቶቹ /የገበታ ፕሮጀክቶቹ/ ተጽእኖ ምን ይመስላል?**

**አምባሳደር ናሲሴ ፡** እንደሚታወቀው መንግሥት በዋናነት አስቻይ ፖሊሲ እና የህግ ማዕቀፍ ማውጣት ፤የግሉን ዘርፍ የማበረታታት ሚና ነው ያለው ። አሁን የምናያቸው የልማት ስራዎች የግሉ ዘርፍ ደፍሮ እንዲገባባቸው የሚያደርጉ ናቸው ። ምክንያቱም የግሉ ሴክተር በብዛት በከተሞች አካባቢ የመወሰን ሁኔታዎች ይታይበታል ። ደፍሮ በርቀት ያሉ ቦታዎችን ማልማት ላይ ውስንነት አለ።

እነዚህን ውስንነቶች አንድም ለመቅረፍ ሁለትም “ኢንስፓየር” አድርጎ ሌሎችም እንዲገቡ ለማስቻል ነው ። ሶስተኛው ደግሞ አስፈላጊ የመሰረተ ልማቶች ወደእነዚህ ቦታዎች እንዲደርሱ ለማድረግ ነው። እነዚህ መሰረተ ልማቶች ወደ ሩቅ በቦታ ሲዘረጉ የፕርይቬት ሴክተሩ በተሻለ ሁኔታ ተነቃቅቶ ወደ ሥራ ይገባል የሚል ሃሳብ ነው ።

ከዚህ አንጻር ምንድን ነው የመጣው ለውጥ ? ከተባለ ከዚህ አንጻር ከፍተኛ ለውጥ አምጥቷል። አንደኛ የሀገሪቱ ሙሉ ገጽታ እንዲታይ ማድረግ አስችሏል። አሁን እየተገነቡ ያሉ የልማት ፕሮጀክቶችን ከወሰድን እንደ ሀገር የነበረው የቱሪስት እንቅስቃሴ በተወሰኑ ቦታዎች ላይ ብቻ ነበር። ልማቱ በጣም ውስን ቦታዎች ላይ ይህን የቱሪስት እንቅስቃሴ ማስፋት አስችሏል።

ኢትዮጵያ በሁሉም አቅጣጫ ውብ ናት። ሁሉም አቅጣጫዋ ታሪክ ጠገብ ነው። ሁሉም የሀገሪቱ ክፍል በጣም ያማረ ውብ የሆኑ ባህሎች አሉት፤ ተፈጥሮውም እንደዚያው ያማረ ነው። ስለዚህ እንደ ሀገር እዚህን ሁሉ ሀብቶቻችን መጠቀም ስንችል ነው እድገት የሚታሰበው



። ሀገርን በሙሉ ገጽታ ከማስተዋወቅ ረገድ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

የገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች እንዳሉ ይታወቃል። ቀጣይ ደግሞ የገበታ ለትውልድ ፕሮጀክቶች በተለያዩ ቦታዎች በተለይም ከዚህ ቀደም ባልተለመዱ ቦታዎች ላይ የሚሰሩ ይሆናል። ይህ ደግሞ መዳረሻዎቻችን ቁጥራቸው እንዲጨምር እና የቱሪስት እንቅስቃሴው ወደ ሁሉም የኢትዮጵያ ክፍል እንዲሆን አስተዋጽኦ አለው። ያ የመጀመሪያው የገበታ ፕሮጀክቶች ዋና አላማ ነው።

ሁለተኛው ደግሞ የእነዚህ የገበታ ፕሮጀክቶች ዋና አላማ መሰረተ ልማቱን ወደተለያዩ የሀገራችን ክፍል ማድረስ ነው ። ብዙ ሰው የገበታ ፕሮጀክቶች የሎጅ ግንባታ ስራዎች ብቻ ይመስሉታል። ነገር ግን ዋና አላማቸው የቱሪስት መሰረተ ልማት ናቸው ። መብራቱ፣ ውሃው ፣ ቴሌኮሙ የመሳሰሉት አገልግሎቶችን ጭምር ነው ይዞ የሚሄደው ።

ይህ ደግሞ አንደኛ ለአካባቢው ማህበረሰብ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ። ሁለተኛ ደግሞ የግሉ ዘርፍ ደፍሮ ወደእነዚህ ቦታዎች ሄዶ እንዲያለማ መንገድ ይከፍታል። ይህንን ለምሳሌ በጨረራ አካባቢ ማየት ይቻላል። በወንጪ አካባቢም እየተጀመረ ነው ። በሌሎች አካባቢዎች በግሉ ዘርፍ ላይ መነቃቃት ፈጥሯል።

በሶስተኛ ደረጃ የቱሪስት ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ እንዲጨምር እንዲሁም የሀገር ገጽታን እንዲገነባ አስችሏል። የሀገር ጎብኚዎች ፍላጎት እንዲጨምር እያደረገም ነው። ከቤት ወጥቶ የመሄድ የማየት ፍላጎቱ እንዲጨምር አድርጓል፤ የውጪውም ቱሪስት አዳዲስ ያልታዩ ቦታዎችን ወጣ ብሎ ማየት እንዲችል አስችሎታል።

በአጠቃላይ ስናየው እነዚህ ስራዎች በቱሪስት ፍሰቱ ላይ ብቻ ሳይሆን እንደ አጠቃላይ የቱሪዝም ዘርፉን በማነቃቃት ላይ እንዲሁም እድገት ላይ ከፍተኛ አስተዋጾኦ አበርክቷል።

**ጥያቄ ፡- የቱሪዝም ሚኒስቴር ከሌሎች ተቋማት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ፣እንዲሁም በቱሪዝም ዲፕሎማሲው ገጽታ ከመገንባት ጋር በተያያዘ እየሰራቸው ያሉ ስራዎች ውጤታማነት ምን ይመስላል?**

**አምባሳደር ናሲሴ፡** እንግዲህ፣ እንደ አጋጣሚ ሆኖ ቱሪዝም ከሁሉም ዘርፎች ጋር የተሳሰረ ነው። መልቲ

**ከኢንሳ ጋርም እንደዚሁ፣ ለምሳሌ በቅርቡ የምናስመርቀው የማርኬቲንግና ፕሮሞሽን የሆነ ሀገራዊ ፕላት ፎርም እየሠራን እንገኛለን**

ሴክተራል ዘርፍ ነው። ከሁሉም ዘርፍ የሚፈልጋቸው ግብዓቶች አሉ። ለሁሉም ዘርፍ የሚሰጣቸው ፀጋዎችም አሉ። ስለዚህ የቅንጅት ሥራ በጣም አስፈላጊ ነው። የቅንጅት ሥራውን በተለያየ መልኩ ከፋፍለን ማየት እንችላለን።

አንደኛ ከመንግሥት ተቋማት ጋር ያለ ትስስርና ቅንጅት ነው። ከዚህ አንፃር በአጋርነት የምናያቸውና በጣም በቅርበትና በጋራ የምንሰራቸው ተቋማት ብዙ ናቸው። ለምሳሌ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ከማስተዋወቅ አንጻር፣ ውጭ የሚደረጉ ሥራዎች፣ እንዲሁም ወደ ሀገር ውስጥ ጋብዘን ከሌላ ሀገር ጋር የምናደርጋቸው የትውውቅ ጉዞዎች ጋር በጣም በቅንጅትና በመተሳሰር አብረን እንሰራለን።

እንዲሁም፣ የኢትዮጵያን ገጽታ ከማስተዋወቅ አንፃር የተሰሩ ቪዲዮዎች ላይ አብረን በቅርበት እንሰራለን፤ በተመሳሳይ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርም እንደዚሁ ከማስተዋወቅና የሀገርን ገጽታ ከመገንባት አንፃር በጣም በቅርበት አብረን የምንሰራው ተቋም ነው። ምክንያቱም እንደ ሌሎች ሀገራት ውጭ ሀገር ላይ ራሱን የቻለ የቱሪዝም ቢሮ የለንም።

እኛ ያ ባይኖረንም ኤምባሲዎቻችንን በአግባቡ ከመጠቀም አንፃር ከውጭ ጉዳይ ጋር በተቻለ መጠን እየሰራን እንገኛለን። የፈለግነው ደረጃ ላይ ደርሰናል ወይ? ከተባለ ገና ብዙ መንገድ ይቀረናል፤ የምናሻሽላቸውና ቅንጅቱን የምናጠብቅባቸው ቦታዎች ይኖራሉ። በዚያ መንገድ አብረን እንሰራለን ማለት ነው።

ዲያስፖራውንም እንደ አምባሳደር በመጠቀም ከማስተዋወቅ አንፃርም ከዚሁ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር አብረን የምንሰራ ይሆናል ማለት ነው። ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመሆን የተለያዩ ጉዞዎችን እያዘጋጀን እዚህ ያሉ ዲፕሎማቶች፣ እዚህ ያሉ አምባሳደሮች ቱሪዝም ስንል ምን ማለት ነው? የሰው ሕይወት ከቱሪዝም ጋር እንዴት የተሳሰረ ነው? የሚሉትን በደንብ እንዲረዱ እያዘጋጀን እንገኛለን።

ይህ ለምን ያስፈልጋል ካልክ፤ እዚህ አዲስ አበባ ቁጭ ብሎ የጉዞ ክልከላዎችን ማድረግ ቀላል ነው። በእርግጥ ስጋት ኖሮባቸው የጉዞ ክልከላ የሚደረግባቸው ቦታዎች ይኖራሉ። አካባቢዎችን እየወሰዱ የማሳየት ጥቅምን በሚገባ እንዲረዱ፣ የሕዝቡን ትስስር፣ ከቱሪዝም ጋር ያለውን ትስስር በሚገባ እንዲረዱ ለማድረግ ያስችላል።

ለዚህ ምሳሌ ላሊበላን ብንወስድ፣ ላሊበላ ኑሮው የተሳሰረው ከቱሪዝም ጋር ነው። ኢኮኖሚያዊ ገቢውም የሚያገኘው በአብዛኛው ከቱሪዝም ነው። ስለዚህ በዚህ ላይ ክልከላ ስታደርግ በዚህ ሕይወት ላይ ችግር እንደሚያስከትል (አፌክት እንደሚያደርግ) ቦታው ላይ ሄዶ በማሳየት ነው።

ለዚህም የግንዛቤ ሥራ ለመሥራት ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከተለያዩ ኢንተርናሽናል ተቋማት፣ እንደ ዩኔስኮ ካሉት ጋር በመሆን ለዲፕሎማቲክ ኮሚኒቲው መድረኮችን እናዘጋጃለን ማለት ነው።በቀጣይ ተመሳሳይ ብዙ መድረኮች ይኖሩናል።

ከዚያ በተረፈ ሌሎች ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች አሉ፤ በቅርበት የምንሰራቸው የሥራና ክሂሎት ሚኒስቴር ሥራን ከመፍጠር አንፃር፤ በተለይ እንደ ዘርፍ ቱሪዝም ሥራ ፈጣሪ ነው። እንደሚታወቀው፣ በዓለም ላይ ካሉ አሥር የሥራ ዘርፎች ውስጥ አንዱ ቱሪዝም ነው። ያ ማለት በጣም ትልቅ አቅም ያለው ነው ማለት ነው። ከዚህ አንፃርም ከእነርሱ ጋር በቅርበት የምንሰራባቸው ቦታዎች አሉ።

ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ባህል አንዱ የቱሪዝም ግብአት እንደመሆኑ ከእነርሱ ጋርም የምንሰራቸው ሥራዎች አሉ። እንዲሁም ደግሞ ከቴክኖሎጂ ጋር ተያይዞ እንደ አርተፊሻል ኢንተለጀንስ፣ ኢንሳ ከመሳሰሉ ተቋሞች ጋር በቅርበት እንሠራለን። ለምሳሌ ከአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ጋር ቢሮን ከማደራጀት አንጻር፤ ሎካል ሰርቨሮች፣ ዴታ ቤዞች የተለያዩ ሥራዎችን ሊያሳልጡ የሚችሉ አፕሊኬሽኖችን ከመሥራት አንጻር አብረን እንሠራለን።

ከኢንሳ ጋርም እንደዚሁ፣ ለምሳሌ በቅርቡ የምናስመርቀው የማርኬቲንግና ፕሮሞሽን የሆነ ሀገራዊ ፕላት ፎርም እየሠራን እንገኛለን። ዘርፉ ወደ ቴክኖሎጂ መምጣት ስላለበት ከእነዚህ ተቋማት ጋር አብረን እንሠራለን። ከባንኮች ጋር በተለያየ መልኩ አብረን እንሠራለን። ለምሳሌ ከንግድ ባንክ ጋር እንደምታውቁት የቱሪስት ስማርት ካርድ ወደ ሥራ እንዲገባ አድርገናል።

ከሌሎች ባንኮች ጋርም የተለያዩ ትብብሮች አሉን። ከዚያ በተረፈ እንደ ኢምግሬሽን፤ ከሰተምና ከመሳሰሉት የግድ ሥራዎችን ጋር ስለሚያስተሳስረን፤ ቱሪስቱም ጥሩ ልምድ ኖሮት እንዲመለስ፤ ከእነዚህ ተቋማት ጋር አብረን በቅርበት እንሠራለን። ፌደራል ፖሊስ በጣም አስፈላጊ ነው። ለምን ከጸጥታ ጋር ተያይዞ ብዙ ጉዳዮች ስላሉ።

በቅርቡ እንዲያውም የምንፈራረመው ይኖራል ማለት ነው። እዚህ ጋ የረሳኋቸው ሊኖሩ ይችላሉ፤ ልረሳ እችላለሁ፤ ያልጠቀስኳቸው ተቋማት ሊኖሩ ይችላሉ። እንደ ናሽናል ባንክ፤ ትራንስፖርት ሚኒስቴር ከመሳሰሉት ጋር የቱሪስት ሳታላይት አካውንት እየሠራን ስለሆን፤ ግብአት ከእነዚህም ስለ ምንወስድ ከተለያዩ፣ ከጠቀስኳቸውም ካልጠቀስኳቸውም ተቋመት ጋር በቅንጅት

ወደ ገጽ 9 ዞሯል

# ወቅታዊ

## “የገበታ ፕሮጀክቶች የግሉን...

ከገጽ 8 የዞረ



እንሠራለን።

ይህ ደግሞ አንደኛ ዘርፉ አዲስ እንደመሆኑ መሠረት እንዲይዝ ያስችላል። ሁለተኛ ደግሞ የቱሪስት አገልግሎቱ እየተሳለጠ እንዲሄድ ያደርጋል። ስለዚህ ከሞላ ጎደል ከመንግሥት ጋር እነዚህን ሥራዎች እንሠራለን። ሌላኛው አስፈላጊ ነገር ከግሉ ዘርፍ ጋር የምንሰራው የቅንጅት ሥራ ነው።

እንደሚታወቀው የግሉ ዘርፍ የቱሪዝም ሴክተሩ ዋንኛ ተዋናይ ነው። ስለዚህ ከግሉ ዘርፍ ጋር በቅንጅት መሥራት በጣም አስፈላጊ ነው። ከዚህ አንጻር እንግዲህ ከኦፕሬተሮቻችን፣ ከቱር ጋይዶች፣ ከሆቴል ማህበራትና ከመሳሰሉት ጋር በጣም በቅርበት እንሠራለን። ለዚህም ጥሩ ማሳያ የሚሆነው በቅርቡ፣ መስከረምና ጥቅምት ላይ በሳይንስ ሙዚየም ያደረግነው ኤግዚቢሽን ነው።

ሙሉ የቱሪዝም ቤተሰብን አንድ ቦታ ሰብስቦ ጥሩ የሆነ ነገር ለማሳየት ችለናል ማለት ነው። ከዚያ በተጨማሪ ግን በዋናነት የኢትዮጵያን ገጽታ ከመገንባት አንጻር፤ ኢትዮጵያን ከማስተዋወቅ አንጻር ከእነዚሁ የግሉ ዘርፍ ተዋናዮች ጋር ሥራዎችም እንሠራለን። ለምሳሌ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ትሬድ ፌሮችን ስንሳተፍ ይዘን የምንሄደው የግሉን ዘር ተዋናዮች ነው። ቱር ኦፕሬተሮች ወደ 40 በመቶ የሚሆነውን እንዲያስተዋውቁ እናደርጋለን። ከእነርሱ ጋር በቅርበት እንሠራለን ማለት ነው። በተለያየ ዘርፍ ከግሉም ጋር፤ ከመንግሥት አካላትም ጋር በቅርበት እየሠራን እንገኛለን።

**ጥያቄ፡- በዘርፉ ያለውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ችግር ለመፍታት ምን እየተሰራ ነው**

**አምባሳደር ናሲሴ፡** ከሰው ሀብት ጋር ተያይዞ ሁለት ክፍተቶች አሉ። አንደኛው ክፍተት በዘርፉ በቂ ሰለጠነ የሰው ኃይል አለ ወይ? ብትለኝ፤ በቂ የሆነ፣ በምንፈልገው ደረጃ በስልጠና አልፎ የመጣው የሰው ኃይል በጣም ጥቂቱ ነው።

,በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ አቅርቦት ብቻ ሳይሆን የክህሎት ጉዳይ ነው፤ ክህሎት ስል ሠልጥኖ ፤ የሚፈለገውን ክህሎት በሚፈለገው ደረጃ አዳብሮ ወደ ሥራ የገባ የሚለውን ነው። የመጀመሪያው ጋር ስንሄድ በጣም ብዙ ተቋማት፣ በጣም ብዙ ዩኒቨርሲቲዎች በቱሪዝም ዘርፉ ሥልጠና ይሰጣሉ። ከዛም ተጨማሪ በቲቪቲ ደረጃ ሲቲቲአይን ጨምሮ፤ ሌሎችም ተቋማት እንደዚሁ ሥልጠናዎችን ይሠጣሉ።

እነዚህ እንግዲህ ቶሎ ወደ ሥራው ይወሰዳሉ። አሁን የግሉ ዘርፍም እየተነቃቃ ብዙ ኢንቨስት እያደረገም ነው። አሁን እነዚህ ወደ ተቋማት ይገባሉ። ነገር ግን አሁንም በምንፈልገው ደረጃ፤ ሙሉ በሚባል ደረጃ በሆቴሎቻችን ላይ፣ በተለያዩ ቦታዎች ላይ የምናያቸው ሙሉ በሙሉ የሠለጠኑ ናቸው ማለት አይቻልም።

ምናልባት ባለ ኮከብ ሆቴሎች ላይ ብዙ የሠለጠኑ ባለሙያዎችን እናይ ይሆናል። ነገር ግን ደግሞ ወደ ታች ወረድ እያልን ስንሄድ የማናይበት ሁኔታ በጣም ሰፊ ነው። ስለዚህ ከዚህ አንጻር የሚሰሩ ብዙ ሥራዎች ይኖራሉ። የካሪኩለም ማሻሻያዎች ላይ የበለጠ ልምምድ በሚሰጥበት ሁኔታ ላይ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ስርአተ ትምህርቱን ከመከለስ ጀምሮ የተለያዩ ሥራዎችን እንሰራለን።

ነገር ግን ይሄ በቂ አይደለም፤ ቅድም እንዳነሳሁት ክህሎቱን ማዳበር፤ ሰልጠን አንድ ነገር ነው። የበለጠ ክህሎትን ማዳበር ደግሞ ሌላ ነገር ነው። ስለዚህ ክህሎትን ከማዳበር አንጻር እንደ ሀገር አንድ ያለብን ክፍተት የኤክሰለንስ ሴንተር (የልህቀት ተቋም) የለንም። የኤክሰለንስ ሴንተር ስለሌለን ብዙ ባለሙያዎች ትልልቅ ሆቴሎች፣ ለምሳሌ ኢንተርናሽናል ሆቴሎችን ወደ ኢትዮጵያ ስናስገባ እነዚህን ሙያዎች ይፈልጋሉ።

የሰለጠነና ልምድ ያለው ሼፍ፣ የጣሊያን ሼፍ ሊሆን ይችላል፤ የቻይና ምግብ የሚሰራ ሼፍ ሊሆን ይችላል። እንዲሁም የተለያዩ ደረጃዎች ላይ ያሉ ባለሙያዎችን በዛ ጥራትና ደረጃ ማቅረብ ያስፈልጋል። እነሱም ይህንን ይፈልጋሉ። ስለዚህ ሌላው እንግዲህ በትኩረት ወደ ፊት መስራት ያለብን ክፍተቶቻችንና የቤት ሥራዎቻችን ናቸው ብለን የምንወስደው ያሉንን ተቋማት ወደ ሴንተር ኦፍ ኤክሰለንስ (የልህቀት ማእከል) ማሳደግ ነው።

አሁን ባሉበት ደረጃ በጣም ብዙ ሥራ ይቀረናል። ስለዚህ ሴንተር ኦፍ ኤክሰለንስ መገንባታችን የግድ ይሆናል። ስለዚህ በሱ ላይ ብዙ ሥራ የሚጠይቀን ይሆናል ማለት ነው። እነዚህን ክህሎት አዳብረው፤ ያንን ክህሎት ይዘው ሊወጡና ወዲያው ወደ ሥራ መግባት የሚችሉ ባለሙያዎችን ማፍራት ላይ አሁንም ብዙ ሥራ ይቀረናል።

**ጥያቄ፡- እናንተ የምትሰጡት የብቃት ማረጋገጫ ሆነ የቁጥጥር ስራዎች ለዘርፉ እያበረከቱ ያለው አስተዋጽኦ እንዴት ይገለጻል ?**

**አምባሳደር ናሲሴ፡** ያው እንግዲህ እንደሚታወቀው የተለያየ የብቃት ማረጋገጥ ሥራዎችን እንሠራለን። የደረጃ ምደባ ሥራዎችን እንሠራለን። የደረጃ ምደባና የብቃት ማረጋገጥ ሥራ በመሰረቱ ጥሩ ሆኖ ሁሌም ብቃት ማረጋገጥ፤ ሁሌም ደረጃ መመደብ ጥሩ ሆኖ በራሱ ብቻውን በቂ አይደለም።

የሀገራችንን የሰርቪስ ኳሊቲ (የአገልግሎት ጥራት) ወደ ተፈለገው ደረጃ ለመውሰድ ብዙ መስራት ያሉብን ጉዳዮች ይኖራሉ። ነገር ግን እነዚህ የብቃት ማረጋገጥና የደረጃ ምደባ ሥራዎች የራሳቸው የሆነ፣ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ አላቸው፤ ለምሳሌ የቱር ኦፕሬተሮችን መውሰድ ይቻላል። የብቃት ማረጋገጥ ሥራዎችን እንሰራለን። እነዚህ የብቃት ማረጋገጥ ሥራዎች የቱር ኦፕሬተሮች በየጊዜው ራሳቸውን እንዲያበቁ፤ የሚቀጥሯቸው ሠራተኞችም በሚገባ የሰለጠኑ፤ ሙያው ያላቸው እንዲሆኑ ያስችላል።

እንደዛ ሲሆን ደግሞ ያው ለሌላው የሚሰጠው አገልግሎት (ሰርቪስ) ያንኑ ያህል ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የራሱ አስተዋጽኦ አለው። የሆቴል ደረጃ ምደባንም ካነሳን በተመሳሳይ መንገድ የምናያቸው፣ የተለያዩ መመዘኛና መስፈርቶች አሉ።የሰው ኃይል እናያለን፣ ፋሲሊቲውን እናያለን፤ የተለያዩ ጉዳዮችን እናያለን። ይህም ስራ ምን ሊሆን ያስችላል፣ ቢያንስ ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት እንዲሰጡና ተቋማት ወደዛ መንገድ እንዲሄዱ ያስችላል። ሙሉ በሙሉ እዛ ደርሰዋል ወይ? የሚለው ጥያቄ እንዳለ ሆኖ ማለት ነው።

እንደምታወቀው የኮከብ ደረጃ ማለት ዓለም አቀፍ መግባቢያ ቋንቋ ነው። ኢትዮጵያ ያለ አንድ ባለ አምስት ኮከብ ሆቴል ዱባይ ካለ ባለ አምስት ኮከብ ደረጃ ሆቴል በታች መሆን የለበትም። ምክንያቱም ባለ አምስት ኮከብ ማለት ዓለም አቀፍ መግባቢያ ቋንቋ ስለሆነ። ስለዚህ ሆቴሎቻችንን ወደዚያ ደረጃ ማድረስ ስለሚያስፈልግ ያንን እየተከታተሉ በቁጥጥር ሱፐርቪዥን፣ በድጋፍ ሱፐርቪዥን ወደዛ ደረጃ እንዲበቁ ማድረግ ያስፈልጋል።

ኮከቡን መስጠት ብቻም ሳይሆን። ስለዚህ ከዚህ አንጻር የጀመርናቸው ጥሩ ጥሩ ስራዎች አሉ፤ ሁለቱ ስራዎች ጥሩ ሆነው፣ ነገር ግን እንደአጠቃላይ እንደ ሀገር ደግሞ የቱሪስት አገልግሎት አሰጣጣችን ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ብዙ መሰራት ያለባቸው ስራዎች አሉ። ስለዚህ ለመጀመር የምናስበው ፕሮግራም አለ። “ናሽናል ሰርቪስ ኳሊቲ አሹራንስን" ወደ ሥራ ለማስገባት ጥናቱም ዲዛይኑም አልቋል።

ይህንን ማድረግ ለምን ያስችላል፣ አንደኛ አቅርቦት ላይ ከማተኮር ይበልጥ ደግሞ የአገልግሎት ጥራት ላይ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዲያተኩሩ እድሉን ይፈጥራል። ሁለተኛው በይበልጥ የአገልግሎት አሰጣጥ መስፈርት ምንድነው የሚል ማህበረሰብንና የወረደ አገልግሎትን የሚጠየፍ ማህበረሰብን መፍጠር ነው። ምክንያቱም በተለያዩ ሀገራት እንደሚታወቀው ሰዎች ደረጃ የሚሰጧቸውን ነው ሌላውም እያየ የሚሄደው።

ሬስቶራንት ስትፈልግ “የትኛው ነው ጥሩ?" የሚለውን ጉግል አድርገህ በደንብ ታውቃለህ። በኢትዮጵያም ስታንዳርድ ወደዚያው መሄድ ስላለብን የወረደ አገልግሎት የሚጸየፍ ህብረተሰብን መፍጠርና በተለያየ ቴክኖሎጂ ተደግፎ፣ የምዘና ሲስተም ተዘጋጅቶ ሁሉም እየተመዘነ፣ ደረጃው እየታወቀ

**ሬስቶራንት ስትፈልግ “የትኛው ነው ጥሩ?" የሚለውን ጉግል አድርገህ በደንብ ታውቃለህ**

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

## “የገበታ ፕሮጀክቶች የግሉን...

ከገጽ 9 የዞረ

መሄድ ይኖርበታል ማለት ነው። ስለዚህ ወደ ፊት ጉግል አድርገህ የትኛው ሬስቶራንት ወይም ሆቴል ጥሩ ነው የሚለውን እንደ ሀገር መድረስ ይኖርብናል ብለን ወደ ሥራ ለማስገባት እየሰራን ነው።

**ጥያቄ ፡- ወደ ቱሪዝም ዲፕሎማሲው እንመለስና በቅርቡ የጨበሬው ዳና ሎጅ ሲመረቅ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ያቀረቡት ጥሪ ነበር። በተለይም የሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ሀገራቸውን እንዲጎበኙ ጥሪ አቅርበው ነበር። በዚህም እርስዎም በመጀመሪያዎቹ ቀናት አቀባበል ሲያደርጉ ነበር፤ አሁን ያለበት ደረጃ እንዴት ነው?**

**አምባሳደር ናሲሴ፡** ቅድም ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ወደ ስልጣን ከመጡ ጊዜ ጀምሮ በተለያየ መንገድ በውጪ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ወንድም እህቶቻችን ጋር ለመድረስ ጥረት አድርገዋል። በአካልም በመሄድ፣ እንዲሁም ደግሞ በተለያዩ ጊዜያት ጥሪዎችን በማድረግ።

ለሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያዊያን የተደረገው ጥሪም የዚያው ቀጣይ ክፍል ነው ብለን መውሰድ እንችላለን። በተለያዩ ጊዜያት በርካታ ኢትዮጵያዊያን ወደ ሀገር እንዲገቡ ጥሪ ተደርጎ በጣም ጥሩ ውጤት አይተንበታል። ለምሳሌ የ2014ቱን ማንሳት ይቻላል፤ በጣም ትልቅ ቁጥር ያላቸው ኢትዮጵያዊያን ወደ ሀገራቸው መጥተው ከሀገራቸው ጎን ቆመው አንደኛ ከሀገራቸው ጋር መሆናቸውን ለውጭው ዓለም አሳይተዋል። ሁለተኛ ሀገራቸው አንፃራዊ ሰላም እንዳለና ሰዎች መምጣት እንደሚችሉ አሳይተዋል። ከዚህ በተጨማሪ ከወገኖቻቸው ጋር ተሳስረው በተለያየ መልኩ ወገኖቻቸውን ደግፈዋል። የተለያዩ የሀገሪቱን ክፍል ጎብኝተው የቱሪዝሙ እንቅስቃሴ እንዲቀጥል የተሻለ እድል ፈጥረዋል።

ከዚሁ ቀጥሎ በ2015 ዓ.ም የተለየ ጥሪ ተደርጓል። አሁንም ለሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያውያን ጥሪ ተደርጓል። ዋና ዓላማው የትውልድ ቅብብሎሽ እንዲኖር ማድረግ ነው። እንደሚታወቀው ኢትዮጵያውያን ለብዙ ዓመታት በውጭ ሀገራት ኖረዋል። ልጆች አፍርተዋል። ልጆቻቸው የማንነት ጥያቄ አለባቸው። የመጡበትን የእናት የአባቶቻቸውን አያቶቻቸውን ሀገር ማወቅ ይፈልጋሉ።

እንደሚታወቀው ደግሞ የሚያኮራ ታሪክና ባህል አለን። ውብ የሆነ ተፈጥሮ ያላት ሀገር አለቻቸው። ይህ እደመሆኑ መሰል ትስስር መፍጠር አስፈላጊ ነው። እነሱም መነሻቸውን ያውቃሉ። ኢትዮጵያ የሁሉም መነሻ ነች። የሰው ልጅ መገኛ ነች። የእናት የአባቶቼ የአያቶቼ ሀገር የሚለው ስሜት ደግሞ በጣም ከፍተኛ ነው። እንደ ሰው ልጅ ሁላችንም መነሻችንን ማወቅ እንፈልጋለን። ይህ ትልቅ ስሜት ነው። ይንን ለማወቅ ያስችላል።

ሁለተኛ መጥተው ባህልና ታሪካቸውን እንዲያውቁ እንዲሁም ለወገኖቻቸው መስጠት እንዲችሉ መቀራረብ እንዲችሉ መንገድ ለመፍጠር ነው። ስለዚህ የጥሪው ዓላማ ሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያውያን መጥተው ሀገራቸውን እንዲያውቁ ነው። ይህንን በሶስት ፌዝ ከፍለነዋል። የመጀመሪያው ከብዝሃ ባህል መሠረት ጋር ይተዋወቁ ብለነዋል።:

ምክንያቱም ይህ ወቅት ብዙ ፌስቲቫሎች ያሉበት እንዲሁም በተለያየ መልኩ ሀገራቸውን ባህላቸውን ለማወቅ የተመቸ አጋጣሚ የሚፈጠርበት ነው። ለዚህም የተለያየ ሁነቶች ተዘጋጅተዋል። ባህላቸውን ያውቃሉ። ይማራሉ። ወደተለያዩ የሀገራችን ክፍል ሔደውም ራሳቸው ለራሳቸው ዲስከቨር ያደርጋሉ።

ሁለተኛው ዙር ከታሪክ መሠረቶች ጋር ይታዋወቁ የሚል ነው። ይህ የዓድዋ ሰሞን የሚጀምር ነው። ከዓድዋ መጀመሩ ብቻ ሳይሆን በተለያየ ወቅትና ሁኔታ ስለታሪካቸው ኢትዮጵያ ለዓለም በተለይ ለጥቁር ሕዝቦች ነፃነት ያበረከተችው አስተዋፅኦ ውይይት የሚደረግበት ነው። ታሪካችንን ወደ ኋላ መለስ ብለን የምናይበት ወቅት በመሆኑ ከታሪካቸው ጋር እንዲተዋወቁ፤ ይህ እድል እንዲኖራቸው ለማስቻል ነው።

በእነዚህ ዙር የተለያዩ የሀገሪቱን ክፍሎች ተዘዋውረው የጉብኝቱ ጉዳይ እንዳለ ሆኖ በሶስተኛው ዙር ሲመጡ ደግሞ ረዘም ያለ ጊዜ ስላላቸው በሚገባ ባህሉንም ታሪኩንም እንዲያውቁ የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር ነው። እንደሚታወቀው በዚህ ወቅት እንደ ሀገር ከአረንጓዴ ዐሻራና እና ከበጎ አድራጎት ጋር ተያይዞ የተለያየ ኢንሺየቲቮች አሉን።

ይህ የእረፍት ወቅታቸውን እንደመሆኑም በእነዚህ ተግባራት ላይ እንዲሳተፉና ይበልጥ የተሳሰሩ እንዲሆኑ ለማስቻል ታሳቦ የተጠራ ጥሪ ነው። ስለዚህ ሁሉም ሰው ይህን በመልካም ወስዶ በጣም በትልቅ ቁጥር ወደ ሀገር እየገባ ነው። ቁጥሩንም ወደፊት አንድ ላይ ደምረን የምናሳውቅ ይሆናል። ነገር ግን በጥሩ ሁኔታ ወደ ሀገር ውስጥ እየገቡ እኛም እየተቀበልን ነው።

**ጥያቄ፡-በተጠናቀቀው በፈረንጆቹ ዓመት 2023 በተለይም ዓለም አቀፍ ቅርሶችን በማስመዝገብ ረገድ ከፍተኛ ሥራ የተሠራበት እንደሆነ በተለያየ መገናኛ ብዙሃን ሲገለፅ ነበር። በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት የሳይንስና ባህል ተቋም የተመዘገቡ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶቻችን ቁጥር እያሻቀበ መጥቷል። በዚህ ረገድ የተሠሩ ሥራዎች ምንድ ናቸው?**

**አምባሳደር ናሲሴ፡-** አንድን ቅርስ አዘጋጅቶ ለዓለም ቅርስነት ማስመዝገብ በጣም በብዙ ውጣ ወረዶች መሃል ያልፋል። ብዙ ሀገራት ለብዙ ነገር ይጠቀሙበታል። የመጀመሪያው የሀገራቸውን ገፅታ ለመገንባት ይጠቀሙበታል። ያላቸውን ለማውጣትና ለዓለም የሚያበረክቱትን ነገር ለሀገር ገፅታ ግንባታ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ስላለው ለእሱ ይጠቀሙበታል።

ሁለተኛው የቱሪስት መዳረሻ ከማልማትና ከማስተዋወቅ አንፃር ከፍተኛ ፋይዳ ያለው ስለሆነ የቱሪስት መዳረሻዎቻቸውን ከማስፋት አንፃር ይጠቁሙበታል። እኛ እንደ ሀገር ብናስመዘግብ ከሞላ ጎደል ሙሉ ኢትዮጵያን ማስመዝገብ እንችላለን ብለን በድፍረት መናገር እንችላለን።

እኔ በግሌ ይህን መናገር እችላለሁ። ለምን ሌሎች እንደ ዓለም ቅርስ የሚያስመዘግባቸውን ጉዳዮች በቅርበት ስለምመለከት ማለት ነው። ስለዚህ የተለያዩ ጉዳዮችና ቦታዎችን እንደ ዓለም ቅርስ የሚያስመዘግቡት አንደኛው ምክንያት እንደ ቱሪስት መዳረሻ ለማልማትና ሰውን ወደ ሀገር ለመሳብ ነው።

እንደሚታወቀው ዩኔስኮ አንድን ቅርፅ ሲመዘግብ ከፍ ያለ ዓለም አቀፍ እሴት “አውትሳንዲንግ ዩኒቨርሳል ቫሊው” አለው ፤ ለዓለም የሚያበረክተው አስተዋጽኦ አለው፤ ከሌሎቹ የተለየ ዋጋ አለው ብሎ ነው የሚመዘግበው። ይህ ትልቅ እውቅና ስለሆነ ቀደም ሲል እንዳልኩት የሀገር ገፅታን ይገነባል።

ሁለተኛ ደግሞ ዓለም አቀፍ እውቅና ከመስጠትና የቱሪስት ፍሰት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲጨምር ከማድረግ አንፃር የራሱ አስተዋጽኦ አለው። በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ የጥበቃና የእንክብካቤ ሥራ ነው። ይህ ሥራ ለቅርሶች ከፍ ያለ ይሆናል። ሀገራት በሚገባ ይንከባከባሉ ይጠብቃሉ። ይህን መሰል አስተዋጽኦ ስላለው ብዙ ሀገራት ከፍ አድርገው የሚያዩት በመሪ ደረጃም መጥተው እውቅናው የሚቀበሉት ነው።

ወደሀገራችን ስንመጣ አሁን የተመዘገቡ ቅርሶች ቅድም እንደጠቀስኩልህ ማስመዝገብና ማስተዋወቅ አለብን ብዬ የምልበት ምክንያት አንደኛ ከአርባ ዓመት በኋላ ነው ለመጀመሪያ ጊዜ ሁለትና ሶስት ቅርስ ስናስመዘግብ። እንደሀገር ደግሞ ላለፉት አስራ ሶስት ዓመታት ምንም ዓይነት ቅርስ አላስመዘገብንም።

ዶክሜንቶቻችንን እንልካለን በተለያዩ ምክንያቶች ዶክሜንቶቻችን አያልፉም። ብዙ ጊዜ ከዶክሜንት ዝግጅት ጥራት፣ ከማስረዳትና ሎቢ ከማድረግ ጉድለት ዶክሜንቶች አያልፉም። በዚህ ዓመት ተጠሪ ተቋማቶቻችን የቅርስ ባለሥልጣን፣ የዱር እንስሳት ጥበቃ ባለሥልጣን እንዲሁም ሌሎችም አካላት በሠሩት ከፍተኛ ሥራ ሶስት የዓለም ቅርሶችን ለማስመዝገብ ዕድል አግኝተናል። ይህ ትልቅ ስኬት ነው።

ይህ እንደሀገር እንድምታው ምንድነው ካልከ አንደኛ የሀገር ገጽታ ይገነባል። ሁለተኛ ፍሪ ፕሮሞሽን ነው። ኢትዮጵያ ያሏት ቅርሶች ሁሉም ቱሪስት መጥቶ ሊያያቸው የሚፈልጋቸው የሚያጓጓ ቅርሶች ናቸው። ስለዚህ ከዚያ አንጻር ያላቸው አስተዋፅኦ ከፍ ያለ ስለሆነ ሁሉም መጥቶ ሊመለከታቸው ይፈልጋል።

**እንደ ሀገር እነዚህ በዓለም አቀፍ ቅርስ ሆነው የተመዘገቡ የዓለም ቅርሶችን ማልማትና ወደመዳረሻነት መቀየር የቤት ሥራችን ነው**

ወደሀገር ቤት የቱሪስት ፍሰትን ከመጨመር አንጻር የራሱ አስተዋጽኦ አለው። ከቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ አንጻር የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ አለው። እነዚህን ቅርሶች እንድንከባከብ እንድናለማ መንገድ ይከፍታል።

እንደ ሀገር እነዚህ በዓለም አቀፍ ቅርስ ሆነው የተመዘገቡ የዓለም ቅርሶችን ማልማትና ወደመዳረሻነት መቀየር የቤት ሥራችን ነው። ለምሳሌ የተለያዩ ቦታዎች በዓለም ቅርስነት ተመዝግበዋል። የተወሰኑት የቱሪስት መዳረሻ ናቸው፤ የተወሰኑት የቱሪስት መዳረሻ አይደሉም።



ለዚህም እነጥያን ማንሳት ይቻላል። ሌሎችም ኦሞ፣ ሎሮባሺ እያልን ማንሳት እንችላለን። እነዚህን ወደ መዳረሻነት መቀየር ኃላፊነት አለብን፤ ከዚህ እውቅና አስፈላጊውን ጥቅም ለማግኘት። ስለዚህ የቤት ሥራ አለብን ሁሉም ሰው ያለውን ፋይዳ ተገንዝቦ እዚህ ላይ መረባረብ ይኖርበታል።

**ጥያቄ - በቀጣይ ምናልባት በዚህ ረገድ የተያዙ ጊዜያዊ ሊስቶች ይወጣሉና የተያዙ ቅርሶች ካሉ?**

**አምባሳደር ናሲሴ፡-** እንደሀገር የመጀመሪያው የቤት ሥራችን የተያዙ በዚህ ዓመት በተለይ በሚቀጥለው ዓመት ሩብ ዓመት ጊዜያዊ ሊስቶቻችንን መከለስ ለዚህም ብሔራዊ ኮሚቴ አቋቁመናል። ብሔራዊ ኮሚቴ ወደ ሥራ አስገብተን ያሉንን ጊዜያዊ ሊስት ውስጥ ያሉትን ለቅርስነት የታጩትን እንከልሳለን። ስንከልስ አንዱ የምናተኩርበት ነገር የወል የሆኑ፣ የጋራ የሆኑ ሀብቶቻችን ላይ ነው።

የኢትዮጵያውያን የጋራ መገለጫ የሆኑ ቅርሶች ላይ ትኩረት እናደርጋለን። ከዚያ በኋላ ደግሞ ወደሌሎች ቅርሶቻችንን ማስመዝገብ እንሄዳለን። ይሄን ባማከለ መልኩ ክለሳ የሚካሄድ ይሆናል። ከዚያ ደግሞ ለሕዝብ ይፋ ይሆናል። ስለዚህ ኢትዮጵያ ለቀጣይ አምስት፣ አስር ዓመታት ልታስመዘግባቸው የምታስባቸውን ሀብቶች ሁሉም ሰው እንዲያውቃቸው፣ ሁሉም ሰው እንዲረዳቸው፣ ሁሉም ሰው በተቻለ መጠን ለመመዝገባቸው ርብርብ እንዲያደርግ መንገድ ይከፍታል።

ምክንያቱም አንድ ቅርስ ሲመዘገብ በጣም ብዙ ሥራ ነው የሚጠይቀው። ዶክሜቱን የማዘጋጀት፣ የማጥራ፣ ከቋንቋው አቀራረብ ከመሳሰሉት ስታንዳርድ ከማስጠበቅ አኳያ አንዱ ሥራ ነው። ሁለተኛው በየጊዜው የሚጠየቁ ጥያቄዎችን መመለስ ዶክሜቱን አሜንድ የማድረግ ሥራ አለ።

ሶስተኛ ሥራ ደግሞ በዶክሜንቱ ላይ ያለው ነገር መሬት ላይ አለ ወይ ብሎ የሚያይ፣ የሚያጠራ ቡድን ይላካል። ይህን ቡድን አምጥቶ በደንብ አስረድቶ ያለውን ተጨባጭ መሬት ላይ ያለውን ጉዳይ በሚገባ አሳይቶ መመለስ ይፈልጋል። ሥራው በዚህ አያበቃም በዓለም አቀፍ መድረክ ላይ የማስረዳት የማሳመን እንዲሁም ሎቢ የማድረግ ሥራ ደግሞ ይቀጥላል። እነዚህ ሥራዎች ሁሉ ተያይዘው ስላሉ ሥራዎቹ ላይ የብዙ ሰዎች ርብርብ ስለሚያስፈልግ ይፋ እንዳደረግን የተለያዩ አካላትን አሰባስበን ፑል አድርገን ይሄን ሥራ የምንጀምር ይሆናል።

/ይቀጥላል/

# የጉሙዝ ብሔረሰብ-

## ባህላዊ የጋብቻ ሥርዓት

**ዳግም ከበደ**

የቱሪዝም ሚኒስቴር ከወራት በፊት የቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ ሀገር አቀፍ አውደ ርእይ ማካሄዱ ይታወሳል። በመድረኩም ከመላው ሀገሪቱ የተውጣጡ የባህል፣ የቱሪዝም ሀብቶቻቸውን ያስተዋወቁ በርካታ ባለድርሻ አካላት ተሳትፈዋል። ከእነዚህ ውስጥ የቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል አንዱ ነው። ክልሉ በውስጡ የሚኖሩ ብሔረሰቦችን ቱባ ባህል፣ የተፈጥሮ ሀብት፣ ቅርስ እና ልዩ ልዩ መስህቦችን በአውደ ርእይው ለውጪና ለሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ማስተዋወቅም ችሏል።

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከሚኖሩ ነባር አምስት ብሔረሰቦች መካከል የጉሙዝ ብሔረሰብ አንደኛው ነው። በሳይንስ ሙዚየም በተካሄደው አውደ ርእይ ላይ የብሔረሰቡ ባህላዊ፣ ታሪካዊ፣ ተፈጥሯዊና የቱሪዝም መስህብ ሀብቶችን የማስተዋወቅ ሥራ በስፋት ተካሂዷል። የዝግጅት ክፍላችን ዘጋቢ በስፍራው በተገኘበት ወቅት ስለ ብሔረሰቡ ባህልና የኑሮ ዘይቤም መረጃዎችን አግኝቷል።

ከዚህ ውስጥ የጉሙዝ ብሔረሰብ ባህላዊ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት አንዱ ሲሆን፣ በዛሬው አገርኛ አምድም ስለዚሁ ጉዳይ በጥቂቱ ዳሰሳ እናደርጋለን። በመድረኩ የተገኙት የክልሉ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ የቱሪዝም ልማት ዳይሬክተር አቶ ሽመልስ አድሬ ‹‹የጉሙዝ ብሄረሰብ ባህላዊ እሴቶች›› በሚል የተደረገን ጥናት መሰረት በማድረግ መረጃውን ሰጥተውናል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ ጉሙዝ የሚለው የአማርኛ መጠሪያ በብሄረሰቡ ቋንቋ "ጉንዛ" ከሚለው ቃል የተወሰደ ሲሆን፣ ፍችውም ጀግና ፣ ጎበዝ ፣ ወንድ እንደ ማለት ነው። ከናይሎቲክ የዘር ግንድ የሚመደበውን የጉሙዝ ብሄረሰብ ጥንተ መኖሪያ አስመልክቶ በርካታ መላምቶች ቢኖሩም ‹‹በምዕራቡ የሀ ገራችን ክፍል ይኖሩ ነበር›› የሚለው ግን ባብዛኛው የብሔረሰቡ አባላት ዘንድ ተቀባይነት አለው። ብሔረሰቡ በጋራ የመኖር፣ በጋራ የመስራት ፣ በጋራ የመብላትና በጋራ የመጠጣት አኩሪና አስደሳች ማኅበራዊ ህይወትን ታድሏል።

‹‹ብሔረሰቡ እጅጉን አስደማሚ ባህል ፣ በእጅጉ ማራኪ ታሪክና በጣሙንም መሳጭ መንፈሳዊና ቁሳዊ ቅርሶች አሉት›› የሚሉት አቶ ሽመልስ፤ ከእነዚህ መካከል ዴሞክራሲያዊ የምርጫና አስተዳደር ሥርዓት፣ ‹‹ቆሚያ›› ተበሎ የሚጠራ ባህላዊ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያን ይጠቅሳሉ። በተለይ የትንፋሽ ሙዚቃ መሳሪያው ከተመረጡ የዛፍ አይነቶች ውጤቶች እንደሚሰራ ይገልጻሉ። የሙዚቃ መሳሪያው ሁነቶችን ወይም ክስተቶችን ምክንያት በማድረግ ጥቅም ላይ እንደሚውልም ይገልፃሉ።

በምሳሌነት ሲጠቅሱም የብሔረሰቡ ታላቅ ሰው ወይም የሃይማኖት መሪ ሲሞት፣ የሰብል አዝመራ ደርሶ ወደ ጎተራ ሲገባ፣ በዘመን መለወጫና በክብረ በዓላት ወቅት ይሄ የሙዚቃ መሳሪያ ጥቅም ላይ እንደሚውል ይጠቅሳሉ። በተጨማሪ በርካታ ባህላዊ ሀብቶች እንዳሉ ተናግረው፣ ከእነዚያ ውስጥ ‹‹ኤፂፃ›› በመባል የሚጠራውን በሴቶች እግር ላይ የሚታሰርና ለዘፈን ማድመቂያነት የሚያገለግል ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያን ይጠቅሳሉ። ሴቶቹ እግራቸውን ከፍ እያደረጉ በለመዱት ስልት ደጋግመው መሬቱን ሲመቱ እርስ በእርሱ እየተጋጨ "ክሽ ክሽ ክሽ፣ ክሽ" የሚል ማራኪ ድምጽ እንደሚያሰማ ይናገራሉ።

አቶ ሽመልስ የጉሙዝ ብሔረሰብ በርካታ ባህላዊ እሴቶች እንዳሉትና እነዚህ ሀብቶች በባህልና ቱሪዝም ቢሮው አማካኝነት ተጠንተው እንደተቀመጡም ይገልፃሉ። ሀብቶቹን ለማልማት ለመጠበቅና ለትውልድ ለማስተላለፍ እየተሰራ መሆኑንም ይጠቁማሉ። በጥናት ተለይተው ከተሰነዱ የብሔረሰቡ ባህላዊ እሴቶች መካከል ባህላዊ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት አንዱ እንደሆነ ይጠቅሳሉ። ይህ ባህላዊ የጋብቻ ሥነሥርዓት ያለውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ፋይዳ አብራርተው፣ በምን መልኩ ተፈፃሚ እንደሚሆንም አብራርተዋል።

> **የልጅቷ ቤተሰቦችም የልጁ ቤተሰቦች በስነ ምግባራቸው መልካም መሆናቸውን ሲሰሙ እንዲሁም ልጅቱ በፍላጐቷ መሄዷን ሲያረጋግጡ ምንም ቅሬታ ሳይሰማቸው የሽማግሌውን መልዕክት ከመስተንግዶ ጋር ይቀበሉታል**

በጉሙዝ ብሔረሰብ የጥሎሽ፣ የለውጥ፣ የቤተሰብ እና ሌሎች በርካታ ባህላዊ የጋብቻ ሥነ ሥርዓቶች ቢኖሩም፣ ለዛሬው እኛ በስምምነት የሚደረግ የብሔረሰቡን የጋብቻ ሥነ ሥርዓት መርጠናል።

### ጉሙዝ- ባህላዊ ጋብቻ ሥነ ሥርዓት

አቶ ሽመልስ በብሔረሰቡ ባህላዊ እሴቶች ላይ የተደረገውን ጥናት ዋቢ አድርገው እንዳብራሩት፤ የጉሙዝ ብሔረሰብ ከሁለት መቶ በላይ ጎሳዎች አሉት፤ በጥናቱ ወቅት ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው የሀገር ሽማግሌች ይህንኑ መስክረዋል። በብሔረሰቡ ዘንድ ጋብቻ የሚፈጸመውም በተለያዩ ጎሳ ባላቸው ጉሙዞች መካከል ብቻ ነው። በአንድ ጎሳ ወይም በተመሳሳይ ጎሳ መካከል ጋብቻ መፈጸም በጥብቅ የተከለከለና አስነዋሪ ተግባር ተደርጎ ይወሰዳል።

አንድ ሰው የአባቱንና የእናቱን ጎሳ /ዘር/ ማግባት አይችልም። በተመሳሳይ ጎሳ ጉሙዞች መካከል ጋብቻ ቢፈጸም በመካከላቸው የሚወለዱ ልጆች መጥፎ እድል ይገጥማቸዋል ተብሎ ይታመናል። ስለዚህ በጉሙዝ ብሔረሰብ ከአንድ ጎሳና ዝምድና ባላቸው የብሔረሰቡ አባላት መካከል ጋብቻ መፈጸም በጥብቅ የተከለከለና የተወገዘ ነው። በስህተት እንኳን ጋብቻ ተፈጽሞ ቢገኝ እንዲፈርስ ይደረጋል።

‹‹ማንኛውም ህብረተሰብ የሚጀምረው ከቤተሰብ ሲሆን፣ የቤተሰብ መሰረቱ በተቃራኒ ፆታዎች መካከል ጥንዶች እርስ በርስ ተፋቅረውና ተስማምተው የሚመሰርቱት የጋራ ህይወት ነው›› የሚሉት አቶ ሽመልስ አድሬ፤ ጋብቻ በህብረተሰብ ደረጃም ይሁን በጋብቻ ፈጻሚዎቹ ዘንድ መሰረታዊ ትርጉም ያለው፣ሰዎች ከአንድ የዕድሜ ክልል ወደ ሌላ የዕድሜ ክልል መሸጋገራቸውን የሚያረጋግጡበት፣ በማህበረሰብ ውስጥ የሚኖራቸው ተግባርና ኃላፊነት፣ ከበሬታና ተቀባይነት ከፍ ወዳለ ደረጃ የሚቀየርበት፣ በግላዊ ሕይወታቸው ውስጥ ከራሳቸው አልፈው የሌላን ሰው ህይወት የሚጋሩበትና የራሳቸውን የሚያጋሩበት ልዩ ምዕራፍ ነው ሲሉም ያብራራሉ።

በብዙ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ዘንድ በወጥነት የሚከወን ማህበራዊ ሥርዓት መሆኑንም ይገልፃሉ። የጋብቻ አፈፃፀሙና ባህላዊ ክዋኔው ግን ከቦታ ቦታ፣ ከባህል ባህል፣ ከሀገር ሀገር እንደሚለያይ ያስረዳሉ።

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልል መንግሥት ያሉ አምስት ነባር ብሔረሰቦችም የራሳቸው የሆኑ ልዩ ልዩ የጋብቻ ሥርዓት አፈፃፀሞች እንዳሏቸው የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ያደረገውን ጥናት በማጣቀስ የሚገልፁት የቱሪዝም ልማት ዳይሬክተሩ፤ ከእነዚህ መካከልም የጉሙዝ ብሔረሰብ አንዱ እንደሆነ ያስረዳሉ። በብሔረሰቡ ዘንድ በባህላዊ መንገድ የሚከወኑ ሥነ ሥርዓቶች መኖራቸውን የሚገልፁት ዳይሬክተሩ፣ እነዚህም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳዎችን መሰረት ያደረጉ መሆናቸውን ያመለክታሉ።

‹‹በጉሙዝ ብሔረሰብ ባህላዊ ጋብቻ ማህበራዊ ፋይዳ አለው›› የሚሉት አቶ ሽመልስ አድሬ፤ በብሔረሰቡ ዘንድ ባህላዊ ጋብቻ አንድ ጎሳ ከሌላ ጐሳ ጋር በመጋባት በሚያደርገው የጋብቻ ሥርዓት ተጋቢዎች ዘር በመተካት ትውልድ ያስቀጥላሉ እንዲሁም ከሁለት የተለያዩ ጎሳዎች በመፈላለግ ሲጋቡ ዘር ከመተካት በተጨማሪ የተጠናከረ ማህበራዊ ዝምድና፣ትስስርና ግንኙነት እንዲኖራቸው ያደርጋል ይላሉ። እንዲሁም በተለያዩ ምክንያቶች የተፈጠሩ ግጭቶች እንዳይካረሩ ለማድረግና ሊፈጠሩ የሚችሉ ግጭቶችን ደግሞ ለመከላከል እንደሚረዳ ያስረዳሉ።

‹‹ከማህበራዊ ፋይዳው በዘለለ በጉሙዝ ብሔረሰብ የባህላዊ ጋብቻ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው የጎላ ነው›› የሚሉት የቱሪዝም ልማት ዳይሬክተሩ፤ በባህላዊ ጋብቻ አማካኝነት አንድ ጎሳ ከሌላ ጎሳ ጋር ተባብሮ በመስራት በሚያደርገው መስተጋብር ሌላ የጉልበት ኃይል ገዝቶ እንዳይጠቀም በማስቻል ወጪንም መቀነስ ያስችላል። ቤተሰብን በመመስረት ሥራን በጋራ በመስራት ገቢን ለማግኘት ይጠቅማል። በጋብቻ በመተሳሰር ያላቸውን ገቢ በቁጠባ እንዲጠቀሙ ያግዛል ይላሉ።

### የስምምነት ጋብቻ

የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የቱሪዝም ልማት ዳይሬክተሩ በጉሙዝ ብሔረሰብ ዘንድ ልዩ ልዩ ባህላዊ ከንዋኔዎችን መሰረት አድርገው የሚካሄዱ የጋብቻ አይነቶች መኖራቸውን ይጠቅሳሉ። ከእነዚያ ውስጥ አንዱና ዋነኛው ‹‹የስምምነት ጋብቻ›› መሆኑን ይናገራሉ። የዚህን የጋብቻ ሥነሥርዓት ይዘትም ‹‹የጉሙዝ ብሔረሰብ ባህላዊ እሴቶች›› በሚል በተሰራ ጥናት ላይ ተመስርተው ሥነሥርዓቱና አፈፃፀሙን እንደሚከተለው በምሳሌ አስደግፈው ይገልፃሉ።

‹‹የስምምነት›› ጋብቻ ሁለቱ ተጋቢዎች ከቤተሰብ ፍቃድ ውጪ ወንዱ ሴቷን በፍቅር አማሎ ይዞ የሚሄድበት የጋብቻ ዓይነት ነው። የጋብቻው ሂደትም መጀመሪያ ወንዱ ልጃገረዷን በተስካር፣ በገበያ እና በልዩ ልዩ ቦታዎች አይቶ ለጋብቻ ይፈልጋታል (ይከጅላታል)። ልጅቷን ባያት ጊዜም ይዘፍንና የፍቅር ጥያቄ ያቀርብላታል። ከዛም ከወደደችው የእጇን አንባር ትሰጠዋለች። እሱም ልጅቷ ወደ ምትኖርበት አካባቢ በመሄድ ውሃ ልትቀዳ ወንዝ ስትወርድ እየጠበቀ ‹‹ይዤሽ ልሂድ›› እያለ ያባብላታል።

እሷም ‹‹በአንድ ጊዜ ጠፍቼ አልሄድም፤ በሌላ ጊዜ ተመለስ›› ትለዋለች። በሌላ ጊዜ ከጓደኞቹ ጋር በመሆን ጠብቆ ይዟት እንዲሄድ ይለምናታል። አሁንም ‹‹በሌላ ጊዜ ተመለሱ›› ትላለች። በሶስተኛ ጊዜ ሲመለሱ ይዘዋት ይሄዳሉ። የልጁ ቤተሰቦችም በመገረም ‹‹እንዴት አመጣህት›› ይላሉ። እሱም ተዋደን ነው፤ የእጅ አምባርም ሰጥታኛለች ብሎ ያሳያቸዋል። ቤተሰቦቹም የማን ልጅ እንደሆነች ይጠይቃሉ። የጥሩ ቤተሰብ ልጅ ከሆነች ደስ ብሏቸው ወዲያውኑ ‹‹ልጅቱ ያለችው ከእኛ ጋር ነው። ሌላ ቦታ እንዳትፈልጉ›› ብለው የተወሰነ ብር ጨምረው ሽማግሌ ይልካሉ።

የልጅቱ ቤተሰቦችም የልጁ ቤተሰቦች በስነ ምግባራቸው መልካም መሆናቸውን ሲሰሙ እንዲሁም ልጅቱ በፍላጐቷ መሄዷን ሲያረጋግጡ ምንም ቅሬታ ሳይሰማቸው የሽማግሌውን መልዕክት ከመስተንግዶ ጋር ይቀበሉታል።

ይህ አይነቱ ጋብቻ ምትክ ይጠይቅበትና የለውጥ ጋብቻ ይፈጸምበት ነበር፡ በአሁኑ ወቅት የለውጥ ጋብቻው እንዲቀር ተደርጓል። በብሔረሰቡ ዘንድ የለውጥ ጋብቻ መፈፀም የቀረ ቢሆንም፣ መልኩን ቀይሮ እንደሚስተዋል የሚናገሩ የሀገር ሽማግሌዎች እንዳሉም አቶ ሽመልስ አድሬ ይናገራሉ።

በአሁኑ ወቅት የጉሙዝ ብሔረሰብ በአብዛኛው እየፈፀመ ያለው የጋብቻ ዓይነት የስምምነት ጋብቻ እንደሆነ መረጃ ሰጪዎቹ ይናገራሉ። ሂደቱም መጀመሪያ አግቢው በገበያ ወይም በተስካር ቦታ አይቶ የወደዳትን ልጃገረድ በፍቅር አማሎ ከጓደኞቹ ጋር በመሆን ይዞ ይሄዳል። ከዛም ወደ ልጅቷ ቤተሰብ ሽማግሌ ይልካል። ስምምነት ላይ ከደረሱ በኋላ ለልጅቷ ቤተሰቦች እንደ ጥሎሽ አንድ በሬ፣ አስር ሺህ ብር የምሶሶ 3 ሺ ብር፣ አንድ ሰሀን ቆጭቆጫ፣ የተለያዩ መጠጦችንና የመሳሰሉትን ይዘው በመሄድ ከቤተሰብ ጋር ስምምነት ይፈጥራሉ። ከዚያ በኋላ የተወሰደውን መጠጥም ሆነ የሚበላ ነገር በመብላትና በመጠጣት ይደሰታሉ፤ ይጨፍራሉ። ከልጅቷም ጋር አብረው በሰላም ይኖራሉ።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## የወጣቶችን የወደፊት ተስፋ ያስመለመው የባህር በር ስምምነት

**እስማኤል አረቦ**



ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ በቀይ ባህር ላይ ይዞታ የነበራትና ቀይ ባህርንም ስታዝበት የኖረች ሀገር ነች። ፲ሺ800 ኪሎሜትር የሚረዝመውን የቀይ ባህር ይዞታ በቁጥጥሯ ስራ ያኖረችና ለወጭና ገቢ እቃዎች ሁለት ወደቦች የምታስተዳደር ሀገር ነበረች። ኢትዮጵያን ከቀይ ባህር ውጪ ቀይባህርንም ከኢትዮጵያ ውጭ ማሰብ አይቻልም ነበር።

ሆኖም የኢትዮጵያን ማደግ በማይፈልጉ ኃይላት ኢትዮጵያ ከቀይ ባህር እንድትወገድ ተደርጓል። ላለፉት 30 አመታትም ያለወደብና ባህር በር ለመኖር ተገዳለች። በዚህም የኢትዮጵያ ወደብ አልባ መሆንም ከስነልቦናዊ ቀውስ ባሻገር ለበርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ጫና ህዝቡ እንዲጋለጥ አድርጎታል። የኢትዮጵያን ክብርና ዝና ዝቅ እንዲል ከማድረጉም ባሻገር በኢኮኖሚ ረገድም ተጎጂ እንድትሆን አድርጓታል።

ለበርካታ መሰረተ ልማቶችና ለድህነት መቀነሻ ልማቶችን ይውል የነበረውን ከ፲ነጥብ 6 ቢሊዮን ዶላር በላይ በየዓመቱ ለወደብ ብቻ በማዋል በድህነት ውስጥ እንድትማቅቅ አድርጓታል። ኢትዮጵያ ወደብ አልባ በመሆኗ ለኪራይና ለመጓጓዣ ከፍተኛ ዶላር ስለምታፈስ የሸቀጦች ዋጋ እንዲንርና የኑሮ ውድነትም እንዲባባስ ምክንያት ሆኗል። በዲፕሎማሲ እና በተጽዕኖ ፈጣሪነትም ረገድ የኢትጵያ ሚና አሽቆልቁሏል።

በኢትዮጵያ አዲስ የመንግስት ለውጥ ከመጣ ጀምሮ በትኩረት ከሰራባቸውና ለውጥ ካመጣባቸው ጉዳዮች አንዱ የባህር በር ጥያቄ ነው። መንግሥት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ለዘመናት ቁጭት ፈጥሮ የነበረውን የባህር በር ጣያቄ በመመለስና ስብራትን በመጠገን ታሪካዊ ሚናውን እየተወጣ ይገኛል። ለ27 አመታት ያህል ፈርሶ የቆየውን የባህር ኃይል እንደገና በማደራጀት ኢትዮጵያ እንደገና የባህር ኃይል እንዲኖራት አድርጓል።

ከዚሁ ጎን ለጎንም ኢትዮጵያ ከ33 ዓመታት በኋላ የባህር በር የምታገኝበት አማራጭ ተገኝቷል። ሰላማዊ አማራጭን ሲከተል ቆየው የኢትዮጵያ መንግስት ሰሞኑን ከሶማሊ ላንድ ጋር የባህር በር የሚገኝበትን መግባቢያ ሰነድ (Memorandum of understanding) ተፈራርሟል ።

ይህ የመግባቢያ ሰነድ ሲተገበር አካባቢያዊ መረጋጋት የሚያመጣና ኢትዮጵያም በቀጣናው ላይ አለኝ የምትለውን የባለቤትነት ጥያቄ መልስ እንዲገኝ በር የሚከፍት ነው። ቀጠናዊ ሰላምን በማስፈን የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የተረጋጋ እንዲሆን በር የሚከፍት ነው።

ይህ ሁኔታ ዛሬ በኢትዮጵያውን ልብ ውስጥ ደስታን ጭሯል። የተስፋ ውጋጋንም ለኩሷል። ለዘመናት ያህል በቁጭት ውስጥ ለነበረው ህዝብም ስብራትን ጠግኖ የወደፊት ተስፋ አለምልሟል። በተለይ የነገ ሀገር ተረካቢ ለሆነው ወጣት ትልቅ ሞራል ሆኗል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ዛሬ 126 ሚሊዮን እንደደረሰ ይታመናል። ከዚህ ውስጥ ደግሞ 70 በመቶ የሚሆነው ወጣት የህብረተሰብ ክፍል ነው። ይህ የህብረተሰብ ክፍል ደግሞ አኪኖሚው ሲያድግ የስራ ዕድል ይከፈትለታል፤ጥራቱን የጠበቀ ትምህርትና የጤና አገልግሎት ያገኛል፤ ባለሀብት ሆኖ ሀገሩን ያገለግላል ከራሱ አልፎ ለቤተሰቡ ብሎም ለሀገር አለኝታ ይሆናል።

ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያን ሸብቦ የያዛትና አብዛኛውን ገቢዋን እየበላ ያለውን ለወደብ የሚወጣው በቢሊዮን ዶላል የሚቆጠር ወጪ ወደ ራሷ ካዝና ሲገባና የባህር በር ጥያቄዋም ሲመለሰ ነው። ይህንኑ የዘመናት ጥያቄም ለመመለስ መንግስት የተከተላቸው መንገዶች ተገቢና የወጣቱንም ወደፊት ህልም ያለመለመ መሆኑን የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ተናግረዋል።

ቶሌራ ሙሉጌታ በሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገቨርናንስና ዴቨሎፕመንት የ4ተኛ ዓመት ተማሪ ነው። ቶሌራ ሰኞ ታኅሣሥ 22 ቀን 2016 ዓ.ም ኢትዮጵያና ሶማሊላንድ የባህር በርን በተመለከተ የመግባቢያ ሰነድ መፈራረማቸውን ሲሰማ ልቡ በሃሴት እንደተሞላ ይናገራል። ላለፉት ዘመናትም ኢትዮጵያ ወደብ እና ባህር በር አልባ ሆና በጎረቤት ሀገር ጥገኝነት ውስጥ መቆየቷ ሲያስቆጨው እንደቆየ ይናገራል።

‹‹ኢትዮጵያ ጥንታዊት ሀገርና እና ቀይባህርንም ለዘመናት ስትቆጣጠር የቆች ሀገር ብትሆንም የቅኝ ገዢዎች በሰሩባት ሴራ የባህር በሯን እድታጣ ተደርጋ ቆይታለች። በዚህም የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በሚፈለገው ደረጃ እንዳያድግ እንቅፋት ከመሆኑም ባሻገር ኢኮኖሚው እያደገ የሚሄደውን የስራ አጥ ቁጥር መሸከም ባለመቻሉ በርካታ ወጣቶች ተምረው ያለስራ ለመቀመጥ ተገደዋል።

**የባህር በር የኢኮኖሚው ዋነኛ ዋልታ እንደመሆኑ መጠን ከሶማሊ ላንድ ጋር የተደረሰው ስምምነት የወጣቶቹን የነገ ተስፋ አለምልሞታል**

ወጣቶች በሀገራቸው ላይም ተስፋ በማጣታቸው ሀገር ለቀው እንዲሸሹና እንዲሰደዱ ሆነዋል። ዛሬ ግን ወጣቱ የተስፋ ብርሃን አይቷል። ከዛሬ የተሻለ ነገ እንደሚመጣም ለመረዳት ችሏል። መንግስት ኢትዮጵያን ከ33 አመታት በኋላ የባህር በር ባለቤት እንድትሆን ማድረጉም ሊያስመሰግነው የሚገባ ነው›› ብሏል።

ቶሌራ እንደሚለውም ኢትዮጵያ ከሶማሊ ላንድ ጋር የመግባቢያ ሰነድ ስትፈርም በርካታ ኢትጵያውን የተደሰቱትን ያህል ጥቂት የሀገር ውስት ሰዎችና የኢትዮጵያን ማደግ የማይፈልጉ ሀገራት ጉዳዩን ለመጣጣል ሲሞክሩ ይታያሉ። ሆኖም ሁለቱ ሀገራት ያደረጉት ስምምነት ማንንም የሚጎዳ አይደለም። ይልቁንም አካባቢያዊ መረጋጋት የሚያመጣና ኢትዮጵያም በቀጣናው ላይ አለኝ የምትለውን የባለቤትነት ጥያቄ መልስ እንዲገኝ በር የሚከፍት ነው። ከሁሉም በላይ ግን የኢትዮጵያን ህዝብ የሞራል ስብራት የሚጠገን ነው።

ስለዚህም ወጣቱ መንግሥት ላከናወነው ተግባር ዕውቅና ሊሰጥ እንደሚገባ ወጣት ቶሌራ ጥሪ አቅርቧል። በተለይም ደግሞ ወጣቱ ሶሻል ሚዲያን በስፋት ስለሚጠቀም ኢትዮጵያን እና ሶማሊ ላንድ ያደረጉትን ስምምነት በአግባቡ ማስተጋባት አለበት። ኢትዮጵያ የባህር በር የማግኘት መብት እንዳላትና ይህን መብቷን እንድትጠቀም ድጋፍ እንዲደርግ ወጣቱ ለመላው አለም ጥሪ ማድረገት አለበት ሲል ወጣቱ ሃሳቡን አሳርጓል።

ያስሚን አህመድ የሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ የ4ተኛ አመት የህግ ተማሪ ነች። ያስሚን እንደምትለው ኢትዮጵያ የባህር በር የሚያስገኝላትን የመግባቢያ ስምምነት ከሶማሊላንድ ጋር ማድረጓን ስትሰማ በጣም ተደስታለች። ከ33 አመታት በኋላ በእሷ ዕድሜ ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት የሚያደርጋትን እድል ማግኘቷ ልቧን በሃሴት ሞልቶታል።

እንደ ህግ ተማሪነቷ ኢትዮጵያ የባህር በር ያጣቸችባቸው ምክንያቶች ተገቢ አለመሆናቸውን ትረዳለች። ኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤት እድትሆን የሚደግፉ በርካታ የህግ ማዕቀፎች ቢኖሩም እስካሁን ድረስ እንደሀገር በበቂ ትኩረት ስላልተሰራ ኢትዮጵያ ባህርና ወደብ አልባ ለመሆን ተገዳለች። አሁን ግን እንደሀገር ለባህርና ለወደብ ጉዳይ ትኩረት መስጠቱ የኢትዮጵያን የወደፊት ተስፋ እንደሚያለመልመው ትናገራለች።

ያስሚን ኢትዮጵያ ሰላማዊ አማራጮችን ብቻ በመጠቀም የባህር በር ባለቤት ለመሆን እያደረገች ያለው ጥረት ፍሬ እያፈራ መምጣቱን ተመልክታለች። ታህሳስ 22 ቀን 2016 ከሶማሊ ላንድ ጋር የተደረገው ስምምነት ኢትዮጵያ የባህር በር የማግኘት አማራጯን ያሳፋና በሰላማዊ መንገድ የኢትዮጵያ ጥያቄዎች ሊመለሱ እንደሚችሉ ተረድታለች።

ሆኖም ያስሚን እንደምትለው የኢትዮጵያ የባህር በር ማግኘት ያላስደሰታቸው ሀገራት አሉ። ከሶማሊ ሊፐብሊክ ጀምሮ ግብጽ እና የአረብ ሊግ ተጠቃሾች ናቸው። የሶማሊ ሪፐብሊክ የሚጠበቅ ቢሆንም ግብጽና አረብ ሊግ በማያገባቸው ጉዳይ ገብተው ነገሩን ለማባባስ የሚያደርጉት ጠረት ተቀባይነት ሌለው ነው። ላስለዚህም ወጣቱ ትውልድ ማህበራዊ ሚዲያን ለሀገሩ ጥቅም የሚያውልበት ጊዜው አሁን ነው።

‹‹በአሁኑ ወቅት ወጣቱ በከፍተኛ መጠን የማህበራዊ ሚዲያን በመጠቀም ላይ ይገኛል። ይህ የህብረተሰብ ክፍል ጊዜውን በማይረቡ ጉዳዮች ላይ ከማዋል ይልቅ የኢትጵያን ጥቅም በሚያስጠብቁ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጎ ሊሰራ ይገባል። የኢትዮጵያን እድገት የማይሹና አሁን የጀመረችውም መንገድ የማይዋትላቸውን ሀገራት በማውገዝ የኢትዮጵያን ትክክለኛ ገጽታ ለቀሪው አለም ማሳየት የወጣቱ ሚና ሊሆን ይገባል። ›› ትላለች ሰሚራ።

በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የሁለተኛ አመት የጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ተማሪ የሆነችው ተማሪ ማርያማዊት በጥሰት የሰሚራና ሃሳብ ትጋራለች። ኢትዮጵያ ለዘመናት ባለቤት ሆና ከቀየችበት የቀይ ባህር አካባቢ እንድትነጠል የተደረገበት መንገድ እንደዜጋ የሚያስቆጭ መሆኑን ታስዳለች።

ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ በቀይ ባህር ላይ የንግድ እንቅስቃሴ ስታደርግ የኖረችና በአካባቢውም ተሰሚነት የነበራት ሀገር ነበረች። ሆኖም ቅኝ ገዢዎች ከአንዳንድ የአካባቢው ሀገራት ጋር በመመሳጣር ኢትዮጵያን ባህር አልባ በማድረግ ከቀሪው አለም ጋር በአግባ እንዳትገናኝ አድርገዋት ኖረዋል። ይህ ደግሞ እንደዜጋ የሚያስቆጭ መሆኑን ትናገራለች።

ሆኖም መንግስት የዜጋውን ቁጭት በመንተራስ ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነቷን የምታረጋግጥበትን መንገድ መቀየሱ የሚያስመሰግነው ነው። በተለይም ለነገው ሀገር ተረካቢ ትውልድ የሀገር ጥቅም ማስጠበቅ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትምህርት የሚሰጥ መሆኑን ታብራራለች።

ተማሪ ማራማዊት አክላም ወጣቱ ትውልድ ጊዜውን በአልባሌ ከሚያሳልፍና አልፎ ተርፎም በተሳሳተ ፖለቲካ ተጠልፎ እራሱንና ሀገሩን በሚጎዳ ተግባር ውስጥ ከመግባት ይልቅ ኢትዮጵያ የምትበለጽግበትን መንገድ አብዝቶ መሻት ይጠበቅበታል።

ማርያማዊት እንደምታምነው መንግስት ከሶማሊ ላንድ ጋር የፈረመው የመግባቢያ ሰነድ በተመለከተ ወጣቱ ጥቅጠሙን በአግባቡ ሊረዳው ይገባል። የመግባቢ ሰነዱ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በማሳደግ ኢንዱስትርሪና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ እንደሚረዳ እና በዚህም ምክንት እየተማረ ላለው ወጣት የስራ ዕድል ለመፍጠር ያስችላል። ኢትዮጵያ በየዓመቱ ከ፲ነጥብ 6 ቢሊዮን ዶላር በላይ ለወደብ ታወጣለች። ይህ ገንዘብ ለሥራ ፈጠራና ለወጣቱ ስብእና ቀረጻ ቢውል ያደገችና ብሎም የበለጸገች ኢትዮጵያን በቀላል መመልከት እንደሚቻል ተማሪ ማራማዊት ታስረዳለች።

በአጠቃላይ ወጣቶቹ እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ የያዘችው ጎዳና ለወጣቱ ተስፋ ሰጪ ነው። በተለይም የባህር በር የኢኮኖሚው ዋነኛ ዋልታ እንደመሆኑ መጠን ከሶማሊ ላንድ ጋር የተደረሰው ስምምነት የወጣቶቹን የነገ ተስፋ አለምልሞታል።

ይህ የመግባቢያ ሰነድ ሲተገበር አካባቢያዊ መረጋጋት የሚያመጣና ኢትዮጵያም በቀጣናው ላይ አለኝ የምትለውን የባለቤትነት ጥያቄ መልስ እንዲገኝ በር የሚከፍት ነው። ቀጣናዊ ሰላምን በማስፈን የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የተረጋጋ እንዲሆን በር ይከፍታል።

ሆኖም የተጀመሩት ጥረቶች ፍሬ እንዲያፈሩ ሰላም ያስፈልጋል። ወጣቱ ከሁሉም ነገር በላይ ለሰላም ትኩረት ሊሰጥ ይገባል። ሀገር በጀመረችው ግስጋሴ መቀጠል የምትችለው ሰላም ሲኖር ነው። እዚህም እዚያም ያሉ ግጭቶች ሊቆሙ ይገባል። ወጣቱም በስሙ ከሚነግዱ ኃይሎች እራሱን ቆጥቦ ለሀገሩ ልማት ፊት አውራሪ ሆኖ ሊነሳ ይገባል የሚል መልክታቸውን አስተላልፈዋል።

# የምድር በረከት

## የብረትና ብረት ነክ ማዕድናት ልማትን እውን የማድረግ ጅማሮዎች

**ወርቅነሽ ደምሰው**



በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ሰፊ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች መካከል አንዱ የማዕድን ዘርፍ ነው። ይህ ሁኔታ ሀገሪቱ በዘርፉ ያላትን እምቅ የማእድን ሀብት በማልማት የሀገር ውስጥ የማእድን ፍላጎትን በመሸፈንና ከውጭ የሚመጡትን የማእድን ምርቶች በሀገር ውስጥ በመተካት ሥራ ላይ ትኩረት ሰጥታ እንድትሰራ እያደረጋትም ይገኛል።

በድንጋይ ከሰል ማእድን ልማት በኩል እየተከናወነ ያለው ተግባር ለእዚህ በአብነት ይጠቀሳል። በኢትዮጵያ ለትላልቅ ፋብሪካዎች የኃይል ምንጭ የሆነው በሲሚንቶ፣ በሴራሚክና በጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች በስፋት ጥቅም ላይ የሚውለውን ይህን የድንጋይ ከሰል ከውጭ የማስመጣቱ ሥራ ሀገሪቱን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ሲያስወጣ ኖሯል። ለማእድን ዘርፉ የተሰጠው ትኩረት በሀገሪቱ ያለውን ከፍተኛ መጠን ያለው የድንጋይ ከሰል ክምችት ወደ ልማቱ እንዲገባ እያስቻለ ነው። የድንጋይ ከሰል የማምረቱ ሥራ ለከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልገውን የድንጋይ ከሰል ምርት በሀገር ውስጥ ምርት መተካት ያስቻለበት ሁኔታም ተፈጥሯል።

ሀገሪቱ ለግንባታው ዘርፍ የሚያስፈልጋትን ብረትም ከውጭ እንደምታስመጣ ይታወቃል። መረጃዎች እንደሚያመላክቱት፤ በዓለም ላይ በየዓመቱ በአማካይ አንድ ቢሊዮን ቶን ብረት ይመረታል፤ በዓለም በከፍተኛ ደረጃ ብረት በማምረት በግንባር ቀደምነት ከሚታወቁት ሀገራት መካከል አውስትራሊያና ብራዚል ይጠቀሳሉ። በተመሳሳይ በአፍሪካ ደቡብ አፍሪካ እና ናይጄሪያ ብረትን በስፋት ያመርታሉ።

የማእድን ሚኒስቴር መረጃ እንደሚጠቁመው፤ ኢትዮጵያ ከአንድ ቢሊዮን ቶን በላይ የሚገመት የብረትና ብረት ነክ የማዕድናት ክምችት አላት። ይሁን እንጂ ሀገሪቱ በየዓመቱ አምስት መቶ ሺ ቶን ብረትና ብረት ነክ ማዕድናት ከዩክሬን፣ ከሩሲያ፣ ከቱርክና ከሌሎች ሀገሮች ታስገባለች። ይህም አገሪቱ ብረትና ብረት ነክ ማዕድናት ከውጭ ለማስገባት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪን እንድታወጣ አድርጓታል።

የብረት ፍላጎቱ ከግንባታው ዘርፍ መስፋፋት ጋር ተያያዞ እየጨመረ በመጣበት ሁኔታ በዚህ አይነት ሁኔታ መቀጠል እንደማይቻል ታምኖበት ወደ ብረት ልማት ስራም ተገብቷል። ከውጪ የሚመጡ የማዕድን ምርቶችን በአገር ውስጥ የመተካቱ ሥራ በግንባታው ዘርፍ በእጅጉ ተፈላጊ የሆነውንና ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪን ሲጠይቅ የኖረውን ይህን ብረት በሀገር ውስጥ ለማምረት ሥራ ለማዋልም ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

ለዚህም በሀገር ውስጥ ያለውን የብረት ማዕድን ክምችት ለመለየት እና ብረት ለማምረት ለሚፈልጉ ኩባንያዎች ፈቃድ የመስጠት ስራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን ከማእድን ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ይጠቁማል። ይህ ሲሆን ብረት ከውጭ ለማስገባት የሚወጣውን ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሪ ማስቀረት ይቻላል።

ሀገሪቱ ካላት የብረት ማእድን ክምችት ውስጥ ከ72 ሚሊዮን ቶን በላይ የሚሆነው የብረት ክምችት ባለባቸው አካባቢዎች ላይ የብረት ፍለጋ ለማካሄድና ለማምረት የሚያስችል ፈቃድ ለጠየቁ ኩባንያዎች የምርት ፈቃድ ተሰጥቷል። በተቀረው የብረት ሀብት ክምችት ላይ ደግሞ የጥራትና የመጠን ተጨማሪ ጥናት ማድረግ እንደሚያስፈልግ ታምኖበት እየተሰራ ነው።

ማእድኑ በአብዛኛው በአማራ እና በኦሮሚያ ክልል የሚገኝ ሲሆን፤ የብረት ማእድኑ ያለበትን አካባቢና የክምችት መጠኑን የሚያመለክት ሥራ እየተሰራም ይገኛል። ኩባንያዎች በአማራ፣በትግራይና በኦሮሚያ ክልል የብረት ማእድን የፍለጋና የምርት ፈቃድ ወስደው በሥራ ላይ እንደሚገኙ መረጃው ያመላክተ ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥም ሰቆጣ ማይኒንግ፣ኤም ኤስ ፒ ስቲልና ኮዬጻ ማይኒን ሼር ኩባንያ (Koyetsa Mining share company) እንደሚጠቀሱ መረጃቸው አመልክቷል።

የማዕድን ሚኒስቴር የኮሙዩኒኬሽና የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ አወቀ ተስፋው ብረትና ብረት ነክ ማዕድናት በኢትዮጵያ በተለያዩ ቦታዎች እንደሚገኙ ይናገራሉ። ከእነዚህ ማዕድናት መካከል ብረት፣ ታንታለም፣ መዳብ፣ ሊቲየም፣ ክሮማይት፣ኒኬል፣ ማንጋነስ ፣ ዚንክን ለአብነት ጠቅሰዋል።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ብረት ለመሰረተ ልማት በጣም

> **አሁን በኢትዮጵያ በብረት እና ብረት ነክ ማዕድናት ፍለጋና ማምረት ሥራ ላይ 18 ኩባንያዎች ተሰማርተዋል። ከእነዚህ ውስጥም 13 ኩባንያዎች በብረት እና ብረት ነክ ማዕድናት ፍለጋ ላይ የተሰማሩ ሲሆኑ፣ አምስቱ ደግሞ ብረት የማምረት ፈቃድ ወስደው እየሰሩ የሚገኙ ናቸው**

ወሳኝ ከሆኑ የማዕድን አይነቶች አንዱ ነው። ያለብረት መሰረተ ልማትን ማሰብ አይቻልም። ኢንዱስትሪና ትልልቅ ሜጋ ፕሮጀክቶችም የሚሰሩት በብረት ነው። ለሁሉም መሰረተ ልማት ግንባታዎች ብረት ያስፈልጋል። ሰፊ የልማት እቅድ ያላት ኢትዮጵያ ደግሞ ከእድገቷና ከፍላጎቷ ጋር የሚጣጣም የብረት ማዕድን አቅርቦት ያስፈልጋታል።

ኢትዮጵያ ብረትና የብረት ውጤቶችን ከውጭ እንደምታስገባ የጠቆሙት አቶ አወቀ፤ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ብረትና ብረት ነክ ማዕድናት ለማምረት ከፍተኛ ፋይናንስና ቴክኖሎጂ የሚፈልግ መሆኑ እንደሆነ ያመላክታሉ። የአገር ውስጥ ባለሃብቶች አቅማቸውን አሰባስበው ብረት ማምረት ላይ ትኩረት አድርገው መስራት እንዳለባቸው ጠቁመው፤ የውጭ ኩባንያዎችም በዘርፉ ላይ እንዲሰማሩ መንግሥት ልዩ ድጋፍ እንደሚያደርግም አስታውቀዋል።

"ለብረት የሚወጣውን የውጭ ምንዛሪ ለማስቀረት በአገር ውስጥ የሚያስፈልገውን ፍጆታ መሸፈን የሚያስችል ከፍተኛ መጠን ያለው የብረት ክምችት በሀገሪቱ ይገኛል" የሚሉት አቶ አወቀ፤ ከአንድ ቢሊዮን ቶን በላይ የብረት ማዕድን ክምችት በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች እንደሚገኝ ጥናቶችን ዋቢ አርገው ጠቁመዋል።

አቶ አወቀ አገሪቱ ያላትን የብረት ማዕድን አውጥታ እንድትጠቀም ለማድረግ ትኩረት የሚሰጠው ቀዳሚ ጉዳይ እንደሆነም ያነሳሉ። የሌሎች አገራት ተሞክሮን ስንመለከት ለብረት ማዕድን ትኩረት ሰጥተው መስራታቸው ውጤታማ አድርጓቸዋል ይላሉ ።

አቶ አወቀ የቀድሞዋ ሶቬት ህብረት /የአሁኗ ሩሲያ/ መሪ የነበሩት ጆሴፍ ስታሊን ሀገሪቱን ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለማሸጋገር በተከናወነው ተግባር በብረት ልማት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ መሰራቱን በአብነት ጠቅሰዋል። ይህም ሀገሪቱ ሁሉንም አቅሟን ብረት ላይ በማድረግ ከፍተኛ ለውጥ በማምጣት ተጠቃሚ እንድትሆን እንዳደረጋት ነው ያመለከቱት።

እንደዚህች ያሉ አገራት በተከተሉት ጠንካራ ፖሊሲ ከራሳቸው አልፈው ለሌሎችም መትረፍ መቻላቸውንም ጠቅሰው፤ ብረትን ማውጣት መቻል ኢኮኖሚውን ለማሳደግ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ይገልጻሉ። "አገራችን ለልማቷና ለዕድገቷ ሊያግዛት የሚችል የብረት ሃብት ባለቤት ነች። ስለዚህ ብረትና ብረት ነክ ማዕድናት ማልማት ላይ በትኩረት እየተሰራ ነው» ሲሉም አስታውቀዋል።

አሁን በኢትዮጵያ በብረት እና ብረት ነክ ማዕድናት ፍለጋና ማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ 18 ኩባንያዎች እንዳሉ አቶ አወቀ ይገልጻሉ። ከእነዚህ ውስጥም 13 ኩባንያዎች በብረት እና ብረት ነክ ማዕድናት ፍለጋ ላይ የተሰማሩ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ አምስቱ ደግሞ ብረት የማምረት ፈቃድ ወስደው እየሰሩ እንደሚገኙ አስታውቀዋል።

የማዕድን ክፍለ ኢኮኖሚ የአገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው ትኩረት ከሰጣቸው ክፍለ ኢኮኖሚዎች አንዱ ነው ያሉት አቶ አወቀ፤ የማዕድን ዘርፍ በዋነኝነት በውጭ ምንዛሪ ግኝት አስተዋጽኦ እንዲኖረው በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚገቡ የማዕድናት ውጤቶችን እና የማዕድን ኢንዱስትሪ ግብአቶችን በአገር ውስጥ መተካት፤ በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ ለዜጎች የስራ ዕድል በመፍጠር ለኢትዮጵያ የመጪዎቹ ዓመታት የብልፅግና ጉዞ የጎላ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ተልዕኮ ተይዞ እየተሰራ እንደሆነ ይገልጻሉ።

በዚህም በ2016 በጀት ዓመት ከውጭ የሚመጣውን የድንጋይ ከሰል ፍላጎት ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ የድንጋይ ከሰል ምርት ለመተካት የሚያስችሉ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች መጠናቀቃቸውን ጠቅሰው፤ ከመካከለኛና ከረዥም ጊዜ አኳያ የብረት ልማትን እውን ለማድረግ የሚያስችሉ የዝግጅት ስራዎችም በተያዘው በጀት ዓመት እንደሚከናወኑ አመላክተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ በ2015 በጀት ዓመት የማዕድን ሚኒስቴር የተሰጡትን ተልዕኮዎች ለማሳካት በርካታ ስራዎችን እያከናወነ ነው። በአንጻሩ ልማቱን በማካሄድ ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳረፉ ተግዳሮቶችም አጋጥመዋል።

ከተግዳሮቶቹ መካከልም የማዕድን ኢንዱስትሪዎች ለጥሬ ዕቃ፣ ለመለዋወጫ መግዣ እያጋጠማቸው ያለው የውጭ ምንዛሪ እጥረት፣ ህገ ወጥ የማዕድናት ግብይትና የኮንትሮባንድ ንግድ፣ በማዕድን አምራችና ኩባንያዎች አካባቢ የተስተዋለው የፀጥታ ችግር ይገኙበታል። ችግሮቹ በተቋማዊ አፈፃፀሙ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅእኖ አሳድረዋል።

እነዚህን ተፅእኖዎች ሊቀርፉ የሚችሉ ሥራዎችን ከሚመለከታቸው ወሳኝ ባለድርሻ አካላትና የፀጥታ ተቋማት ጋር በቅንጅት በመስራት ህገወጦችን የመቆጣጠርና ሕጋዊ እርምጃዎች ተወስደዋል ያሉት አቶ አወቀ፣ ይህ ሥራ በ2016 በጀት ዓመትም ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

በሀገሪቱ በብረትና ብረት ነክ ማዕድናት ፍለጋና ልማት ላይ ለመስማራት የሚፈልጉ አካላት የሚያተርፉባቸው በርካታ መልካም እድሎች እንዳሉም አቶ አወቀ ጠቁመዋል። እሳቸው እንዳብራሩት፤ ከእነዚህም መካከል መንግሥት ለዘርፉ የሰጠው ልዩ ትኩረት በዘርፉ ለመስማራት ለሚፈልጉ አካላት መልካም አጋጣሚ ይፈጥራል። በተጨማሪም ኢትዮጵያ እምቅ የማዕድን ሀብት ያላት ሀገር መሆኗ እና አቅምና ልምድ ያላቸው ኩባንያዎች በዘርፉ ለመሰማራት ፍላጎት እያሳዩ መምጣታቸው ሌላኛው መልካም አጋጣሚን የሚፈጥር ነው። ለማዕድን ዘርፉ የተሰጠው ትኩረትም በዘርፉ የትኛውንም የማዕድን አይነት ለማልማት ለሚሰማሩ ባለሀብቶች አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል።

እንደ አቶ አወቀ ማብራሪያ፤ አሁን ላይ ብረትና ብረት ነክ ማዕድናትን ለማምረት እየተሰሩ ያሉ ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ። በዘርፉ ለተሰማሩ ኩባንያዎች ድጋፍና ክትትል በማድረግ ወደ ማምረቱ ስራ እንዲገቡና የውል ግዴታቸውን እንዲወጡ የማድረግ ሥራዎችም ይሰራሉ። ከዚህ በተጨማሪም በማዕድን ልማት አካባቢና በማህበረሰቡ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎች እንዲቀንሱ የሚያደርጉ ተግባሮችም ይከናወናሉ።

በማዕድኑ ልማት አካባቢ የሚኖሩ ማህበረሰቦች ከልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑና ልማቱን ከአካባቢ ጥበቃና የማህበረሰብ ፍላጎት ጋር የተጣጣመና ዘላቂ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ጠቁመው፤ ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ማዕድናት ምርት በመጠንና በጥራት በማሳደግ የውጭ ምንዛሪ ማስገኘትና ከውጪ የሚገቡ ማዕድናትን በአገር ውስጥ ምርት የመተካቱ ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ይገልጻሉ።

በቀጣይም ሀገሪቷ ለብረት ማዕድን የምታወጣውን የውጭ ምንዛሪ በማዳን ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር በማሰብ መታቀዱን የጠቆሙት አቶ አወቀ፤ በዚህ ዙሪያ እየተሰሩ ያሉ ሥራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ አመላክተዋል።

መንግሥት ለማዕድን ዘርፉ ትኩረት ሰጥቶ ከውጭ የሚገቡ የማዕድን ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች የመተካት ጅማሮ ኢኮኖሚያዊ አንድምታው ከፍ ያለ እንደሆነ የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ። አሁን ላይ ሀገሪቷ ያላትን የማዕድን ሀብት ክምችት በመለየት ትኩረት ተሰጥቶቸው እየተሰሩ ያሉ ሥራዎች አበረታች እንደሆኑም ይናገራሉ። በተለይ የድንጋይ ከሰል ሙሉ ለሙሉ በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት እየተሰራ ያለው ሥራና ብረትንም እንደዚሁ በሀገር ውስጥ ለመተካት እየተደረጉ ያሉት ጥረቶች አበረታች ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ መሆናቸውን ያመላክታሉ።

**መዝናኛ**

# የብዕር ጠብታ

## የረፈደ ሩጫ

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

ጠባቧ ክፍል የተለያዩ ቀለማት ባላቸው አምፖሎች ደማምቃላች። ቦግ - እልም በሚለው የብርሃን ፍንጣቂ ውስጥ አንዲት ተስፋ-ቢስ ሴት ትታያለች። ፊቷ ላይ ሰላሳ ሁለተኛ ዓመቷን የሚያሳብቅ ሻማ ከነጭ ቶርታ ኬክ ጋር ተሰይሟል። የተለያዩ አይነት መጠጦች እንደ ክብር ዘበኛ የሙዚቃ ባንድ የእድሜዋን ቁጥር አጅበውታል። ማርታ ወደ ኋላ መለስ ብላ የመጣችበትን የሰላሳ ሁለት ዓመት የሕይወት ጎዳናዋን አየችው። ያልተኖረ ወጣትነት፣ ታይቶ የጠፋ ልጅነት ግሳንግሱን ይዞ ፊቷ ድቅን አለባት። ሁሌ ትናንትን ስታስብ ራሷን ትጸየፈዋለች። ምድር ላይ በኖረችባቸው ሰላሳ ሁለት ዓመታት ውስጥ አንድም የሚያኮራ ነገር አለማድረጓ ያበሳጫታል። ጊዜ የእሷን የእድሜ ቁጥር ከማግዘፍ ባለፈ የፈየደላት አንድም ነገር አልነበረም። ከሁሉም በላይ ደግሞ በዚህ ሁሉ ጉዞዋ ውስጥ "የኔ" የምትለውን የነፍስ አጋር አለማግኘቷ ያስከፋታል።

የእጅ ሰዓቷን አየች . . . ሰላሳ አምስት ደቂቃዎች ቀርተዋታል። ሳምሶን ሊመጣ . . . አስረኛው ወንድ ሆኖ ወደ ሕይወቷ ሊገባ እየጠበቀችው ነው። ሳምሶን ምድር ላይ ከተፈጠሩ ወንዶች ሁሉ አስፈሪ ፊት ያለው ወንድ ነው። ሲበዛ ጥቁር ነው፣ በጭስ የጠቆረ የባላገር ግርግም የመሰለ። ሁሉም ሴቶች መርጠው የተዉት የሚመስል አስቂኝ ፍጥረት፤ በጥቁር ጸጉሩ መሀል እንደ ጋን ስር እንጉዳይ ያቸፈቸፈ ሽበት የወጣበት አጭርና ዘርፋጣ ወንድ። ዘጠኝ ወሯ እንደደረሰ ነፍሰጡር ሴት ሆዱ ወደ ፊት የተነረተ ቦርጫም። ጥርሶቹ በሲጋራና ጫት የበለዙ ለንቦጫም . . . ሳምሶን ይሄን ሁሉ ነው። ይሄን ወንድ ልታገባው ነው . . .። እድሜው ስንት ይሆን? ጠፋባት። ብቻ ግን "አንቱ አትበይኝ" እያለ ሲቆጣት እንደነበር ታስታውሳለች። ከፊቱ አቀማመጥ ተነስታ ብትገምት እንኳን የእሷን እድሜ ሁለት እጥፍ ቀርጥፎ እንደሚበላ እርግጠኛ ነበረች። አባቷን ልታገባ ነው።

ከተቀመጠችበት ተነስታ ወደ በሩ ተራመደች። አፍላነት የከዳቸው ጡቶቿ እንደ ንጉሥ አሽከር አንገታቸውን ወደ መሬት አጉብጠው እንደ እሷ በትካዜ ተውጠዋል። የበሩን ጉበን ተደግፋ በሃሳብ ጭልጥ አለች። ትናንትን ገላ መቅበር ያቃታት ሴት ናት . . . ትናንት ዛሬ ቢሆን ትላለች . . . በትናንትናዋ ውስጥ የምታስተካክላቸው ብዙ ነገሮች ነበሩ። ትናንትና ሲበዛ ኩራተኛ፣ ሲበዛ ፌዘኛ ነበረች። ውበቷን ሳታስቀድም የተራመደችው አንድም ጎዳና አልነበረም። በሩ ላይ እንደቆመች ዛሬ ቢሆን ወደምትሻም አምና ተጣደፈች። የመጀመሪያውን የፍቅር ጥያቄ ያቀረበላት ወንድ ምሳሌ ነበር . . . በሩ ጉበን ላይ እንደቆመች ምሳሌ ትዝ አላት። ያኔ ገና አስራ ስምንት ዓመቷ ነበር . . .። አቤት! ድምጹን ስትወድለት ድምጹ ዛሬም ድረስ ከነውበቱ ይታወሳታል።

> **እድሜዋ ሄደ። የሰፈሩ ሰው "ቆሞ ቀር" እያለ ይሰድባት ጀመር። ከብዙ ጊዜ በኋላ የእድሜዋ ማምሻ ላይ ለአርባ አራቱ ተስላ እንደ ምንም ብላ ከአንድ ሰው ጋር ተዋወቀች**

ግን ናቀችው . . . " ሂድና ቢጤህን ፈልግ" ስትል በጓደኞቹ ፊት አዋረደችው። ያ፣ ማን ነበር ደግሞ የአንደኛ ዓመት የኮሌጅ ተማሪ እያለች አላስወጣ አላስገባ እያለ ሲያስቸግራት የነበረው? ትዝ አላት፤ ፍስሀ ነው። አሁን እሱ ምኑ ይጠላል? ምኑን ጠልታ እንዳባረረችው እሷም አታውቀውም። በሕይወቷ ከባድ ጥፋት ያጠፋችው የፍስሀን የፍቅር ጥያቄ አለመቀበሏ ይመስላታል። ዛሬ ላይም ሆነ የትናንቱ መልከመልካሙ ፍሰሀ ይናፍቃታል።

ልቧ ወደ ሌላኛው ወንድ በሃሳብ ተሸቀነጠረ። መልሀቅን ሳትጥል እዛም እዚህም ዋዠቀች። ያ፣ ማን ነበር ፊቱን ከዝንጀሮ ላይ የሰረቀ የሚመስለው፣ በቤት መኪናው እየመጣ ካልሸኘሁሽ እያለ የሚጨቀጭቃት? አስታወሰችው ማስረሻ ነው። "ይሄን ፊት ይዘህ እኔን ማግባት ያምርሃል? መጀመሪያ መስፍን እንጅነሪንግ ሄደህ ፊትህን አስቀይረህ ተመለስ" ነበር ያለችው። አቤት ግፏ . . .።

ይስሀቅ ትዝ አላት . . . በልቧ ውስጥ እውነት ቢኖር ኖሮ ይስሀቅ የእሷ ባል ይሆን ነበር። የትኛውም ወንድ እንደ ይስሀቅ እውነትን ይዞ የቀረባት አልነበረም። "የእውነት ነው የማፈቅርሽ፣ ሕይወቴን ሙሉ ካንቺ ጋር ማሳለፍ እፈልጋለሁ" እያላት ነበር የገፋችው። "የኔ ነፍስ ላንቺ ነው የተፈጠረችው። ካንቺ ሌላ ማንንም ማፍቀር አልችልም" እያላት ነበር የናቀችው። ሌላው ይቅርና እየሰደበችው የሚከተላት፣ እየናቀችው የሚያከብራት የነፍሱ የእውነት ጠል አይረሳትም። አሁን ላይ ስታስበው ይስሀቅ ወደ ሕይወቷ ፍቅርን ብቻ ይዞ አልነበረም የመጣው . . . ብዙ ነገሮችን ይዞላት ነበር አመጣጡ። ትናንት ይሄን ሁሉ ነበረች። ፍቅርን በንዋይ የምትመዝን ሴት።

የመጣላትን በረከት ስትገፋ፣ የቀረባትን ስትሸሽ ሃያ አምስተኛ ዓመቷን አከበረች። የፍቅር ታሪኳ ግን አልቆመም። ሃያ አምስተኛ ዓመቷ በአሮን ፍቅር ተጀመረ። "በፍቅርሽ ላብድ ነው፣ አንቺን ማግባት አማራጭ የሌለው መፍትሄ ነው" ሲል አሮን አማላጅ ላከባት። በቤተሰቡ ሀብትና በሚነዳው መኪና ሊያማልላት ሞክሮ አልቻለም። በመጨረሻ ብዙ ጥሮ ምሳ ሊጋብዛት ቀጠራት። ከዛን ቀን ወዲህ ግን ደግማ አላገኘችውም። ትናንትና እንዲህ ነበረች . . . በኩራትና በማን አለብኝነት የተሞላች። በነፍሷ ውስጥ ፍቅርና እውነትን አንቃ የገደለች። የሰዎች እንግልት ያስደስታታል፤ አፍቅረዋት ሲያጧት፣ ተመኝተዋት ሲከተሏት ነፍሷ ሀሴት ታደርግ ነበር። መፈለጓን፣ መወደዷን የምትለካው በሰዎች ጭንቀትና መከራ ነበር።

በሆነ አጋጣሚ ደጀኔ ከሚባል ሰው ጋር ተዋወቀች። ከብዙ ውትወታ በኋላ ሊገናኙ ተቀጣጠሩ። ከእሱ ጋር መታየት የሰማይን ያክል ከብዷት ነበር። ስትቀርበው ግን እንደምታየው አይነት አልነበረም። ማንም የሌለው ብዙ ነገር ነበረው። ሲበዛ ደግ ነበር። እሱ ጋ ያየችውን መልካምነት እስካሁን ድረስ የትኛውም ወንድ ጋ አላየችውም። ግን ምን ያደርጋል "አትመጥነኝም" ብላ አባረረችው።

እድሜዋ ሄደ። የሰፈሩ ሰው "ቆሞ ቀር" እያለ ይሰድባት ጀመር። ከብዙ ጊዜ በኋላ የእድሜዋ ማምሻ ላይ ለአርባ አራቱ ተስላ እንደ ምንም ብላ ከአንድ ሰው ጋር ተዋወቀች። በዝናብ ስትደበደብ አይቶ መኪና አቆመላት። እንደ ድሮው ቢሆን ዞራም አታየውም ነበር። ሳታመነታ ገባች . . . ቤቷ አደረሳት። ዝም ብሎ መለያየት ነውር ሆኖ ስልክ ተለዋወጡ። ሁለት ቀን ተደዋወሉ . . . በሶስተኛው ቀን "አብረን እንደር" አላት . . . "ካላገባኸኝ አብሬህ አላድርም" ብላው ተለያዩ። በሌላ ቀን ሱፐር ማርኬት ውስጥ ገባች . . . ትርፍ ጊዜዋን የምታሳልፈው ወንድ በመፈለግ ሆኗል። ለይምሰል ጉዳይ ያላት ትምሰል እንጂ በምትሄድበት ሁሉ ፍላጎቷ ባል የሚሆን ወንድ መተዋወቅ ነበር። ቶሎ ተዋውቃ ቶሎ ማግባት ትሻለች . . . "ቆሞ ቀር" ከመባል ለመዳን። ግን እንዳሰበችው የሆነ ምንም ነገር አልነበረም። ሰላሳኛ ዓመቷን ለብቻዋ አከበረች።

አንድ ቀን ራሷን ጠልታ ስለሞት እያሰበች ለብቻዋ ቁጭ ብላ ነበር . . .

ከኋላዋ አንድ ድምጽ አስደነበራት።

ወደ ኋላዋ ዞረች፤ ሲጋራ ከሚያጨስ አንድ ሰው ጋር ተገናኘች። ከሳምሶን ጋር . . .

በሰላሳ ሁለተኛ ዓመቷ ላይ "እመጣለሁ" ብሏት እየጠበቀችው ነው . . . ይመጣ ይሆን?

# ዓለም አቀፍ

## ለ200 ዓመታት ጦርነትን ያላስተናገደችው ስዊድን መጪው ዘመን አሳስቧታል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በረዥም የሰላም ዘመን የምትታወቀውና ጦርነት ጨርሶውኑ እየረሳች መጥታለች የምትባለው ሰሜን አውሮፓዊቷ ስዊድን ከሰሞኑ ስለ ጦርነት በስፋት መነገሩ ዜጎቿን አስጨንቋል።

በተለይ የሀገሪቱ ሁለት ከፍተኛ የጦር መኮንኖች 'ስዊድን ለአይቀሬው ጦርነት መዘጋጀት አለባት' የሚል ማስጠንቀቂያ ከተናገሩ በኋላ ጉዳዩ በሕዝብ ዘንድ ትልቅ መነጋገሪያ ሆኗል።

አንዳንዶች መጪው ዘመን ከ200 ዓመታት በላይ በሰላም ለኖረችው ስዊድን አስጊ ነው ሲሉ ይናገራሉ።

የሲቪል መከላከያ ሚኒስትር የሆኑት ካርል አስካር ቦህሊን በአንድ የደህንነት ጉባዔ ላይ እንደተናገሩት 'ስዊድን በመጪው ዘመን ጦርነት ሊያጋጥማት ይችላል።'

ይህን ሃሳብ የሚጋሩት የጦሩ ዋና አዛዥ ጄኔራል ማይክል ባይደን ሁሉም ስዊድናውያን ለጦርነት ቢያንስ የሥነ ልቡና ዝግጅት ያድርጉ ሲሉ አሳስበዋል።

ይህን የሁለቱን ወታደራዊ መኮንኖች ሃሳብ 'ተጨባጭነት የሌለው' ሲሉ ያወገዙት ተቃዋሚዎች በሰላም ሀገር የጦርነት ነጋሪት መጎሰም ትክክል አይደለም ብለዋል።

የቀድሞዋ የስዊድን ጠቅላይ ሚኒስትር ማክደሊና አንደርሰን ለስዊዲን ቴሌቪዥን እንደተናገሩት በአካባቢው የደህንነት ሁኔታው አሳሳቢ መሆኑ የማይካድ ቢሆንም ጦርነት ደጃችን መጥቷል ብሎ ማሰብ ግን ትንሽ የተጋነነ ነው።

ብሪስ (Bris) በሚል ምሕጻር የሚታወቀው በስዊድን የልጆች መብት ተቆርቋሪ ድርጅት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ልጆችና አዳጊዎች በቀጥታ ስልክ እየደወሉ መጪው ጦርነት እንዳሳሰባቸው ይነግሩናል ብሏል።

ድርጅቱ ከዚህ ቀደም እንዲህ ዓይነት ጥሪዎች ደርሰውት እንደማያውቁና ምናልባት ወጣቶች በቲክቶክና ሌሎች ማኅበራዊ ሚዲያዎች ስለ ጦርነት የሚያዩት ነገር እያስጨነቃቸው እንደመጣ እንገምታለን ብሏል።

የድርጅቱ ቃል አቀባይ ማጃ ዳህል ለቢቢሲ እንደተናገሩት እንዲህ ዓይነት የጦርነት ወሬ ለአዋቂዎች ይዘው ሲመጡ ለልጆች በምን መንገድ መነገር እንዳለበት ቀድመው ማሰብ ነበረባቸው ብለዋል።

ምንም እንኳ ይህ የጦርነት ስጋት ድንገት መነጋገሪያ ቢሆንም ጦርነትን ለረሱት ስዊድናውያን የጦር መኮንኖቹ ማሳሰቢያ የማንቂያ ደውል ሆኗል።

ከሁለት ምዕተ ዓመት በላይ ደንበኛ ጦርነት ውስጥ ገብተው የማያውቁት ስዊድናውያን ኔቶን ሙሉ በሙሉ ጫፍ ደርሰዋል።

የሚጠብቁት የቱርክ ፓርላማና የሀንጋሪ ፓርላማ ጥያቄያቸውን እስኪያጸድቅ ብቻ ነው። የስዊድን የጦር አዛዥ ንግግራቸው አዲስ እንዳልሆነ ተናግረዋል።

ከአንድ ወር በፊት ምሥራቅ ዩክሬንን የጎበኙት የጦር አዛዡ ሀገራቸው የዩክሬን ፓይለቶችን እንደምታሰለጥን ተናግረዋል። ስቶክሆልም ግሪፐን የተባሉ ተዋጊ ጄቶችን ለዩክሬን ለመስጠት እያሰበች እንደሆነም ጠቅሰዋል።

ጄኔራል ባይደን እንደተናገሩት ስለ መጪው ጦርነት ስናገር ስጋት ለመጫር ሳይሆን ሁሉም ስዊድናዊ የራሱን የሥነ ልቡና ዝግጅት እንዲያደርግ ለማስቻል ነው ብለዋል።

ፊንላንድ ኔቶን በይፋ የመቀላቀሉን ሂደት ያጠናቀቀች ሲሆን ሞስኮ ነገሮች ከቁጥጥር ውጭ ከወጡ ፊንላንድ ዋጋ ለመክፈል የመጀመርያዋ ሀገር ትሆናለች ስትል



አስጠንቅቃለች።

የዩክሬን ፕሬዚዳንት ዘለንስኪ ስዊድንና ሌሎች አጋር ሀገሮች በርካታ የጦር መሣሪያ እንዲያመርቱና በጋራ ጠንካራ ኃይል እንዲገነባ እንደሚሹ አስገንዝበዋል።

የስዊድን ጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስተርሰን በበኩላቸው በያዝነው የፈረንጆች ዓመት ሀገራቸው ኔቶ ያስቀመጠውን የወታደራዊ ወጪ መጠን እንደሚያሟሉ ቃል መግባታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

ኔቶ ሀገሮች ከጠቅላላ ዓመታዊ ጥቅል ምርታቸው 2 እጁን ለወታደራዊ ወጪ እንዲያውሉ ይፈልጋል። ስዊድን በዚህ ስሌት ለወታደራዊ ወጪ ከዚህ ቀደም ከምትመድበው እጥፍ ገንዘብ መመደብ ትጀምራለች ማለት ነው።

አስካር ጆንሰን የተባሉ በስዊድን መከላከያ ዩኒቨርሲቲ የጦር ጉዳዮች ተንታኝ እንደሚሉት አሁን በስዊድን የሚወራው የጦርነት ስጋት 'አይሆንም የሚባል አይደለም' ይላሉ። ይሁንና ስጋቱ ሊያጋጥም የሚችለው ሩሲያ በዩክሬን የጀመረችው ጦርነት ሲቋጭና ሠራዊቷን በድጋሚ ስትገነባ እንዲሁም አሜሪካ የተባበሩት አውሮፓ ሀገራትን በጦርነት መርዳት ስታቆም ሊሆን የሚችል ስጋት ነው።

"እነዚህ ነገሮች አይሆኑም አይባልም፤ ሊከሰቱ ይችላሉ" ይላሉ አስካር ጆንሰን።ስዊድን ለመጨረሻ ጊዜ ጦርነት የገጠማት ከጎረቤት ኖርዌይ ጋር ለአጭር ጊዜ ሲሆን ይህም እንደ አውሮፓዊያኑ በ1814 ዓ/ም ነበር። ስዊድን በ2ኛው የዓለም ጦርነት ገለልተኛ አገር ነበረች።

# ስፖርት





## የሠራተኛው የበጋ ወራት ውድድሮች እሁድ ይጀመራሉ

**ቦጋለ አበበ**

የ2016 የሠራተኞች የበጋ ወራት ስፖርታዊ ውድድሮች ከነገ በስቲያ በኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ በሚከናወኑ የተለያዩ መርሀ-ግብሮች ይጀመራሉ። ለረጅም ወራት በሚካሄደው የበጋ ወራት ውድድሮች ወደ ሰላሳ የሚጠጉ የሠራተኛ ስፖርት ማህበራት እንደሚሳተፉ አረጋግጠዋል።

በየዓመቱ ጠንካራ ፉክክር የሚያስተናግደው የእግር ኳስ ውድድር በዘንድሮው የበጋ ወራት በርካታ ማህበራት ተፋላሚ ይሆናሉ። በዚህ በእግር ኳስ ውድድር ሃያ አንድ ማህበራት ተሳታፊ ሲሆኑ ፉክክሩ በሁለት ዲቪዚዮን ተከፍሎ ይካሄዳል። በአንደኛ ዲቪዚዮን ዘጠኝ ማህበራት ተፎካካሪ ለመሆን ተዘጋጅተዋል፣ በሁለተኛው ዲቪዚዮንም አስራ ሁለት ማህበራት ናቸው ተፎካካሪ የሚሆኑት። የቤት ውስጥ የስፖርት ውድድሮችን ጨምሮ በአስር የስፖርት አይነቶች ፉክክር በሚደረግበት የበጋ ወራት ውድድር በሁለቱም ፆታ በአትሌቲክስ፣ ጠረጴዛ ቴኒስ፣ ቮሊቦል፣ ዳማ፣ ቼስ፣ ገበጣ፣ ገመድ ጉተታና ሌሎችም የስፖርት አይነቶች ከአንድ ሺ አምስት መቶ በላይ ሠራተኞች ተሳታፊ እንደሚሆኑ የኢሰማኮ የስፖርት ክፍል ኃላፊ አቶ ዮሴፍ ካሳ ተናግረዋል።

ውድድሩ ከነገ በስቲያ በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ መክፈቻውን ቢያደርግም በቀጣይ ቀናት በተለይም የእግር ኳስ ውድድሮች በጎፋ ካምፕ ሜዳ፣ በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት፣ ስብስቴ ነጋሲ ትምህርት ቤት እንደሚካሄዱ አቶ ዮሴፍ አስረድተዋል። የቤት ውስጥ ውድድሮችም ሜክሲኮ በሚገኘው የመብራት ኃይል ክበብ የሚካሄዱ ይሆናል።

የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን (ኢሰማኮ) በየዓመቱ ሶስት የተለያዩ ስፖርታዊ ውድድሮችን ያከናውናል። ለረጅም ጊዜ የሚካሄደውና በርካታ ሠራተኞችን የሚያሳትፈው




**የሠራተኛው የበጋ ወራት ውድድሮች ከነገ በስቲያ በድምቀት ይጀመራሉ፣**

የበጋ ወራት ውድድር አንዱና ዋነኛው ሲሆን፣ ዓለም አቀፉን የሠራተኛ ቀን (ሜይ ዴይ) አስመልክቶ የሚካሄደው ውድድር ሁለተኛው ነው። ሌላው በክረምት ወራት በተለይም በወንጂ ስቴድየም የሚካሄደው ሀገር አቀፍ ውድድር ትልቅ ትኩረት የሚሰጠውና ሠራተኛውም በጉጉት የሚጠብቀው መድረክ ነው።

እነዚህ ውድድሮች ሠራተኞች እርስ በእርስ እንዲተዋወቁ፣ ጤናው የተጠበቀና አምራች ዜጋን ለማፍራት ፣ የሠራተኞችን አንድነት ለማጠናከር፣ የልማት ተቋሞቻቸውን ማስተዋወቅና የባለቤትነት ስሜታቸው እንዲጠናከር ዓላማ በማድረግ የሚከናወኑ ናቸው።

በኢትዮጵያ ረጅም እድሜ ካስቆጠሩ አንጋፋ የስፖርት መድረኮች አንዱ የሆነው ይህ የሠራተኞች ውድድር በዚህ ዘመን ሠራተኛው በስፖርት የሚያደርገው ተሳትፎ ለሚሠራበት ድርጅት ውጤታማነት የሚኖረውን አስተዋጽኦ የጎላ እንደሆነ አሠሪዎች እንደሚረዱት ይታመናል። በመሆኑም ስፖርቱ የሠራተኛውን አንድነትና ለጋራ ጉዳይ አብሮ የመቆም ባህሉን እንደሚያጠናክር ይነገራል። በሀገሪቱ የተለያዩ ተቋማት ውስጥ የሚያገለግሉ ሠራተኞች በስፖርታዊ እንቅስቃሴ እየተሳተፉ ጤናማ፣ ንቁና አምራች ዜጎች እንዲሆኑ ውድድሮችን ማሰናዳት ውጤታማ ሠራተኛ ማፍራት እንደሚያስችል ይታመናል።

በአሠሪና ሠራተኛው መካከልም ጥሩ ግንኙነት እንዲዳብር በማድረግ ምርትና ምርታማነትን በመጨመር ለኢንዱስትሪ ሰላም መስፈን የላቀ አስተዋጽኦ እንደሚኖረውም ይታመናል። የሠራተኛ ማህበር ዓመታዊ ውድድሮችን ማዘጋጀት ሠራተኛውን እርስ በርስ ከማቀራረብ አንፃር የጎላ ሚና እንዳለውም ባለፉት በርካታ ዓመታት በተካሄዱ ውድድሮች ለመታዘብ ተችሏል።

በኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ኮንፌዴሬሽን በሚሰናዱ ውድድሮች ላይ ተቋሞቻቸውን ወክለው በሚካፈሉ ተወዳዳሪዎች መካከል ከተቋም ጋር ያለውን መቀራረብ፣ ልምድ ማካፈል እንዲሁም ለተለያዩ ክለቦች ግብዓት የሚሆኑ ስፖርተኞች ማፍራት የቻለ ውድድርም ነው። በውድድሩ በሚካፈሉ ተቋማት መካከል በሚፈጠረው ፉክክር ምክንያትም ሠራተኛው የተሻለ ውጤት ይዞ ለመምጣት ሲሽቀዳደምና ለዓመታዊ ውድድሩ ዝግጅት ሲያደርግ መመልከት የተለመደ ነው።

የሠራተኛው የስፖርት መድረክ እንደ ሀገር በርካታ ፋይዳዎች ያሉት ቢሆንም በብዙ ፈተናዎች ውስጥ እየተካሄደ አሁን ያለበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ከነዚህ ፈተናዎች አንዱ የተሳታፊ ማህበራት ቁጥር በሚፈለገው ደረጃ አለማደጉ ነው። የተሳታፊ ማህበራትን ቁጥር ወደላቀ ደረጃ ለማሳደግ የኢሰማኮ የስፖርት ክፍል እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ ጥረት ማድረጉን እንደቀጠለ የሚናገሩት አቶ ዮሴፍ፣ “እኛ በርካታ ማህበራት እንዲሳተፉ ጥያቄ እናቀርባለን የሚመጡት ግን በሚፈለገው ልክ አይደለም፣ ይህ ከበጀትና አሰሪዎች ለስፖርት ካላቸው አመለካከት ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል፣ ለስፖርቱ ግንዛቤና ጥሩ አመለካከት ያላቸው አሰሪዎች ሠራተኞችን የማሳተፋቸውን ያህል የሌላቸውም አሉ።” በማለት ምክንያቱን ያስረዳሉ።

አዳዲስ ማህበራት ወደ ስፖርቱ የመምጣታቸውን ያህል በተለያዩ ምክንያቶች ነባር የነበሩ የሚቀሩበትም ሁኔታ አለ። የነዚህ አብዛኛው ችግር የበጀት ነው። ይሄ ሲስተካከል ግን ወደ ስፖርቱ ለመመለስ ፍላጎት አላቸው።

እንደ አቶ ዮሴፍ ገለፃ፣ የሠራተኛው ስፖርት በኮቪድ ምክንያት ለሶስት ዓመት ተቋርጦ ባለፈው ዓመት ለመመለስ ትልቅ ትግል ተደርጓል። ተሳክቶም ዘንድሮ ከኮቪድ በኋላ ለሁለተኛ ተከታታይ ዓመት የበጋ ወራት ውድድሮች ይካሄዳሉ። ያም ሆኖ የሠራተኛውን ስፖርት የሚያካሂድበት የራሱ የማዘውተሪያ ስፍራ አለመኖር ሁሌም የስፖርቱ ትልቅ ችግር ነው። ኢሰማኮ ሠራተኛው ስፖርታዊ ውድድሮቹን የሚያደርግበት የራሱ ማዘውተሪያ ስፍራ ባለቤት እንዲሆን ባለፉት ዓመታት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ብዙ ጥረቶች ቢደረጉም አሁንም ችግሩ ሊቀረፍ አልቻለም።